# የማይጨው

# ቁስለኛ።

ለ፳፭ኛው ዓመት የዘውድ በዓል
ኢዩቤልዩ የተዘጋጀ

ከመኰንን ዘውዴ።

አ.አ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ.ም

በብርሃንና ሰላም
በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ።

# የማይጨው ቁስለኛ።

ለ፳፭ኛው ዓመት የዘውድ በዓል

ኢዮቤልዩ የተዘጋጀ

ከመኰንን ዘውዴ።

አ.አ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ.ም

በብርሃንና ሰላም

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘመነ መንግሥት በ፳፭ኛው ዓመት ይህ መጽሐፍ ታተመ።

ታጥቀናል ለማክበር ኢዮቤልዩን፤
ለመግለጽ ቀርበናል ደስታችንን፤
በግጥም በመዝሙር እንደዚህ እያልን፤
ዘለዓለም ኑርልን ብርሃናችን፤
ጥበብን መግበን አሳዳጊያችን፤
አባታችን ጠቅል መልካም መሪያችን።

በግርማው ተፈሪ የሆነው ሰው ማነው
ብርሃንና ሰላም ኃይለ ሥላሴ ነው።

ዕድሏማ ንግሥት እቴጌ መነን፤
የልዑላን እናት የነአስፋ ወሰን፤
ሰማነው አየነው መልካም ተግባርዋን፤
ጸሎትዋ ተሰምቶ አዳነን እኛን።

ዕድለ መልካም ነህ ተከተል ግቡን፤
ከፍቶልሃል ጠቅል የባሕር በሩን፤
አድርገናል ተስፋ አስፋ ወሰኑን።

# ማውጫ።

ምዕራፍ ፩። ....................................................................................10
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ስለ ነፃነቱ ደሙን ለማፍሰስ ማይጨው ሲዘምቱ። ....................................................................................10
ምዕራፍ ፪። ....................................................................................11
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከጦር ሜዳው ወደ ጦር ሠፈር ሲመለስ። ....................................................................................11
ምዕራፍ ፫። ....................................................................................17
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከጦር ሠፈር ሲደርስ። ..........................17
ምዕራፍ ፬። .................................................................................... 19
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ነጭ ለባሽ ወታደር በጉዞ ላይ። ........ 19
ምዕራፍ ፭። .................................................................................... 24
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ አሸንጌ ከጓድ ጦር ሲገናኙ። ............ 24
ምዕራፍ ፮። .................................................................................... 29
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከአሸንጌ ከጦር ሠራዊቱ ጋር ሲጓዙ። 29
ምዕራፍ ፯። ....................................................................................31
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በወይዘሮ እንዳላጣሽ ቤት። ...31
ምዕራፍ ፰። .................................................................................... 34
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ከእግዜር ሰጠኝ ጋር ሲጓዙ። 34
ምዕራፍ ፱። ....................................................................................37
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ደሴ አቅራቢያ ሲደርሱ። .......37
ምዕራፍ ፲። .................................................................................... 38
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ደሴ ከተማ እንደገቡ። .......... 38
ምዕራፍ ፲፩። .................................................................................... 39

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከካሣዬ ጋር በአባቱ ቤት ሲደርስ።.... 39
ምዕራፍ ፲፪።........................................................................ 40
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል ወሬ እንደተጠሙ። ............................................................ 40
ምዕራፍ ፲፫።........................................................................ 43
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ከወይዘሮ የምሥራች በሰሙት ወሬ እንደተጠቀሙ። ................................................................ 43
ምዕራፍ ፲፬።........................................................................ 47
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከካሣዬ ጋር ወደ አባቱ መኻታ ቤት ሲሔድ።.......................................................................... 47
ምዕራፍ ፲፭። ......................................................................52
በአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ምክር መላው ቤተሰብ እንደተባበረ።52
ምዕራፍ ፲፮።........................................................................ 60
አገረ ገዥው የአገር ተወላጅ ለጐሐይቅ ሲደርሱ።....................... 60
ምዕራፍ ፲፯።........................................................................ 63
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ የተዘረፈ ልብሱን ለመቀበል ወደ ለጐሐይቅ ሲሔድ ....................................................................... 63
ምዕራፍ ፲፰።........................................................................ 68
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ከቤታቸው ሲደርሱ።........... 68
ምዕራፍ ፲፱። ...................................................................... 74
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ወደ ሸዋ ለመምጣት ሲያስቡ። ............................................................................................ 74
ምዕራፍ ፳።........................................................................ 78
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በአቶ ልመንህ ቤት።............ 78
ምዕራፍ ፳፩። ...................................................................... 82

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ሁለተኛ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ ሲሔዱ። ........ 82
ምዕራፍ ፳፪። ........ 87
የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ የግርማዊነታቸውን መምጣት ሲጠባበቁ። ........ 87
መዝሙር። ........ 91
ስለደራሲው በጥቂቱ........**Error! Bookmark not defined.**
የደራሲው ሥራዎች ........ 94

ተማሪ ለቀለም አባቱ ሊያበረክት የሚችለው ከአእምሮ ባፈለቀው ዕውቀቱ ያገኘውን ራሱ የሰራውን የእጁን ሥራ ስለሆነ ለግርማዊነትዎ ፳፫ኛ የዘውድ በዓል ኢዮቤልዩ መታሰቢያ የግርማዊነትዎን ታሪክ ከሚመለከቱት ጦርነቶች አንዱን ታሪካዊ የሆነውን የማይጨውን ጦርነትና ሁኔታውን የምታስታውሰውን ይህችን «የማይጨው ቁስለኛ የተባለችውን ትንሽ መጽሐፍ ለግርማዊነትዎ በትሕትና አበረክታለሁ።

ባሪያዎ።

መኰንን ዘውዴ።

# መግለጫ።

በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድና ቸርነት በአርበኞች መንገድ ጉለሌ የሚገኘው አሁን የመድኃኔ ዓለም ትምህርት ቤት የተባለው ፲፱፻፳፫ ዓ.ም በፊት የቦይስካውት ትምህርት ቤት ነበር።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም በቦይስካውት ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ጊዜ ከገቡት ተማሪዎች አንዱ ሆኖ በአዳሪነት በትምህርት ቤቱ ገባ።

በሥጋ ከወለዱት አባትና እናት የበለጠ የሚያስቡ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሳምንት ሁለት ቀን ትምህርት ቤቱን እየጐበኙና የፍሬ ምግብ እየሰጡ በሚያደርጉት አባታዊ ጉብኝት፤ በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ከሦስት መቶ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች በግርማዊነታቸው ከፍ ያለ የአባትነት ሥራ እየተደሰቱ ትምህርታቸውን በትጋት ሲከታተሉ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈም ከበረከቱ ተሳታፊ ሆኖ ትምህርቱን ሲከታተል ቆየ።

ጠላት ውድ አገራችንን ለመውረር ቀደም ያለ ድርጅት አድርጎ መነሣቱ በቁርጥ ሲረጋገጥ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በግራዝማች አበራ ግዛው አዛዥነት ለተመረጠው ወታደር አሠልጣኝነት ከትምህርት ጓደኞቹ ጋር ተመረጠ። ዕውቀቱን ለወገኖቹ አካፍሎ ካሠለጠናቸው ወታደሮች ጋር የአምሳ እልቅና መዓርግ አግኝቶ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ማይጨው ዘመተ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ልማት፤ ለሕዝባቸው ዕድገት ብለው በዘረጉልን የትምህርት ገበታ ልዩ ልዩ ዘመናዊ ትምህርት ስንከታተል፤ ግፈኛው ጠላት ጥንታዊ ቂሙን ሊበቀል አገራችንን

በግፍ ለመውረር በመነሣቱ ትምርህርታችን ተቋረጠ እያለና በጠላት የግፍ ሥራ እያዘነ ለአገሩ ደሙን ሊአፈስላት ዘመተ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ምንም እንኳ ቆስሎ በሕይወቱ ከጦርነቱ ቢመለስ በሥጋዊ አካሉ ላይ በየጊዜው የደረሰበት ሥቃይ ብዙ ስለ ሆነ፤ በታሪኩ ውስጥ ይገኛል።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ በጠላት ወረራ ምክንያት ትምህርቱ ይቋረጥ እንጂ፤ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በተመሠረተው ትምህርት ቤት ገብቶ ዕውቀት ገብይቷል።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ታሪክ ከእውነተኛው ከማይጨው ዘመቻ ታሪክ የተወሰደ ሲሆን፤ ለአንባቢዎች እንዲጥም ጥቂት ማጣፈጫ ልብ ወለድ ታሪክ ተጨምሮበታል። የጠላትን የግፍ ሥራ ከመሠረቱ የሚያውቅና የተከታተለ፤ የጠላት የግፍ አፈጻጸም ከዚህ አሥር አጠፌታ ብልጫ እንዳለው በዘመኑ ላይ መከራው የገረፉቸውና አባት፤ እናት፤ ወንድም እኅት ባል፤ ወይም ሚስት የሞተባቸው አይዘነጉም። ይህንንም ታሪክ በልብ ወለድ መንፈስ አዘጋጅቼ ለገናናው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የ፳፫ኛ ዓመት የዘውድ በዓል ኢዮቤልዩ መታሰቢያ ለማበርከት ያሳሰበኝ፤ በዘመኑ ላይ የጠላትን የግፍ ሥራ ያዩና የግፉ ተካፋይ ሆነው ሕይወታቸው በተአምራት ለተረፈው ማሳሰቢያ እንዲሆን ነው።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድል አድራጊነት ኢትዮጵያ በአዲስ ዘመን አዲስ የሆነ ዘመናዊ ሥራዋን በምታፋጥንበት በአሁኑ ዘመን በሺ የሚቆጠሩ ወጣቶቿ በአገር ውስጥና በውጭ አገርም በትምህርት ገበታ ላይ ይገኛሉ። የጠላት የግፍ ሥራና ሙሉ ታሪኩ በብዙው በታሪክ መጻሕፍት ተጽፎ የዛሬ ወጣቶች የተከታተሉትም ቢሆን፤ ይህች «የማይጨኤ ቁስለኛ» የተባለች መጽሐፍ የጠላትን የግፍ ሥራ ከብዙ በጥቂቱ በአጭሩ የምታስታውስ ስለሆነች ትናንት የደረሰብንን

መከራ ለማስታወስና በዘመኑም ላይ ያልነበሩት ባለፈው ጊዜ በወገኖቻቸው ላይ የደረሰውን የጠላት የግፍ ወረራና የአሁኑን የነፃነት ኑሮ ለማመዛዘን የሚረዳ ማስታወሻ ስለምትሆን ነው።

ሰው ሰው ነው ሊባል የሚቻለው ወደ ኋላ ያለፈውን መከራ ሲያስታውስ ነው። ያለፈውን መከራ ያስታወሰ እንደሆነ አሁን ያለንበትን ኑሮ ጣዕሙን ያውቃል ሰው ደካማ ፍጥረት ሲሆን አቅሙን መጥኖ አይኖርም። አቅምን ለመመጠን ያለፈውን አስታውሶ፤ አሁን ያለንበትን፤ ሲያመዛዝን ነው። ያለፈውን እያንዳንዳችን አስታውሰን ከአሁኑ ጋር ስናመዛዝነው ሀብታችን ንብረታችን፤ ሕይወታችን አገራችንና፤ ነፃነታችን፤ ንጉሠ ነገሥታችን ብቻ መሆናቸውን በጥልቅ እንገነዘባለን።

ደራሲው።

# ምዕራፍ ፩።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ስለ ነፃነቱ ደሙን ለማፍሰስ ማይጨው ሲዘምቱ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ከንጉሠ ነገሥቱ በተቀበለው አደራ ስለ ነፃነቱ እስከ መጨረሻው ጠብታ ደሙን ለማፍሰስ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም በማይጭው ዘምቶ በጦሩ ሜዳ ከጠላት ጋር ግንባር ለግንባር ገጥሞ በቈራትነትና በጀግንነት በመትረየስ ጠላትን ሲያርገበግብ ውሎ ወደ ማታ በጠላት መድፍ ቈሰለ።

ግዳጁን የፈጸመው ጀግና ወታደር ስለ ፈሰሰው ደሙና ስለ ቈሰለው አካሉ ምንም ፀፀት ሳይሰማው ከአባት በተወረሰ ታሪካዊ ጀግንነት ግራና ቀኝ ሆነው በመትረየስና በልዩ ልዩ መሣሪያ ጠላትን እንደ ቅጠል ያረግፉት የነበረውን የጦር ጓደኞቹን በዓይኑ ቢቃኝ አጣቸው።

ከምሽጉ ወጥቶ ቢመለከት ወታደራዊ ሥራቸውን ፈጽመው ጠላት ከሥር፤ የጦር ጓደኞቹ ከላይ ሆነው ተቃቅፈው እንደወደቁ አየ። ከወገንና ከጠላት ጦር የወደቀውን ተመልክቶ የኢትዮጵያ ጀግኖች ሆይ እንደ ጤፍ ክምር ጠላትን አንዱን ባንዱ ላይ እንባብራችሁ የሞት ጽዋችሁን ተቀበላችሁ። ይህ የጀግንነት ሥራችሁ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለዘለዓለም ሲተላለፍ ይኖራል። ከዓርባ ዓመት በፊት የነበረውን ቂም በመበቀል የአገራችንን ታሪክና ነፃነት ለመደምሰስ የረጅም ጊዜ ድርጅት አድርጎ የመጣውን ጠላት አመድ አድርጋችሁ ግዳጃችችሁን ፈጸማችሁ። ስለ አገራችሁ ነፃነት ደማችሁ በጀግንነትና በሰማዕትነት ፈሰሰ። ሥራችሁ ለትውልድ ኵራትን የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ ደማችሁም፤ በኢትዮጵያ ላይ በደረሰው የግፍ ወረራ ምክንያት ስለ ነፃነታቸውና ሃይማኖታቸው

መሥዋዕት ሆነው በጦር ሜዳ ከወደቁት ኢትዮጵያውያን ጋር የጠቢባን ጠቢብ፤ የኃያላን ኃያል ለሆነ ለልዑል እግዚአብሔር ድምጹን ያሰማል።

ጐን ለጐን በተሰለፍንበት የጦር ሜዳ የጀግንነት ተግባራችሁን ፈጽማችሁ ስትለዩኝ ሥጋዬ ቆስሎ ደሜን እያንጠባጠብኩ ታሪካዊ የሆነ ሥራችሁን በማየት የዓይን ምስክር በመሆን ብቻ የናንተን ዕድል ባለማግኘቴ በዕድሌ ተማረርኩ።

ከንግዲህ ወታደራዊ ግዳጃችሁን ለመፈጸም ዕድል አግኝታችሁ ጠላትን ተንተርሳችሁ አንቀላፋችሁ። የናንተ የጀብዱና የጀግንነት ሥራ የመጀመሪያውን የታሪክ ገጽ ይዞ ሲያስታውሳችሁ ይኖራል። የኢትዮጵያን ነፃነትና ሃይማኖትዋን ለማጥፋት የመጣው ጠላት ኃይሉ ተሰብሮ ንጉሠ ነገሥትዋ ድልን በጨበጡ ጊዜ ታሪካቸውን ለትውልደ ትውልድ ሲያስተላልፍ የሚኖር የስማቸው መታሰቢያ ሐውልት በዚያች ሥፍራ ይቀረጽላቸዋል ሲል ትንቢታዊ ቃል ተናግሮ ተሰናበታቸው።

# ምዕራፍ ፪።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከጦር ሜዳው ወደ ጦር ሠፈር ሲመለስ።

የኢትዮጵያ ጦር በሕገ ወጥነት በተጣለ የመርዝ ጢስ ተፈትቶ ከሞት የተረፈው ወደ ሠፈር መመለሱን የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ የተረዳው የጀግንነት ትግላቸውን ፈጽመው በሞት ጥላ ሥር ካረፉት ጀግኖች መካከል ቆሞ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻውን ንግግር ሲያረግ ነው።

ከጦሩ ሠራዊት ጋር ለመቀላቀል በምርኩዝ ጥቂት ምዕራፍ እልፍ ሲል በሜዳው ሁሉ የጠላት ሬሳ ተከምሮ የኢትዮጵያ ጀግኖች አልፈው አልፈው ከጠላት ሬሳ ጋር አንቀላፍተው አየ። የወገን ጦር ከመውደቁ ጎዘን

ሲሰማው እንደ ገብስ ክምር የበዛው የጠላት ወገን ሬሳ ስለሆነ ኅዘኑ ተከፈለለት።

«ያገሬ የኢትዮጵያ ጀግኖች ሕግ በከለከለው የመርዝ ጢስ ሳትሰቃዩ ጠላት በግንባር ቢገጥማችሁ ኖሮ በጀግንነትና በቈራኝነት መንፈስ ጠላትን አስጨንቃችሁ ፈጽማችሁ ታጠፉት ነበር። ምን ይሆናል ከሰማይ የሚወርደውን የመርዝ ካፊያና የቦምብ መርግ ለመከላከል ጊዜው አልፈቀደልንም» እያለ ጉዞውን ሲቀጥል ከፍ ያለ አደጋ የደረሰበት ቊስለኛ ሲያጣጥር አገኘው።

ልቡ በኀዘን ፍልፃ ስለ ተወጋ የራሱን ድካምና ስቃይ ረስቶ ቀረብ ብሎ ቊስለኛውን ለማነጋገር ሞከረ። ቊስለኛው በመርዝ ጢስ አካሉ ደክሞ በመትረየስ ሁለት ታፋው ደቅቆ ከፍ ያለ ስቃይና ፃዕር ይሰማው ነበር፤ የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ እቁስለኛው አጠገብ ተቀምጦ፤ ከወደቀበት ቀና አድርጎ ለማነጋገር ሲሞክር ከቊስሉ በቀር የመርዙ ጢስ በጣም አድክሞት ስለ ነበረ ሳይቻለው ቀረ።

የአገሬ ልጅ ጀግናው ወታደር ሆይ፤ ከወደቅህበት ቀና አድርጌ ላእንጋግርህና ልረዳህ ፈልጌ ነበር። ነገር ግን ሥጋዊ ኃይሌ የደከመ ስለ ሆነ ሳይቻለኝ ቀረ። እንግዲህ በምን ልርዳህ? ምንስ እንድረዳህ ትፈልጋለህ? እስካሁን ያጋጠመኝ የጀግንነት ሙያቸውን ፈጽመው በሞት ጥላ ሥር ያረፉትን ጀግኖች ነበር፤ አሁን ግን ከፍ ባለ ሥቃይ ሆነህ አንተን ስላገኘሁህ በውነቱ መፈጠሬን አስጠላኝ።

የአገርህን ወራሪ ጠላት በአገርህ መሬት በጀግንነት ስትከላከል በደረሰብህ ከባድ አደጋ ልረዳህ ካለመቻሌ ይልቅ ከኔ የተሻለ የሚረዳህም ልጠራልህ ሳልችል ያለ አንድ ርዳታ ሥቃይህን ብቻ በማየት ልቤ በኀዘን ተነካ።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ ሆይ፤ በኔ ላይ የደረሰው አደጋ ከፍ ያለ ሆኖ ብሰቃይም፤ አንተም ቁስለህና በመርዝ ጢስ ተለብልበህ የደከምክ

ስለሆነ፤ ከራስህ አልፈህ እኔን ልትረዳ እንደማትችል አውቃለሁ። እኔ የምፈልገው ርዳታ ጠብታ ውሃ ሲሆን፤ ይህንን ልታደርግልኝ እንደማትችል አምናለሁ።

ቊስለኛው ወታደር ኧረ ለመሆኑ በአሁኑ ሰዓት አንተ ከወዴት መጣህ? ከማንኛውም ከፍለ ጦር ነህን? እስካሁን ቊስለኛ ሲተላለፍ አላየሁም እንዴትስ ለመዳን ቻልክ?

<u>የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤</u> ወንድሜ ለእግዚአብሔር ምን ይሳነዋል። እንኳን እኔን ካንተ የተሻልኩትን ቊስለኛ አንተንስ ካለህበት ከባድ ሥቃይ በቅፅበት ሊያድንህ ይችል የለምን? ለመነጋገር ችለህ ከጠየቅኸኝ የሚሰማህ ሥቃይ ትንሽ እንኳን ቢከፈልልህ ጥቂት ላነጋግርህ። በግራዝማች አበራ ግዛው በሚመራው የጦር ሠራዊት መትረየስ ተኳሽ ስለ ነበርኩ፤ ከጠላት ምሽግ በጣም ቀርቤ የወታደርነት ግዳጄን ስፈጽም ወደ ማታ በመድፍ ጥይት ቆሰልኩ። መትረየሴም፤ በመድፍ ጥይት አመድ ሆነች። ሰውነቴን ለይቼ ሳውቅ ባዳምጥ ተኩስ ቆምአል።

ምርኩዝ ፈልጌ ብዘዋወር የጦር ጓደኞቼ የጠላትን ወታደር ርስ በርሱ አደራርበው እነሱም በላዩ ላይ ወድቀው አየሁ። በመካከላቸው ቆሜ ስለ ጀግንነታቸው ጥቂት ደቂቃዎች ብቻዬን ካጉረመረምኩ በኋላ ጉዞዬን ስቀጥል የጠላት ወታደር ሬሳ እንደ ቅጠል ረግፎ ጀግኖቹ የኢትዮጵያ ወታደሮች እልፍ እልፍ ብለው ተኝተዋል። በተፈጥሮ ባሕርይ ጀግንነት ገንዘባቸው የሆነውን የኢትዮጵያ ወታደሮች የጠላትን የጦር ወታደር እንደምን አድርገው እንዳሰጡት አይቼ እየተገረምኩ ስጓዝ አንተን አጋጠመኝ።

<u>ቊስለኛው፤</u> የኔ ሕይወት ሕይወት ካለው ጋር አይመዛዘንም። ነፍስና ሥጋ ካልተለያዩ ሕይወት አለው መባል አይቀርም። ሎጥን ከሰዶምና ከገሞራ ጥፋት መርጦ ያወጣ አምላክ ከዚህ ከእሳት ውስጥ አንተን አድኖ

የኔን ሥጋዊ ሥቃይና የጦር ጓደኞችህን የጀግንነት አወዳደቅ ለማየት በመመረጥህ ዕድለኛ ነህ። የድል ዕድል ለጊዜው ከኛ ርቃ የጦር ሠራዊቱ በመርዝ ጢስ ቢፈታም እስከዚያው በተደረገው ጦርነት የወገን ጦር እንደተጎዳ ይገመት ይሆናል። አንተ አብዛኛውን በዓይንህ ያየህ ስለ ሆንክ ድልም ባያገኝ የጠላትን ያህል የኢትዮጵያ የጦር ወታደር ጉዳት እንዳልደረሰበት አይተሀል።

የኔ ሕይወት ተስፋ ያለው ሕይወት አይደለም። ሥቃዩ ስለ ተሰማኝ ከወንድሜ ርዳታ ጠየቅሁ። ለሁሉም ነገር ቈራጥ መሆን ያስፈልጋል። የሚሰማኝን ሥቃይ ከአንተ ጋር በመነጋገር ልረሳው እሞክራለሁ። ብቻዬን ቀርቼ ሥቃይ ከሚሰማኝ አንተ አጠገቤ ባለህበት ጊዜ ውስጥ ነፍሴ ከሕይወቴ እንድትለይ እመኛለሁ።

ይህ ከመሆኑ በፊት አንድ ነገር ልገልጥልህ አስታወስኩ። ጠላታችን ከመስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም መረብን ተሻግሮ ወረራ ስለ ጀመረ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መስከረም ፳፫ ቀን ለሕዝባቸው ባስታወቁት የክተት አዋጅ ነፃነት የሌለው ሕዝብ በጠላት እጅ እንደ ከብት እየተነዳ ካገሩ የሚወሰድ በገዛ ምድሩ ርስቱን በሌላው ሰው እጅ እያየ ጢሰኛ ሆኖ በውርደትና በመረረ ኀዘን የሚኖር በከብቱና በንብረቱ በመቃብሩ መሬት እንኳን የማያዝበት ለዘሩ የሚተላለፍ ባርነት ወርሶ የሚኖር ሕዝብ ነው። ስለዚህ እንኳን ሌላው ሰው ንጉሥም ጳጳስም ቢሞት ሰው ነውና ዘሩ ይተካበታል። ያገር ነፃነት ሲጠፋ ግን ምትክ የሌለው ባርነቱም ከዘር ሲተላለፍ ከማይሞት ስም ጋራ የሚኖር፥ የዘለዓለም እስር ነውና ጠላት ምንም በሚሻሪያው ቢኮራ ሞት የጋራ መሆኑ የታወቀ ነው» ብለው የተናገሩት ንጉሣዊ ቃል ታወሰኝ። ነፃነታችን በባዕድ እጅ ተገፋ ሰንደቅ ዓላማችን በባዕድ እግር ተረግጣ፥ የመቃብር መሬት እስከ መነፈግ ከመድረስ ጠላትን በተቻለ መጠን ጨፍጭፈን ከዚህ ረግፈን ብንቀር ለኛ ክብር ለትውልድ ኲራት እንሆናለን። ይህ

የግርማዊነታቸው ንግግር በአሳቤ መጥቶ ሲሰማኝ የደረሰብኝን ሥቃይ ረሳሁት።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> አሁን በዝርዝር የተርናገርከው የግርማዊነታቸው ንጉሣዊ ቃል ልቤን መታው። አስበህም ስለ ተናገርከው አመሰግንሃለሁ። የነፃነት ጸጋ መገፈፍ፥ በአገራችን የመቃብር መሬት እስከ መነፈግ እንደሚያደርስ የተረጋገጠ ነው። የአገራቸውን ሞት ሳያዩ ከጠላታቸው ጋር አንገት ለአንገት ተቈላልፈው የሞቱት ሞቱ ሊባል አይቻልም።

የአገራቸውን ሞት ዓይተው በአገራችው የመቃብር መሬት እስከ መነፈግ የሚደርስባቸው የሞት ሞት ሞትዋል። እንደ ጦር አርበኞች በጦር ሜዳ በጀግንነት ውዬ የሞትን ጽዋ አጥቼ ሕይወቴን ለማዳን በምርኩዝ እጓዛለሁ። የጠላትን የጭቆና አገዛዝ ከሚፈጸምባቸው አንዱ እኔ መሆኔ አይደለምን?

<u>ቍስለኛው፤</u> ይህንንም ስላልኩህ እንደ ጦር ጓደኞቼ አልሞትኩም ብለህ መጸጸት አይገባህም። ይሁላችንም በጦር ግንባር ረግፎ መቅረት ለአገራችን አይጠቅማትም። ውርደቱን በልበ ሡሌዳ ጽፎ ስለ አገር ነፃነት እስከ መጨረሻው ጠብታ ደምን ማፍሰስ ይገባል። አገር የምትረዳው በአሁኑ ጦርነት ብቻ ሳይሆን በቈራጥነት መንፈስና ተስፋ ባለመቍረጥ ጠንክሮ በመከከከልም ጭምር ነው። በአርበኝነት ሆኖ የጠላትን አገዛዝ መቃወም ከዚህ የበለጠ ጦርነትና የጀግንነት ሥራ ነው። ግማሹ የፖለቲካ ጦርነት ሲያደርግ ግማሹ የጀግንነት ጦርነት በማድረግ በማናቸውም በኩል ከፍ ያለ ኅብረት የተደረገ እንደሆነ የጠላት አገዛዝ ኃይሉ ይሰበራል። ከዚህ ባለመሞትህ እግዚአብሔርን አመስግነህ ስለ አገራቸው ነፃነት ሕይወታቸውን ለማሳለፍ ቆራጥነት ካላቸው ጋር ሆነህ በዱር በገደል እንድትከላከል አሳስብሃለሁ።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ እስካሁን አንነጋገር በምን ክፍለ ጦር ውስጥ እንደሆንክ አልነገርከኝም፤ ብትገልጥልኝ በወደድኩ፤

ቍስለኛው፤ አስቀድሜ ልገልጥልህ አስቤ ነበር። ነገር ግን እኔ ከዚህ ስለሆንኩ መታወቄ እንደማያገለግልህ ገምቼ ሌላውን ነገር መነጋገር ወደድኩ። ከጠየቅሽኝም የክብር ዘበኛ ባልደረባ ነኝ። አሁን ስቃዩ ስላስጨነቀኝ ልገላገለው ነው ብሎ ወዲያው ነፍሱ ከሥጋው ተለየች።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ አስቀድሞ ሥቃዩን ባየ ጊዜ መንፈሱ በኀዘን ተነክቶ ሲያዝን ባነጋግረው ጊዜ አሳቡ ተከፈለለት። ጥያቄውን ከመጨረሱ በፊት ለአንድ ጊዜ ጥያቄው አጭር መልስ እንደ ሰጠው የዕረፍት ጊዜ መቃረቡን ነግሮት በጀግንነትና በቈራጥነት ባሕርይ እንደተሸፈነ የሞት ጽዋውን ተቀበለ።

በጦር ሜዳ ከፈጸመው የጀግንነት ሥራው በላይ ግርማዊነታቸው የተናገረውን ታሪካዊ ቃል በአእምሮው ቀርጾ ያንን ያህል ሥቃይ ሲሰማው የጀግናውን ወኔና ልበ ሙሉ ቆራጥነት የሥቃዩን ስሜት አሳቡን ሊያስቀረው ባለመቻሉ በሚሰማው ሥቃይ መካከል ያገሩን ውርደትና ጥፋት፤ በባዕድ እጅ መውደቅ የመቃብር መሬት እስከ መነፈግ እንደሚያደርስ አስታውሶ በማረፉ የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ ትካዜ ገብቶት ጥቂት ደቂቃዎች ያህል በአሳብ ባሕር ውስጥ ዋኘ። አገርን መርዳት በዚህ ጦር ሜዳ ብቻ አይደለም። በፖለቲክና በአርበኝነትም ሆኖ ከዚህ የበለጠ የጀብዱ ሥራ ለመሥራት ይቻላል፤ ያለውን ቃል በአሳቡ ውስጥ እያመላለሰ ወደ ጠቅላይ ጦር ሰፈር ጉዞውን ቀጠለ።

# ምዕራፍ ፫።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከጦር ሠፈር ሲደርስ።

ትውልድ ካለፈ በኋላ የሚከተለውን ትውልድ ፍሬውን የሚያገኝበትን የሕይወት ዛፍ መትከል ይገባል። አምላክ ዳር ድንበሯን በባሕር ከልሎ የሰጠን አገር ከሁሉ ይልቅ ልትከበር ይገባታል።

ተጣጥሮ መነሣት ፈጽሞ ሳይወድቁ ነው። የሰው አገር ሳንፈልግ በታሪክና በጂዖግራፊ አቀማመጥ የማይለያዩትን የባሕር በሮቻችንን ሰጥተን አልበቃው ብሎ አገሪቱን በሙሉ ለመውረር እስከዚህ ለመጣ ጠላት ሱሪ የታወቀ ወንድ ቀርቶ ሴቶችም ቢሆኑ የሴትነት ባሕርያቸውን ለውጠው በጀግንነትና በቈራጥነት ተስፋም ባለመቁረጥ መከላከል ግዴታቸውና ሊፈጽሙት የሚገባ ተግባራቸው ነው።

ነገር ካለፈ ይቆጫል። ጊዜ ካመለጠ ይጸጽታል። ጊዜ በእጅ ያለ ገንዘብ አይደለም፤ እጅ ሳይፈለቀቅ የማታጣ ረቂቅ ነገር ነው። የሚያልፍ ቀን የማያልፍ ስም ይሰጣል። የሚገባ ግዳጁን የፈጸመ ጀግናው ከፍ ባለ ሥቃይ ላይ ወድቆ ሰውነቱ በደም ተለውሶ ሲሠቃይ ሥቃዩን ከምንም ሳይቆጥረው ወደ ፊት እንደ ምን መከላከል እንደሚገባ ተስፋ ያለው የጅግንነት ምክሩን ጥሎ በቅፅበት ሔደ። ጀግናው ከጀግኖች የኢትዮጵያ የጦር ወታደሮች ጋር የማያልፈውን ስም ተክሎ በመርዝ ጢስ የተጐሳቀለው ሰውነቱና በመትረየስ ጥይት የደቀቀው የታፋው ቁስል ሳይሰማው በአገሩ ፍቅር ልቡ እየተቃጠለ ለወደፊቱ አደራ ጥሎ አለፈ።

ጀግናው ወታደር ሆይ ግዳጅህን ፈጽመህ ሞትህን ሕይወት የሚያደርግና ስምህን ዘለዓለም በአፍለኛነት የሚያስጠራ ሥራ ሠርተህ በማለፍህ ዕድለኛ ነህ። በሰጠኸን ምክር ተመርተን ለአገራችን ልንፈጽምላት የሚገባን ግዳጅ ፈጽመን ስማችንን በታሪክ መዝገብ ላይ

ለትውልድ ተክለን እንድንከተልህ አትርሳን ብሎ የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ ተሰናበተው።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ ወደ ጦር ሠፈር ጉዞውን ሲቀጥል ጊዜው ምሽት ስለ ነበረ የጨረቃዋ ብርሃን የፀሐይዋን ያህል ስለ አበራችለት እስራኤልን በእሳት ብርሃን የመራቸው አምላክ እኔንም ቢመርጠኝ ነው እንጂ የጨረቃዋ ብርሃን ይህን ያህል አይደምቅም እያለ ከጦር ሠራዊቱ ሠፈር ቢደርስ የጦር ሠራዊቱ ከመርዝ ጢስና ከቦምብ ናዳ ለመዳን ለጊዜው ያገኘው መከላከያ በሌሊት መጓዝ ስለ ነበረ በጨረቃዋ ብርሃን የጦር ሠራዊቱ ተጉዞ ሠፈሩ ምድረ በዳ ሆኖ አገኘው።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ ካለፈው የባሰ ፈተና ሰለገጠመው አስቀድሞ የተናገረውን አስታወሰ። እንደ ጦር ጓደኞቼ የሞት ጽዋ ተነፍጌ ፈራሽ አካሌ በቁስልና በደም ተጨማልቆ በመትረየስ ፋንታ የእንጨት ምርኩዝ ጓደኛዬ ሆኖ ስጓዝ ተባራሪ ጥይት አግኝቶ ካልሆነ ቦታ ላይ የወደቅሁ እንደሆእን በዕድሌ እንዴት አዝን ብሎ ቁስለኛውን ወታደር ወታደራዊ ግዳጁን ፈጽሞ ከማለፉ በፊት የነገረው ስለታወሰ፤ መንፈሱ በአሳብ ማዕበል ተዋጠ፤ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ያለ መከራ ጻጋ፤ ያለ ድካም ዋጋ አይገኝም። የምድር ሰው ሁሉ ከንቱ ሲሆን ከንቱ ያልሆነ መሥራት አያቅተውም። በተድላ በኖርኩበት ጊዜ ወዳጆቼ የበዙ ሆነው ሳልፈልጋቸው በዙሪያዬ ይገኙ ነበር፤ በመከራ ማዕበል እኔና አገሬ በተዋጥን ጊዜ ወዳጄና አነጋጋሪዬ መከራዬ ብቻ መሆኑን ማወቅ አለብኝ። እግዚአብሔር ይሁን ያለው ነገር ጊዜ ይጠብቃል እንጂ ምንም ቢሆን ሳይሆን አይቀርም።

ስለዚህ አሳቤን ወደ ኋላ ከመመለስ ወደ ፊት መግፋት ይሻለኛል ብሎ ጉዞውን ቀጠለ። አምስት ምዕራፍ ያህል እንደ ሔደ ከጦር ሠራዊቱ በቦምብና በመርዝ ጢስ ተቋርጦ የቀረ የቦምብ ርችት የገረፈው ሰው አገኘ። ሰው ያስባል፤ እግዚአብሔር ይፈጽማል። በውድቅት ሌሊት በዚህ

ጫካ ብቻዬን ከጓዴ ከመከራ ጋር እየተወያየሁ ከአሁን አሁን ያውሬ ራት እሆናለሁ እያልኩ በሀሳብ ባሕር ውሥጥ ስዋኝ አነጋጋሪ አገኘሁ። ተመስገን ጌታዬ ከዚህ የከፋ ነገር አታሳየኝ ብሎ ከወዴት እንደመጣና በምን ክፍለ ጦር ውስጥ እንደ ነበረ ጠየቀው።

ከጦር ሠራዊቱ ተቋርጦ በደረቅ ሌሊት ብቻውን ከአሁን አሁን የዱር አውሬ ቀለበኝ እያለ ወደ ፊት ሲገሠግሥ የሚያነጋግር ወገኑ የሆነ ስለ አገኘ እግዚአብሔር ሆይ ቸርነትህ ለዘለዓለም ነውና የእጅህን ሥራ ቸል አትበል። እንደ ጊዜህ ኃይልህ ይሁን ብሎ በአንቃዕድዎ ከተናገረ በኋላ በነጭ ለባሽ ውሥጥ የከምባታ ጦር ነኝ ብሎ ለጥያቄው መልስ ሰጠው።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ እግዚአብሔር በርሱ ያመኑትን ስለ ታላቅ ስሙ ቸል የማይል ስለሆነ እኔም ብቻዬን እየተነጋገርኩ የዱር ዓራዊት ራት የሆንኩ እየመሰለኝ በምጥ ላይ ሆኜ ስጓዝ አንድ ዓይነት በሆነ የጭንቅ ምጥ ላይ በመገናኘታችን በሃይማኖት ብትጸና ሃይማኖትም በአንተ ቢጸና የምትሻውን ሁሉ ታገኛለህ የተባለው ቃል አስታወስኩ። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና እየተጨዋወትን ጉዞአችንን እንቀጥል።

# <u>ምዕራፍ ፬።</u>

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ነጭ ለባሽ ወታደር በጉዞ ላይ።

<u>ነጭ ለባሽ ወታደር፤</u> እንደሰመመን ወደ ኋላ የሚጐትተን ድካማችን እንዲከፈልልን ለሕዋሳታችን ፈውስ የሚሆን ጣዕም ያለው ጨዋታ አሰማኝ።

<u>የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤</u> ወንድሜ ደስ የሚያሰኝ ጥያቄ ስላቀረብክልኝ በውነቱ በምስጋና ተቀብያሀለሁ። በአንደበታችን ሌላ ነገር

አግብተን ብንነጋገር ንግግሩ ስለማይጥመን የአገራችንን ጉዳይ ብቻ ብንነጋገር እወዳለሁ።

ነጭ ለባሽ ወታደር፤ ከአገራችን ጉዳይ በቀር ዛሬ ኧረ ለመሆኑ ምን ልንነጋገር እንችል ይመስልሃል! የኔም አሳብ የአገራችንን ጉዳይ ብቻ መነጋገር ነው።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ አገር ሲኖር መኖር አገር ሲሞት መሞት አለብን። እኖራለሁ ማለት በአገር ነው። ያለ አገር፤ ያለ ንጉሥ ሕይወት የለም። ቤት የሚቆመው በምሰሶና በማገር ሲሆን ሰውም የሚቆመው በነፃነትና በአገር ነው። ጉልቻ የላቀው፤ አመድ ያጠለቀው ማነው ቢሉ አገር የሌለው ነዋ፤ ይባላል። ለአገር መሞት በተፈጥሮ ግዴታ ከምንሞተው ጋር አይቆጠርም። የሰው ልጅ ጊዜውን በመከራ ካላሳለፈ ታሪክ የለውም። ታሪክን የሚወልድ መከራ ነው። መከራም፤ የጽድቅ ማጣሪያ ነው። ሰውም የመከራ መጽሐፍ ማለት ነው። ታሪካዊ ሥራ ለመሥራት ቈራጥ መሆን ያስፈልጋል። የሰው ልጅ ጊዜውን በመከራ ካላሰለፈ ታሪክ የለውም። አባቶቻችን ከአርባ ዘመን በፊት ይህንኑ ጠላታችንን በአድዋ የጦር ሜዳ እንደ ቅጠል አራግፈው አፈር አስግጠው የድል አክሊል ተቀዳጁ። የአባቶቻችን ጀግንነት አስከብሮን ኖረ። ጊዜ የሰወረውን ጊዜ ይገልጸዋል። ጠላት እስከ ጊዜው ታጋሽ መስሎ ቢታይ ቂሙን አይረሳምና አስታውሶ ለመቀበልና አገራችንን ለመውረር መጣ።

በታሪክ ተያይዞ እንደመጣው የኢትዮጵያ ነገሥታት ጀግንነትን በደም የወረሱት ስለ ሆነ በጦር ሜዳ ተሰልፈው ይዋጋሉ፤ ያዋጋሉ። ግርማዊ ንጉሠ እንገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ «ከኛም ከጦር ሠራዊታችን መካከል ለመገኘትና ፈተናውን ለመካፈል ቈርጠን ስለተነሣን ይህንኑ እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ መላው ዓለም ተረድቶታል» ሲሉ የተናገሩትን ንጉሣዊ ቃል ለመፈጸም ከጦር ሠራዊቱ ጋር በጦሩ ሜዳ ተገኝተው ጠላትን አርገብግበውታል።

የተፈጥሮ ጀግንነቱ በዓለም ደምቆና አሸብርቆ የታወቀው የኢትዮጵያ የጦር ወታደር ከሰማይ የሚርከፈከፍበትን የመርዝ ጢስና የቦምብ ናዳ በቈራጥነትና በትዕግሥት ተቀብሎ እስከ መጨረሻው ጠብታ ደሙን አፍስሶ ቢዋጋም፤ በዓለም ሕግ በተከለከለው የመርዝ ጢስ ወደ ኋላ መመለስ ግድ ሆነበት።

በሃይማኖት የተፈተነች ተስፋ ሁል ጊዜ ድል አድራጊ መሣሪያ ናት፤ ለጊዜው ድሉ ለጠላትም ቢሆን እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አሳልፎ በጠላት እጅ አይጥላትምና ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የድል ሰይፍ አስታጥቆ ድሉን በድል ይመልሰዋል። ከንብ የሚገኘውን ማር እንደምንወድ ከንብ የሚገኘውንም ሥራና ትጋት መውደድ አለብን። ንብ አውራውን አያስነካም። አውራውን ተቃዋሚና ፈላጊ ሲመጣ በኅብረት ተከላክሎ ያባርረዋል። እንደዚሁም ነፃነታችንንና አውራችንን ለማጥፋት የመጣውን ጠላት ተባበረን ማባረር አለብን።

ብዙዎቹ የጦር ጓደኞቼ ወታደራዊ ግዳጃቸውን ፈጽመው ጠላትን እየተንተራሱ አንቀላፍተዋል። ከዚያ መካከል የታሪክ ምስክር ልሆን እግዚአብሔር በከሃሊነቱ አትርፎ ጉዞ ስቀጥል ሁለት ታፋው የደቀቀ ወታደር ግዳጁን ፈጽሞ ነፍሱ ከሥጋው ሳትለይ በከባድ ሥቃይ ላይ ሆኖ ሲያጣጥር አገኘሁት። ልረዳው ብሞክር አቅም ስለ አጣሁ አጠገቡ ተቀምጬ ሳነጋግረው ፃዕሩና ጭንቀቱ ሳይሰማው «ለአገር መከላከልና አገርን መርዳት በዚህ ጦር ሜዳ ብቻ አይደለም። ኅብረታዊ በሆነ የጀብዱ ሥራ በውስጥም በውጭም በፖለቲክ በኢትዮጵያ ተራራዎችና ጅረቶች እየተዘዋወሩ በአርበኝነት ጠላትን ማሰቃየትና መቀነስ ያስፈልጋል» ሲል የነገረኝ ነገር በአእምሮዬ ተቀርጾአል።

አስቸጋሪ ነገርን ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል ለማሸነፍ መጋደል ያስፈልጋል። ጀግናው ወታደር እንደተናገረው በዱር በገደል እየተዘዋወርን

ጠላትን አስጨንቀን ካላጠፋን ሕይወታችን ሕይወት አለው ሊባል አይችልም።

<u>ነጭ ለባሽ ወታደር፤</u> በሰፊው ዘርዝረህ የነገርከኝን ይህን ታሪካዊ ቃል የእግዚአብሔር መልአክ እያቀበለህ እንደሆነ ነው እንጂ፤ ከፍ ያለ አስተያየት የተመረኰዘ ንግግር በአሁኑ ሁኔታህ ከአሳብህ ይፈልቃል ብዬ አልገምትም። ከአንተም ንግግር ይልቅ፤ አንተ የዓይን ምስክር ሆነህ ያየኸው ቊስለኛ ጀግናው ወታደር የነገረህን ስትገልጽልኝ የጀግናውን ንግግር በግዙፍ እንደሰማሁት ሆኖ በፊቴ ውል አለብኝ።

መገፋትን የታገሠ ቢወድቅም ይነሣል። ማለፍ ባይኖር የጠሉት ቀን ነዋሪ ሆኖ ያስጨንቅ ነበር። ይዘገያል እንጂ ድል ሁል ጊዜ ከእውነት ወገን ነው። እስከ ሞት ድረስ መታመን የሕይወት አክሊል ያቀዳጃል።

«ባለቤት ካልጮኸ ጐረቤት አይረዳም፤ እንደ ተባለው እኛ በዱር በገደል ሆነን ጠላታችንን ካልተከላከልን የነፃነት ጸጋችን ተገፎ ይቀራል። እግዚአብሔር የሚኖረው ራሱን ከሚረዳ ሰው ጋር ነው። ራሳችንን በራሳችን ለመርዳት በቈራጥነት ከተነሣን እግዚአብሔር ጥላ ከለላችን ሆኖ ይረዳናል። እግዚአብሔር እንዳልተለየንና አሳልፎ እንዳልሰጠን የምናውቀው የጦር መሪአችን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በሕይወት ጠብቆ ከመርዝ ጢስና ከቦምብ የተረፈውን የጦር ሠራዊታቸውን ይዘው መመለሳቸውን ስናይ ነው።

እግዚአብሔር እስራኤልን ከፈርኦን እጅ ሲያስወጣቸው ሙሴን አሥነስቶ ነው። «እኔም እላችኋለሁ። አትደንግጡ ከርሳቸውም አትፍሩ፤ እግዚአብሔር አምላካችሁ በፊታችሁ የሚሄደው እርሱ ሰለናንተ ይዋጋል» ብሎ በሙሴ አድሮ እሥራኤልን እንዳወጣቸው፤ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አድሮ እኛንም ከጠላት አገዛዝ እንደሚያወጣን ተስፋ አድርገን የራሳችንን ግዳጅ መፈጸም አለብን።

በሃይማኖት የተፈተነች ተስፋ ሁል ጊዜ ድል አድራጊ ናት። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዘዋወሩ ፈተናን መታገስ የድል ማግኘት ተስፋ ያስገኛል።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ ለቀጠሮ ያብቃን ያገር ጉዳይ እንደ እግር እሳት የሚያግንገበግብ ስለሆነ የአገራችንን ጉዳይ ስንነጋገር ድካም ሳይሰማን መንገዳችንን አቈራርጠን። አሁን ሌሊትም ነጋ። አውሮፕላን አደጋ እንዳይጥልብን ጥግ እንያዝ።

ነጭ ለባሽ ወታደር፤ ይህ አሁን የደረስንበት አሸጌ ነው። ባሕሩ የጠራ ሰማይ መስሏል። ቤተ ክርስቲያን በአቅራቢያችን ስላለ፤ ወደዚያው ጠጋ ብለን እንረፍ።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ መልካም ነው እንዲያውም የጦር ሠራዊቱ ከዚህ የሠፈረ መሰለኝ ምክያቱም የሰው ድምፅ ተሰማኝ።

ነጭ ለባሽ ወታደር፤ እውነትህን ነው፤ የተራራው እግርጌ ዙሪያና ዓፀደ ቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያውን በሰው ተመልቶአል።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ ከጦር ሠራዊቱ ጋር ከተቀላቀልን፤ አንተም የክፍል ጦርህን ፈልግና ከጓደኞችህ ጋር ተቀላቀል። እኔም የክፍሌን ጦር ልፈልግ በማናቸውም ረገድ ይላላከኝና ይረዳኝ የነበረው ከአዲስ አበባ ድረስ ያመጣሁት ካሣዬ በሕይወት እንዳለ ልፈልገው ተባብለው አሸንጌ ላይ ተለያዩ።

# ምዕራፍ ፫።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ አሸንጌ ከጓድ ጦር ሲገናኙ።

የአምሳ እለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ በአሸንጌ የጓድ ጦሩንና የግል ረዳቱን ባገኘው ጊዜ ካሣዬ ከሰማይ እንደ ወረደ ቈጠረው እንጂ፤ ከምድር እንደተገኘ አልገምተም፤ በተገናኙ ጊዜ፤ አንገቱ ላይ ተጠምጥሞ ሙተሀል ብዬ እርሜን አውጥቼ ዕድሌን አያማረርኩ በሐዘን ተጨብጨ የጭነት በቅሎህንና የጭነት አህያህን ከመርዝ ጢስ ከቦምብ እየተከላከልኩ ለወላጆችህና ለዘመዶችህ ምን ብዬ እነግር ይሆን እያልኩ በአሳብ ሜዳ ስዋልል ከሰማይ እንደወረደ በመካከላችን በመገኘት በጣም ደስ አለኝ። አሁን ሰዓቱ ረፋድ ስለሆነ ቦምብ ጣይ አውሮፕላን መጥቶ አደጋ እንዳይጥልብን ሰዋራ ቦታ ይዣለሁና በዚያ አረፍ እንበል።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ በመገናኘታችን እኔንም ደስ ብሎኛል። ነገር ግን ደስታችን ፍጹም ደስታ ስላይደለ በጣም ደስ አይበልህ። እኔ ብሞትም በኔ የሚተካ ከእኔ የበለጠ ጀግና ኢትዮጵያ ትወልዳለች። እኔ ሞቼ አገሬ ኢትዮጵያ ከሞት በዳነች ደስታህና ደስታዬ ፍጹም በሆነ ነበር። ለወላጅጆቼ የምትነግረው ወሬ ጨንቆህ በአሳብ ሰመመን ላይ መሆንክን ገለጥክልኝ። እኔን ይዘህ ከወላጆቼ ዘንድ አሁን ስትሔድ ምን ብለህ ልታወራ ይሆን? ወላጆቼ እኔ ሞቼ አገሬ ብትድን እንጂ፤ የኔን መትረፍ ያገሬን ሞት እንደማይወዱ እመን። ስለዚህ ወደ ቤተሰቦቻችን ስንሔድ በየግንባራችን የሚታየው ኀዘን እንጂ ደስታ አለመሆኑን አስብ። ዕድለኞች ጀግኖች ወታደሮች ጠላቶቻቸውን አስቀድመው እየተንተራሱ ተኝተዋል። ስም ከመቃብር በላይ ይውላል እንደተባለው ስማቸውን ከመቃብር በላይ በወርቅ ቀለም አስጽፈው በማለፋቸው ዕድለኞች ናቸው። የኛ ትግልና የኛ ፈተና ግን ከምን ዕድል ላይ እንደሚጥለን ገና አላወቅንም።

ኧረ ለመሆኑ በዚህ እስከ ስንት ሰዓት እንቀመጣለን? የጠላት ሰላይ አውሮፕላን እያንዣበበ ወረቀት ይበትናል። ምን እንደሚል ለማወቅ ወረቀቱን ባገኘን መልካም ነበር።

ካሣዬ፤ ተሰምቶኝ የነበረውን ደስታ በኃዘን መልክ የሚለውጥ ከባድ ነገር ተናገርከኝ፤ ኧረ ለነገሩ አገር ትሞታለችን? እኛ ከሞት ከተረፍንና ተመልሰን አገራችን ከገባን ዕድለኞች ነን ብዬ ነበር፤ አሁን በገለጽከው አነጋገር እኛ ሙተን ቀርተን አገራችን ብትድን የበለጠ ሙያና ክብር መሆኑን አስረዳኸኝ። እውነትህን ነው እኛማ በጉንፋንና በእንቅፋት እንሞት የለምን? በውነቱ የተናገርከው ቃል ሕሊናዬን መታው። የገዛ ራሱን ኃዘን ልብ ያውቃል። ሌላ ሰው ሊመረምረውም አይችልም።

በዚህ የምናሳልፈው ጊዜ ቀኑን ሙሉ ነው የብርሃንን ቀናችን በጨለማ ስለ ተለወጠ ሌሊቱን እንጓዛለን። ቸር እግዚአብሔር እስራኤልን ቀን በደመና ሌሊቱን ሁሉ በእሳት ብርሃን መርቷቸው የለምን? እኛንም እንደዚሁ በማይመረመር ቸርነቱና ከሐሊነቱ ይመራልና።

ሰው ሁሉ ራሱን ለመከላከል ከተጠለለበት እየወጣ የጠላት ሰላይ አውሮፕላን የሚጥለውን ወረቀት ያነሣል። ምን እንደሚል ለማወቅ ሔጄ ላምጣ። የጠላት ሰላይ አውሮፕላን የጣለውን ወረቀት አገኘሁ። አንብበውና የሚለውን እንወቅ።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ የጠላትን አሳቡን ማወቅ ይጠቅማል፤ ነገሩን መቀበልና ማመን ስሕተት ነው። የበተነው ወረቀት የኢትዮጵያ ወታደር እስከ አንድ ወር አገርህ ግባ አልነካህም የሚል ነው። ቀበሮ በአፉ ሥጋ የያዘውን አሞራ ቃለ መልካም ነህና ቃልህን አሰማኝ ማለቷ አፉን ሲከፍት ለሚጥለው እንጂ ለቃሉ ማማር ጉምጅታ አይደለም። ጠላትም እስከ አንድ ወር አገርህ ግባ አልነካህም ያለው ከመርዝ ጢስና ከቦምብ የተረፈው የጦር ወታደር ከተጠለለበት ወጥቶ ሜዳ ሲገባ በአውሮፕላን ሆኖ በቦምብና በመትረየስ ለመፍጀት የተመቸ ቦታ እንዲያገኝ ነው። ይህ

ያለንበት የአገራችን አይደለምን? እውነት ከሆነ ከአገራችን ሊያሳድደን የመጣው ጠላት ወደ አገሩ አይመለስምን?

ካሣዬ፤ ባለመጠንቀቅ የሚመጣ ጉዳት ባለማወቅ ከሚመጣው ጉዳት የበለጠ ነው። ጠላት የበተነውን የማታለያ ቃል ተከትሎ ነጭ ለባሽ ወታደር ጉዞውን ስለ ቀጠለ መንገዱንና ሜዳውን መላው፤ የጠላት ሰላይ አውሮፕላንም ሁኔታውን ዝቅ ብሎ ይመለከታል። የሠራዊቱ ብዛት ደምቆ ስለታየው አውሮፕላኑ ተመለሰ። ከባድ ቦምብ ጣይ አውሮፕላንና መትረየስ ተኳሽ አውሮፕላኖች መጥተው ከመርዝ ጢስና ከቦምብ የተረፈውን ይጨርሱታል ብዬ ሰጋሁ።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ አቤቱ ፈጣሪያችን ረድኤትና ድኅነት የሚገኝ ካንተ ዘንድ ነው። ጌትነትህን የተማፀኑ ሁሉ ይድናሉ። ዳዊትን ከክፉ ጦር ዳንኤልን ከአንበሳ አፍ እንዳዳንካቸው ንጹሑን የኢትዮጵያውያንን ደም ለማፍሰስ ከሚከታተለን ጠላት አድነን። በመከራ የተቀጠቀጡትን አድን በስደት የተበተኑትን ሰብስብ፤ መንገድ ከሚሄዱትም ጋር በረድኤት ሒድ፤ በመከራ የተጨነቁትን ኢትዮጵውያንን አድን በጽኑ ሥቃይና መከራ ላይ ያሉትንም አስብ።

ካሣዬ፤ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እንደነገርኩህ ከባድ ቦምብ ጣይና መትረየስ ተኳሽ አውሮፕላኖች ሰማዩን መልተው በሰልፍ መጡ። በጣም ወደታች ዝቅ ብለው ቦምብና ጥይቱን ከቦምብና ከመርዝ ጢስ ተርፎ በነበረው ወታደር ላይ ነዙት። የአርባ ዓመት ቂም ያልረሳ ጠላት ትናንት በማይጨው ጦር ሜዳ ስንት ወገኖቹ በኢትዮጵያ ጀግኖች እንደ ቅጠል ረግፈው፤ አልነካችሁም እስከ አንድ ወር አገራችሁ ግቡ ብሎ የዘራውን የማይጨበጥ የውሸት ወሬ አምኖ ለቦምብ ጣይ አውሮፕላን ከማይመች ለጊዜው መከላከያ ከሆነው ሠዋራ ቦታ ወጥቶ በጠራ ሜዳ ላይ መጨፍጨፍ የሚያሳዝን ነው።

የሰውን አእምሮ የሚያውቅ፤ ልብ ያሰበውን፤ ኩላሊት ያመላለሰውን የሚመረምር ከሐሊ አምላክ በአንቃዕድዎ ሆነህ ስለጠቅላላው ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያ ያደረግኸውን ጸሎት ሰምቶ ከሰማይ የሚወርደውን ቦምብ እንደ ኳስ እያንከባለለ መዓቱን በምሕረት እንዲለውጠው ከመለመን በቀር በጠራ ሜዳ ላይ የሚጓዝ ሠራዊት መጠጊያና መጠለያ የለውም። የቀኑ ሰዓት አልቆ ተራው ወደ ሌሊቱ ሰለ ተዛወረ ከማታው አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ሆንዋል። አውሮፕላኖቹም ተመልሰዋል። ጓዛችንን እንጫንና ጉዞአችንን እንቀጥል።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> የቦምቡ ነጐድጓድ ራስ ምታት ጥሎብኝ ሔደ። ሜዳው በቦንብ ሲታረስ ውሏል። በበቅሎ ተቀምጦ ለመሔድ ይቸግር ይሆናል። ቀን ከኛ ጋር የዋለ አምላክ ሌሊትም በመካከላችን አለ። ስለዚህ እየተነጋገርን ጉዞአችንን እንቀጥል።

<u>ካሣዬ፤</u> የቦምብ ነጐድጓድ፤ የመትረየሱ መስካካት ሲገመት በሜዳው ላይ የነበረው ሠራዊት አንድም ሊተርፍ አይችልም። መሬቱ በቦምብ መታረሱ ብቻ ሲታይ በውሥጡ ምንም ያህል የሰው ሬሳ አይታይም። የጠላት ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በሰልፍ ሆነው ቦምብ ለመጣል ሲያንዣብቡ ያቀረብካት የሕሊና ጸሎት እግዚአብሔር ዘንድ ደርሳ ቦንቡን በነጐድጓድ ብቻ አሳልፎታል። ከልብ የሚፈላ ኃዘንና ጸሎት ታላቅ ኃይል አለው። ነቢዩ «ነፍሴን ከተሰለፍብኝ በሰላም አድናት» እንዳለው በመርዝ ጢስ የተንገላታው ጦር ከወረደበት የቦምብ ነጐድጓድ ድኗል።

አሁን ኮረምን አልፈን አህዮ ልንደርስ ነው። ሌሊቱም ሊነጋ እኩል ሰዓት ቀረ። አህዮ ስንደርስ ሌሊቱ ተራውን ለቀኑ ይለቃል። የጦር ሠራዊቱም አህዮ ሠፍሮ ቀኑን ያሳልፋል።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ንግግርህ ከምግብ ይበልጥ ስለጣመኝ ሳልመልስልህ የሌሊቱን ጉዞአችንን ፈጽመን ሌሊትና ቀን ተለዋወጡ። የጦር ሠራዊቱ አህዮ ይሠፍራል። የጠላት ሰላይ አውሮፕላንም

እንደትናንትናው ሐሰት የተመላ ወሬ የያዘ የማታለያ ወረቀት ይበትን ይሆናል። አሁንም የሚታለል ይኖር ይሆን? ነቢዩ «በአንተ እመንሁ ነፍሴን አትጣል ከሚያጠምዱኝ ወጥመድ ጠብቀኝ። ከክፉ አድራጎችም አሽክላ፤ እኔ ብቻ እስካልፍ ድረስ» ብሎ እንደለመነው፤ ለሱ የተለመነ ለኛም ተለምኖ እንደሚያሳልፈነ ተስፋ አለን። የጦር ሠራዊቱ የሠፈር ስለሆነ ዕቃችንን እና ሳርፍ።

<u>ካሣዬ፤</u> የለመደውን የማታለል ተግባር ለመፈጸም የጠላት ሰላይ አውሮፕላን መጣ። የጦር ሠራዊቱ የሠፈረበትን አይቶ ተመለሰ እኩል ሰዓት ባልሞላው ጊዜ ከባድ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ብቅ አሉ። ደርሰው በላያችን ላይ አንዣበቡ ቦምቡን እንደ ዝናም አወረዱት። ተመልከት በቅሎአችንና አህያችን ግጦሽ ለመፈለግ ራቅ ብለዋል። ቦምቡን እንደ ዝናም በብዛት አወረደው። በበቅሎአችንና በአኅያችን አደጋ የደረሰ መሰለኝ። ሥጋሁ ሐጂ ልይ፤ በቅሎዋና አህያችን ከብዙ የጋማ ከብቶች ጋር በቦምብ ተመትተው ወድቀዋል። አንተ ቁስለኛ ስለሆንክ እንደ ልብ ባለመራመድህ የበቅሎዋ መታጣት አሳዘነኝ። ከአሸንጌ እስከዚህ ያለች ግር መጣን። በግርህ የጦር ሠራዊቱን ልትከተል የምትችል አይመስለኝም።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> እስካሁን ከአንደበትህ የሚፈልቀው ንግግር ከአንተ የአእምሮ ችሎታ የወጣ ሳይሆን፤ እግዚአብሔር እያቀበለህ እንደምትናገር ግምት ወስጃለሁ። በአሁኑ አነጋገር ግን ስለ ተሳሳትህ የሰው እውቀት ከንቱ መሆኑን አሰብኩ። በበቅሎአችንና በአኅያችን አደጋ አዘንክ፤ ከነሱ ይልቅ ነፃነትን ያህል ጸጋ ተገፍፈን ስንንከራተት የበቅሎአችን ጥፋት ከዚህ የባሰ ነውን የበቅሎአችንንና የኅያችንን ጥፋት ዛሬ ሊያሰማኝ ከትናንት ጀምሮ ውስጥ እግሬ ከተረከዜ ላይ ብጉንጅ ስለያዘኝ በጦር ሜዳ ከቈሰልኩት ይልቅ ሥቃዩ የዚህ በርትቶብኛል። እስካሁንም ያልነገርኩህ አሳብ ላይ ትወድቃለህ ብየ ነው። ሆኖም፤ ካለፍነው የበለጠ መከራ አይገጥመንም።

# <u>ምዕራፍ ፺።</u>

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከአሸንጌ ከጦር ሠራዊቱ ጋር ሲጓዙ።

<u>ካሣዬ፤</u> የቀኑ ብርሃን ተራውን ለሌሊት ስለ አስረከበ የጦር ሠራዊቱ ጓዝ ማንሳት ጀምሮአል። ለጊዜው ይጠቅመናል የምንለውን መርጠን የቀረውን መተው አለብን። በዕቃ ሸክም በኩል የአንተን ርዳታ አልፈልግም የሚሰማህን ሥቃይ ታግሠህ ከጦር ሠራዊቱ ጋር መጓዝ ከቻልክ ትልቅ ዕድል ነው። የውሥጥ እግር ብጉንጅ እንደያዘህ እስካሁን ሳትነግረኝ ሥቃይህን በቈራጥነት ታግሠህ ችለኸዋልና በጉዞአችን ላይ እንደምንበረታ ተስፋ አለኝ።

<u>አምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> በበዛት የሚጓዘው የጦር ሠራዊት ጥቂት በጥቂት እያለ ራቀን፤ የተቻለኝን ያህል ጥርሴን ነክሼ ከጦር ሠራዊቱ ተቋርጠን እንዳንቀር ብርታትና ንቃት የሚሰጥ ቃል እየነገርኩህ የተቻለኝን ያህል ለመራመድ እሞክራለሁ።

ከቦምብ መከላከልና ከሌሊቱ ጉዞ ድነን በቀን ለመጓዝ ዕድል በማግኘታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው። ከጭንቅ ቦታ ወጥተን ከዚህ የደረስነው በኛ ኃይል ሳይሆን በአምላክ ቸርነት ነው። ፈሳሹን ውሀ ግራና ቀኝ እንደ ግድግዳ አቁሞ ሞገዱን አርግቶ እስራኤልን በባሕሩ መካከል በደረቁ ያሳለፈ አምላክ ከሰማይ ከሚወርድብን የመርዝ ጢስና የቦምብ ናዳ አድኖን ከዚህ ካደረሰን የወደፊቱንም ርሱ ያውቃል።

ኢትዮጵያ በጀግኖቿ ታፍራ ነፃነትዋን እስካለንበት ዘመን ድረስ ጠብቃለች፤ ነፃነትዋን ለመድፈር የመጣውን ጠላት ከአባቶች በወረሰው የጀግንነትና የቈራጥነት ሙያ የኢትዮጵያ የጦር ወታደር እስከ መጨረሻው ጠብታ ደሙን በማፍሰስ በጀግንነት ተከላክሎአል። በቈራጥነትና በጀግንነት ምንም ቢከላከል ጊዜው ከዳው።

<u>ካሣዬ፤</u> ከማር የሚጣፍጥ የወንድ ወኔ የሚቀሰቅስ ንግግር በማድረግህ በሰውነቴና በሰውነትህ ይታይ የነበረው የድካም ሰመመን ጠፋ። ረጅሙን ጉዞአችንን አቈራርጠን መቅደላ ደረስን። ብዙ ጊዜ የተለየኋቸውና የተለዩኝ ወይዘሮ እንዳናጣሽ የሚባሉ አክስት ነበሩኝ። በሰውነትህ ላይ ያለው ቊስል አመንምኖህ ተዳክመሀል። ከጦር ሠራዊቱ ጋር አብሮ ለመዝለቅ የምትችል አይመስለኝም። ከትውልድ አገራችን ከደረሰን ወደ ፊት የምናደርገውን ጊዜው ራሱ ያውቃል። የወዘሮ እንዳላጣሽ ቤት በአሳቤ ትዝ ስለሚለኝ አቅጣጫው በዚህ ነውና እንሒድ።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ከትውልድ አገራችን ብንደርስም ከጦር ጓደኞች ተለይቼ መቅረቴን እንደ ክዳት እቈጥረዋለሁ። የሰውነቴትን መመንመንና መዛል አንተም ባትገልጽልኝ በድካም ምክንያት ልቤ አንዳንድ ጊዜ ወደታች ይጐትተኛል። ከጦር ጓደኞቼ ጋር አብሬ እየተጓዝኩ ፍጻሜየን ልመልከት ስወድ ቃልህን ለማስተሐቀር ደስ ስለማይለኝ አሳብህን ተቀብያለሁና ወደ አክስትህ ቤት ጕራ እል።

# ምዕራፍ ፯።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በወይዘሮ እንዳላጣሽ ቤት።

ካሣዬ፤ ከወይዘሮ እንዳላጣሽ ቤት ደረስን። ርሳቸውም በቤታቸው ደጃፍ ቆመው እነሆ ይታያሉ። አክስቴ ወይዘሮ እንዳላጣሽ እኔ ካሣዬ ነኝ እንደምን ከረሙ።

ወይዘሮ እንዳላጣሽ፤ የማን ካሣዬ ነው በሕይወት ይኑር ይሙት አልሰማሁም። መልኩም ርሱን አይመስለኝም። እንደ ሣር የመነመነ ሌላ ሰውም አብሮት አለ። ለሁሉም ነገር ጠጋ ብዬ ልየው።

ካሣዬ፤ በጦር ሜዳ በመርዝ ጢስ ሰውነቴ ተቃጥሎ ፊቴ በመበለዙ ዘነጉኝ እንጂ ካሣዬ ነኝ። አብሮኝ ያለውም የጦር ወታደር የአምሳ አለቃ ማዕርግ ያለው ነው። ሰውነቱ እንደተፋቀ ኸማት መንምኖ የሚታየው በጦር ግምባር ጠላትን በመትረየስ ሲያርገበግበው ውሎ መትረየሱ ዱቄት ሆኖ ርሱም ቆስሎ በጀግንነት ሙያ ለአገሩ ግዳጁን የፈጸመ ጀግና ወታደር ነው። እኔም የሔድኩት በተለይ ርሱን ልረዳውና ላገለግለው ነው። እንዲሚያዩን በጣም ድካም የተሰማን ስለ ሆነ ማረፊያ ቢሰጡን እንወዳለን።

ወይዘሮ እንዳላጣሽ፤ ወይ ልጄ አሁንማ በአነጋገርህ ለየሁህ፤ ካሣዬ እስቲ ልሳምህ። ከትንሹ እልፍኝ አርፋችሁ፤ እግዜር ሰጠኝ እግራችሁን ይጠባችሁ በዛ ውለታሽም የምትበሉትና የምትጡት ታመጣለች።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ካሣዬ በላን ጠጣን ድካማችን ተቀነሰ ዘመድና መድኃኒት የተቸገሩለት እንደ ተባለው በችግራችንና በጭንቃችን ጊዜ አክስትህ መድኃኒት ሆኑን። ረጅም ጊዜ ያለን መስሎን ለአገራችን

ከማሰብ አንቦዝን የኔ ዘመዶች በቅርብ ተንታ ይገኛሉ። ሰው ሰጥተውን ወደኔ ዘመዶች ሔደን ትንሽ ቀን ካረፍን በኋላ ስለ አገራችን የምናደርገውን ብናስብ እወዳለሁ። ስለዚህ ወይዘሮ እንዳላጣሽን ፈቃድ ጠይቀን እንሒድ፤ በሳቸው ቤት ብዙ ቀን ቆየን። ለወገን ሊደረግ የሚገባውን የርኅራኄና የቸርነት ሥራ አደረጉልን።

<u>ካሣዬ፤</u> የደግ ሰው ልብ የርኅራኄ መብቀያ ነው። ችግረኛን በተቻለው የረዳ እግዚአብሔር በከሐሊነቱ ይረዳዋል። በርኅራኄ ስላደረጉልን ርዳታ አክስቴን ከልብ እናመሰግንዎታለን። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ትውልዱ ከዚህ አገር ስለሆነ ዘመዶቹ በቅርቡ ተንታ ይገኛሉ። እነሱን እንድንጠይቅ ከሰው ጋር እንዲልኩን ፈቃድዎ ይሁን።

<u>ወይዘሮ እንዳላጣሽ፤</u> የሰውነታችሁ ጉስቍልና ከፊታችሁ አልተወገደም። ጥቂት ጊዜ ብትቆዩ ክፉ አልነበረም። በድካም ላይ ድካማ አልጨምርባችሁም ብዬ ነው እንጂ ስለ ጦርነቱ ጥቂት ላነጋግራችሁ እወድ ነበር። እንደሰማነው የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ምንም የተቻለውን ያህል የጀግንነት ባሕርዩን በቆራጥነት ቢያሳይ፤ ጊዜው ስላረዳው ግንባሩ ታጥፎ ከናንተ በፊት ዘማች ተመልሷል። ከዓይን ጆሮን ማመን ስለ ማይቻል የዓይን ምስክሮች ስለሆናችሁ ሁኔታውን ብትገልጹልኝ።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ፀሐይ ያየውን ሰው ሳያየው አይቀርም እንደሚባለው የተደረገ ነገር መገለጡና መታወቁ አይቀርም። የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት በተፈጥሮ ባገኘውና ከአባቶች በወረሰው ጀግንነት በቆራጥነት በጦር ሜዳ መሥዋዕት ሆኗል። የጋዝ መርዝ ጢስ ከሰማይ እየተርከፈከፈበት የቦምብ ናዳ እየወረደበት ሁሉንም በትዕግሥት ተቀብሎ እስከ መጨረሻው ጠብታ ደሙን አፈሰሰ። ብዙ ጀግኖች ጠላታቸውን እያስቀደሙ ተቃቅፈው ወደቁ። ነገር ግን ድል ያለችው በእግዚአብሔር እጅ በመሆኗ ጊዜ ስላልረዳን የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ግንባሩ ታጠፈ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ጨርሶ እንዳልተጣላት የምናምንበት አንድ ነገር አለ። ከጦር ሠራዊቱ ጋር በጦር ሜዳ ተገኝቶ በጀግንነት ሲዋጋና ሲያዋጋ የዋለው ጀግናው ንጉሠ ነገሥቷ በሕይወት ተመልሰዋል። የንጉሠ ነገሥቷ ሕይወት ካለ ድሉን በድል በቅርብ ጊዜ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ እንደሚሰጣት አረጋግጥልዎታለሁ።

<u>ወይዘሮ እንዳላጣሽ፤</u> እባብ ቀጭን ነው ብሎ ራሱን አይረገጥም። ጉበዝም ቈራጥና ልበ ሙሉ ጀግና ከሆነ ተጠቅቶ አይቀርም። የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አባት ጀግናው ልዑል ራስ መኰንን በአድዋ ጦር ሜዳ ጠላትን ከፍ ባለ ጀግንነት አፈር እንዳስጋጡት ታሪክ ይነግረናል። የጀግና ልጅ የኢትዮጵያን ደም በድል አድራጊነት እንደሚመልሰው ማናቸውም ተርታ ሰው ያመነበት ነው።

የነፃነት ጸጋ የተገፈፈ ሰው፤ አገር፤ ወገን፤ ቤት፤ ርስት አለኝ ብሎ ሊናገርና ሊመካ አይገባውም። የምትጮህ ድመት አይጥ አትይዝም። የሚመካ ሰው ሥራ አይሠራም፤ እንደሚባለው አሳባችን ትምክህት ሳይሆን ወንድም ሴትም ቢሆን ተባብሮ ነፃነታችንን የደመሰሰውን ጠላት ለማጥፋት በምንችለው ነገር ሁሉ መታገል አለብን፤ የአገር ጉዳይ ቸል የሚገባ አይደለም። ሕይወታችን ያለው በነፃነታችን ነው። ነፃነት ከሌለ ሕይወትም የለም። የኢትዮጵያ ነፃነት ተመልሶ ንጉሠ ነገሥቷ በመንበረ መንግሥታቸው ተቀምጠው ይህን የመከራ ዘመን ለመነጋገር የምንበቃበት ጊዜ እንደመታ ሳንጠራጠር በምንለምነው እግዚአብሔር ተስፋ እናደርጋለን።

# ምዕራፍ ፰።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ከእግዜር ሰጠኝ ጋር ሲጓዙ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ ከእግዚአብሔር ሰጠኝ ጋር በበቅሎ ሆነው አምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ዘመዶች አገር ደረሱ። እህቱ ወይዘሮ ማቆያ ወንድማቸውን ለማወቅ ቸገራቸውና ጥቂት ደቂቃዎች ያህል አተኩረው ይመለከቱት ጀመር። ከካሣዬ ጋር ለመነጋገር ጥርሱን ፈልቀቅ ሲያደርግ ወይዘሮ ማቆያ ወንድማቸውን በአሳሳቁ ለይተው አንገቱ ላይ ተጠምጥመው የናፍቆት ስሜታቸውን ገለጡ።

በተለይ ማረፊያ ተቀብለው ከውጪ ለሚመጣ መንገደኛ ሊያደረግ የሚያስፈልገውን አቀባበል በትሕትናና በኃዘን ፈጸሙ። ጥቂት ቀን ያህል በዚያው እንደተቀመጡ ከደሴ የወይዘሮ ማቆያ ወንድም አቶ ማንተናግሮ ከነጓዙ ሸሽቶ መጣ።

ወይዘሮ ማቆያ በድንጋጤ ተቀብለው የመታበትን ምክንያት ቢጠይቁት፤ ደሴ በጠላት እንደተወረረች ነገራቸው። እኛ ባለማወቅ፤ ነው እሱ ባወቀው ኃጢአታችን ፈጣሪያችን ለጊዜው ሊቀጣን ነው እንጂ እስከ መጨረሻው አሳልፎ ሊሰጠን አይደለም እያሉ የስደተኞቹን ዕቃ ወደ ቤት አገቡ።

አቶ ማንተናግሮ ከአምሳ አለቃ በድሉና ከካሣዬ ጋር ተገናኝተው ጠላት በደሴ ከተማ መግባቱንና እንደገባም የዘማቹንና በከተማው ያለውንም ሕዝብ ቤት እየበረበረ አሰቃቂ ግፍ መፈጸሙን ገለጸላቸው። ንግግሩንም በመቀጠል የጠላትን አሳብ ያወቀ ከተማውን እየለቀቀ በባላገር ስለተቀመተ ለጊዜው ውርደት አላገኘውም። የተታለለው በቤቱ እንደ በግ እየታሠረ ዓይኑ እያየ ንብረቱንና ሚስቱን አስደፈረ። ይህን ሳያይ በጦር

ሜዳ ጠላቱን አስቀድሞ ሕይወቱን ያሳለፈ የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት ነው።

ሰው ቤቱን፤ ንብረቱን፤ ሚስቱን ከተቀማ በውነቱ አለሁ ይላልን? ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በተናገሩት ትንቢታዊ ቃል «ነፃነት የሌለው ሕዝብ በጠላት እጅ እንደ ከብት እየተነዳ ካገሩ የሚወሰድ፤ በገዛ ምድሩ ርስቱን በሌላ ሰው እጅ እያየ ጢሰኛ ሆኖ በውርደትና በመረረ ኃዘን የሚኖር፤ በከብቱና በንብረቱ በመቃብር መሬት እንኳን የማያዝንበት፤ ለዘሩ የሚተላለፍ ባርነት ወርሶ የሚኖር ሕዝብ ማለት ነው» ያሉት ሲፈጸም በዓይኔ በማየቴ ሕይወቴን ጠላሁት። ሞት ለሰው የተፈጥሮው ግዴታ ዕዳው ነው። በልዩ ልዩ ምክንያት በየጉድባው እንሞታለን። ይህን ውርደት ከማየት እንኳን ወንድና ሴትም ቢሆን ስለ ነፃነት ከጠላት ጋር ግንባር ለግንባር የጀግንነት ሥራ ሠርቶ ለማይሞት ታሪክ መልካም ስም ጥሎ ማለፍ ዕድል ነው።

«በሣል በጉንፋን የምትሞተውን ሞት ከሩቅ አገር እኛን ለማጥቃት ለመጣው ጠላታችን ባገርህና በርስትህ በቤትህ ላይ ሆነህ መመከት አቅቶህ ለአገርህ ለኢትዮጵያ ሞትን ብትነፍጋት፤ ደምህን ሳታፈስ ብትቀር በፈጣሪህ የምትወቀስበት በዘርህ የምትረገምበት ነውና የተለመደ የጀግንነት ልብህን ሳታበርድ ወደ ፊት የሚቈይህን ታሪክህን እያሰብክ ጠንክረህ ለመዋጋት ቈርጠህ ተነሣ» የተባለው የግርማዊነታቸው መሪ ቃል እንኳን ወንድንና ሴትን ከቤት አያውልም። በአገራችን ተራሮችና ሸንተረሮች እየተዘዋወርን ካልተከላከልን ሕይወት አለን ብሎ መቀመጥ የበለጠ ጸጸት ማትረፍ ነው።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ጠላት በደሴ ከተማ ከመግባቱ የፈጸመውን የግፍ ሥራ እያንገፈገፈህ እነርከን። ይህ የግፉና የመከራው ዋዜማ ነው። ንብረቱንና ቤቱን መቀማት ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያውያንን

ከኢትዮጵያ መሬት ፈጽሞ አጥፍቶ አገሪቱ በጠላት ነገድ እንድትሞላና የኢትዮጵያ ነፃነት ተደምስሶ እንዲቀር የጠላት አሳብ ነው።

ግርማዊነታቸው የተናገሩትን ቃል ትንቢታዊ ቃል መሠረት አድርገህ የጠላትን የአረመኔነትና የግፍ ሥራ ስትነግረን አንድ ነገር ትዝ አለኝ። የክብር ዘበኛ ባልደረባ ወታደር የጀግንነት ግዳጁን ፈጽሞ ሁለት ታፋው በመትረየስ ደቆ፤ ነፍስና ሥጋው ሊለያዩ ሲጣጣር አገኘሁት። ጠጋ ብየ ሳነጋግረው አሁን አንተ የተናገርከውን የግርማዊነታቸውን ንግግር ዘርዝሮ፤ ሰው በአገሩ የመቃብር መሬት ከተነፈገ ንብረቱን ከተቀማና እንደሚታረድ ሠንጋ ከተነዳ የሕይወት ኑሮ አለኝ ሊል ይችል ይሆን?» ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል» እንደሚባለው የነጻነት ጸጋን የተገፈፈ ሰው ኑሮው በምድር ካሉት ፍጥረቶች በታች በጉድጓድ ውሥጥ እንደ ተጣለ ጉድፍ ነው። ከዚህ ዓለም የኑሮ መጽሐፍ ልፋቅ፤ ነፍስና ሥጋዬ በትግል ላይ መኖራቸውን ምንም ባውቅ ነፃእንት የሌለው ሕዝብ እንደ እብድ ውሻ የሚቅበዘበዝ፤ ሳይጠጣ የሰከረ ነው። ሰው የሚከበርበትንና የሚታፈርበትን ነፃነት ተነጥቆ በሕይወት እኖራለሁ ማለት ጊዜ የሚያመጣውንና ጊዜ ጊዜ የሚመልሰውን ለመመርመር አእምሮ የሌላቸው የደካማዎች መንፈስና አስተያየት ነው ብሎ አሳቡን ገልጾልኝ ተለያየን።

ወላጅ አባቴ የሚናገሩት በተሁለደሬ አውራጃ ከደሴ ከተማ ከሠላሳ ኪሎ ሜትር በማይቀር በአንድ ቀበሌ ነው። አባቴ በሕይወት መኖራቸውን ለማወቅ ከካሣዬ ጋር እሔዳለሁ። አንተ ከነገርከኝ የበለጠ መፈጠርን የሚያስጠላ፤ የጠላትን የግፍ አፈጻጸም እንሰማ ወይም እናይ ይሆናል። ጠላት በደሴ ከተማ ስለ ገባ የከተማው ሕዝብ እየተሰደደ ወደ ባላገር መጣ። እናንተ ለጠላት ወጥመድ ለመመቸት ወደ ደሴ ልትሔዱ ነው። ብትቆዩ በወደድኩ ነበር። እናትና አባታችሁን ከናፈቃችሁ ከተማ ሳትገቡ በባላገር አድርጋችሁ በቀጥታ እንትድሔዱ አደራ፤ ብለው ወይዘሮ ማቆያ አሰናበትዋቸው።

# ምዕራፍ ፱።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ደሴ አቅራቢያ ሲደርሱ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። በሁለተኛው ቀን በደሴ አቅራቢያ ስለ ደረሱ ስለ ከተማው ንግግር ጀመሩ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ካሣየ ካሁን ቀድም ደሴን ታውቀዋለህን? አዎን አውቀዋለሁ። ከአሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ በአቅጣጫው ሆነን የምናየው የደሴ ከተማ ነው። የጠላትን የግፍ አፈጻጸም በወሬው ጠግበነዋል። ነገር ግን ከተማ ገብተን ሁለንተናውን ቀስ ብለን ብንመለከተው ጊዜ የሚያመጣው አይታወቅምና ለታሪክ ምስክር ለመሆን ይጠቅመናል።

ካሣዬ፤ ጠላት የሚፈጽመውን የግፍና የጭካኔ ሥራ በወሬ ከመስማት በዓይን ማየት እውነት ነው ይጠቅማል። ነገር ግን የተለበለበ ግንድ የመሰለ ፊታችንን ጠላት ሲያይ ከጦር ሜዳ እንደተመለሰ ያውቃል። አንዳች የጀግንነት ሥራ ሳንሠራ ተይዘን እንደ በግ የታረድን እንደሆነ ለወገን ጸጸት እናተፋለን። ይሁን እንጂ እንደማንታወቅ ሆነን ለመግባት የምንችልበትን መንገድ እናስብ። ወደ መንደር ጐራ ብለን በአገሬው የሚሠራ ሻሽ ዓይነት ጨርቅ እንግዛና ጠምጥመን ከተማ ለመግባት እንችላለን።

# <u>ምዕራፍ ፲፡፡</u>

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ደሴ ከተማ እንደገቡ።

የአምሳ አለቃ ተረፈና ካሣዬ እስከ ጀሮአቸው ጠምጥመው ደሴ ከተማ ገቡ። እየተዘዋወሩ ከተማውን ሁሉ አዩ። ሮቢት በሚሉት ሠፈር የጠላት ወታደር እንደ ጉንዳን ፈሶበት አዩ። ጥቂት ኢትዮጵያውያን በከተማዋ ውር ውር ሲሉ፤ ከተማዋ በጠላት ወገን ተመልታለች። በከተማዋ የሚታዩ ኢትዮጵያውያን ጺጋቸው የተገፈፈ ሆኖ መገላመጥ ያበዙ ነበር። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ሁሉንም ነገር ከተመለከቱ በኋላ፤ ጉዞአቸውን ወደ አምሳ አለቃ አባት ቤት ሲቀጥሉ ያዩትን ሁሉ መገላመጥ ጀመሩ።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> የጠላትን አኳኋን በማየቴ ደስ ብሎኝ እግዚአብሔርን አመሰገንኩ። እንኳን የሰው የከተማዋ ጺጋ ተገፎ፤ በብዛት የሚቆጠር ጠላት በከተማዋ ሲኖር አንድም ሰው ያለባት አልመሰለም።

የኢትዮጵያ መሬት ጠላትን እንዳልተቀበለችው በዚህ ልንረዳው እንችላለን።

<u>ካሣዬ፤</u> በአሳቤ ውስጥ ያለውን ተናገርከው፤ የኢትዮጵያ መሬት ጠላትን እንዳልተቀበለች የታወቀ ነው። ነፃነት የሌለው ሕዝብ፤ ጠባቂ እንደሌለው መንጋ ነው። በሮቢት የሠፈረውን የጠላት ጦር ስንመለከት አንድ የጠላት ወታደር አንዱን ኢትዮጵያዊ በርግጫ ሲረግጠው አየሁ። ኢትዮጵያዊው ርግጫውን ተቀብሎ እንባውን አፈሰሰ። እንባ ታላቅ መሥዋዕት ነው። ከሰውነታችን ሲወጣ የውኃ መልክ ቢኖረውም ከመላ አካላችን የሚከፈል ደም ስለ ሆነ የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዕንባ ተጠራቅሞ ስለ ኢትዮጵያ ግፍና በደል አቤቱታ ማቅረቡ አይቀርም።

አይሁድ ፋሲካቸውን ባደረጉበት ቀን ጌታችንን በቅንዓት አሳልፈው በሰጡት ጊዜ የተቀበለውን መከራ እያሰብን ከሕሊና ሥጋ የተነሣ በሕሊና መንፈስ የምንሻውን ሁሉ ይፈጽምልናል። ስለዚህ እንደ ጉንዳን የሚርመሰመሰው የጠላት ጦር እንደ ወጣ በንኖ የሚቀርበት ጊዜ አለ።

# ምዕራፍ ፲፩።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከካሣዬ ጋር በአባቱ ቤት ሲደርስ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ከካሣዬ ጋር አባቱ ቤት ደረሰ። አባቱ ባዩት ጊዜ እግዚአብሔርን አመስግነው በናፍቆት ተቀበሉት። መላው ቤተ ሰብ ሁሉ ደስታቸውን ሲገልጹላቸው የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በፊታቸው ደስታ አልታይም አለ። ከጦር ሜዳ በደህና በመመለሳችሁ ደስ ብሎን ሁላችንም ደስታችንን ስንገልጽላችሁ በፊታችሁ የደስታ መልክ ባለማየታችን ቅር አለን ብለው የአምሳ አለቃ አባት ተናገሩ።

የአምሳ አለቃ በዕድሉ ተረፈ፤ ከጦር ሜዳ በደህና መመለሳችንን ምክንያት አድርጋችሁ በደስታ ስለ ተቀበላችሁን እናመሰግናለን ስለኛ ደስ ሲላችሁ በፊታችን ላይ ደስታ ባለመታየቱ ቅር እንዳላችሁ የተወደዱ አባቴ ገለጹልን። ደስታችሁና ደስታችን ፍጹም ሊሆን ይችል የነበረው መመለሳችን በድል አድራጊነት ቢሆን ነበር። ሕይወታችንን የምንወደውና ደስ ሊለን የሚችል እኛ ቀርቶ እናንተም ጭምር ስለ ነፃነታችን ከሕይወት መዝገብ ተፍቀን አገራችን ኢትዮጵያ በነፃነት ታፍራ አሁን ከደረሰባት ሞት ብትድን ነበር። አገር ሲኖር መኖር፤ አገር ሲሞት መሞት ተገቢ ነው። እኔ ከካሣዬ ጋር ስለ መጣሁ ደስ አላችሁ። የነፃነት ጸጋ ከላያችን ላይ ተገፎአል። እረኛችንንና ጠባቂአችንን አጥተን እንደ ከብት መንጋ ጠላት

ወደ ፈለገው ነድቶ ሊያርደን ይችላል። የኛ የኑሮ ፍጻሜ ይህ ከሆነ ደስታ አለን?

ውድ ልጄ ሆይ፤ ምንም ከአብራክ ሥጋዬ የተከፈልክ ብትሆን በአእምሮ አስተዋይነት በልጠኸኝ፤ አሁን የተናገርከው እስከ መቃብር አይረሳኝም። እውነት ነው የኛ ደስታ፤ መሠረት እንደሌለው በድቡሽት ላይ እንደተሠራ ቤት ነው። የመታመን ዋጋው የሕይወት አክሊል ነው። ወታደራዊ ግዳጅህ የሚጠይቀውን የታማኝነት ተግባርህን እንዳልረሳህ ተረዳሁ። የመንፈስ ጽናት ያጐናጸፈህ አምላክ ይጠብቅህ።

# ምዕራፍ ፲፪።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል ወሬ እንደተጠሙ።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> በአባቱ ቤት ከካሣዬ ጋር ሁለት ወር ያህል ከተቀመጠ በኋላ ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ሁኔታ አንዳች ወሬ ለመስማት ባለመቻሉ ከካሣዬ ጋር ወደ ሸዋ ግዛት ለመምጣት አሰበ።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> እዚህ ከተቀመጥን ሁለት ወር አለፈን። ስለ አገራችን ጉዳይ ምንም ወሬ አጣን። ወደ ሸዋ ብንሔድ ተስፋ ያለው ወሬ እንሰማለን። ጠላት መንገዱና ቤቱን እያስፋፋ ይሠራል። ከዋሻ ከማሻሻል ሥፍራ ተቀምጠን አንዳች ነገር አንሰማም። ሕይወት በጊዜ ርዝመት አይቈጠርም። የሚገመተው በተሠራበት ብዛት ነው።

<u>ካሣዬ፤</u> ወደ ሸዋ ብንሄድ በውነቱ ደስ ይለኛል። ደግሞ የሚጠቅምና የመንፈስ ኃይል የሚሰጥ ጠቃሚ ወሬ እንሰማለን። ነገር ግን አባትህ በዕድሜያቸው ገፍተዋል። ስለ ኢትዮጵያ ነፃነትና ስለ ንጉሠ ነገሥቷ

ተጋድሎ ጧት ማታ የሚሰማቸውን መራራ ኃዘንና የሚያፈሱትን ዕንባ ታያለህ።

በዚህ ላይ አንተ የተለየህቸው እንደሆነ ኃዘናቸው የበረከተ ይሆናል። እኛንም አይቀናንም። ለመሔድ ብንሞክርስ ያለይለፍ ወረቀት መተላለፍ እንችል ይመስልሀልን? ከፊቃዳቸው ወጥተን ስንሔድ ካራ ቆሬ ላይ የተያዝን እንደሆነ ለአባትህ የምትጨምርላቸውን ከባድ ኀዘን አስብ።

በነገሩ ርግጠኛ ባለመሆኔ ልነግርህ አልፈለገግሁም እንጂ ከሸዋ አንድ ሰው መጥቶ ከወይዘሮ የምሥራች ቤት ሰንብቶ ሔደ። ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ለወይዘሮ የምሥራች አንዳንድ ነገር ሳይገልጥላቸው አይቀርምና እጠይቃለሁ።

<u>የምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> በአሳቤ ውሥጥ የሚመላለሰውን የአገሬን ጉዳይ በአባቴ በመለወጥህ አዘንኩ፤ ከዘመቻ የኛ ሕይወት በሰላም በመመለሱ አባቴና ቤተ ሰቦቼ የገለጹልንን ደስታ አስብ።

ደስታቸው መሠረት ያልያዘ ደስታ መሆኑ ገልጨላቸው፤ ውድ አባቴ እስከ መቃብር እንደማይረሱት ነግረውኛል። ትጉሕ ሰው ሲሔድም ሲመለስም እንደ መጋዝ ሥራ አይፈታም። ለጊዜው ያለንበትን ሁኔታ ብቻ ተመልክተን ሥራ መፍታት አይገባንም።

አባቴን ጥያቸው ብሔድ እንደሚያዝኑብኝ አውቃለሁ። አባትንና እናትን እንድናከብር ታዘናል። አባትንና እናትን ማክበር ዕድሜ ያረዝማል። እንዲያውም ለአባት ማገልገልና መገዛት የሚያስጠቅም ነገር ነው። የአባት በረከት እንዲያድርብን፤ ቢኖረን ሰጥተን ባይኖረን በጎ ነገር ተናገረን አባትን ማክበር አለብን። የአባት ምርቃት የልጆች ቤት ያጸናል። የናትም መርገም ሥር መሠረቱን ያጠፋል። የአባቱንና እናቱን የማይረዳና የሚያሳዝን ሑሩ እምኔየ ወዲያ ሒዱ የሚል የእግዚአብሔር አዋጅ ይፈጸምበታል። ይህንን ሁሉ ሳውቅ አባቴን አሳዝኜ ከመሔድ የአንተን ምክር እቀበላለሁ።

ካሣዬ፤ የአባትንና የእናትን ፈቃድ መጣስ ነፍስንና ሥጋን አጣምሮ እንደሚጐዳ ከኔ የበለጠ ስታውቅ አስቀድመህ የጠየቅኸኝ ለፈተና መሰለኝ። ለአንተ ድንገተኛ ወዳጅ አይደለሁም። ብዙ ጊዜ ከአንተ ጋር የመከራህ ተካፋይ ሆኜ የኖርኩ ልባዊ ወዳጅህና ረዳትህ ነኝ፤ የሆነ ሆኖ ሰው ሊያደርገው የሚገባውን ማመዛዘን ስለ አለበት ነገሩን አመዛዝነህ አሳቤን በመቀበልህ ደስ አለኝ።

በተነጋገርነው መሠረት ከወይዘሮ የምሥራች ቤት ሔጄ ከሸዋ የመጣው ሰው ስለ አገራችን ጉዳይ ምን ዓይነት ቸር ወሬ እንደሚሰማቸው በጠይቃቸው ሰውነትን የሚያለመልም ወሬ ስለ ነገሩኝ መንፈሴ በደስታ ረክቷል።

በአለፈው ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ጀኔብ ላይ ለተሰበሰበው የዓለም መንግሥታት ጉባዔ የኢትዮጵያን ጉዳይ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቀረቡ። ከተናገሩአቸው ታሪካዊ ቃሎች የቀዳኋቸው «አውሮፓም ይህን ነገር እንዳለቀ አድርጎ ቢቈጥረው በራሱ የሚደርስበን የሚጠብቀውን ዕድል ማሰብ ይገባዋል፤ እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ»

«እዚህ የተሰበሰባችሁ የዓለም እንደራሴዎች ሆይ፤ አንድ ንጉሠ ነገሥት በደረሰበት ኀዘን ማድረግ የሚገባውን ሥራ ለመፈጸም ጄኔብ ወደናንተ መጥታችሁ። ለሕዝቤ ምን ምላሽ ልውሰድለት።

ይህ የምሥራች ቃል በሸዋና በሌሎችም አገሮች እንደ ተሰማ ከዘመቻ የተመለሰውና ወደ ዘመቻም ሳይሔድ የአገሩን ጸጥታ ይጠበቅ የነበረው አብዛኛው ጀግና የኢትዮጵያን ተራራዎችና ጅረቶች መከላከያ አድርጎ በአርበኝነት ጦርነቱን ለመቀጠል ተሠማራ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ቸር ወሬ እንዳሰማኸኝ ወደፊትም ቸር ወሬ ያሰማህ። የደከሙ አባቴን ጥዬ ልሔድ ያልኩት ይህን የመሰለ የተስፋ

ምግብ አጥቼ በጠላት ዲናሚት ጩኸት ጆሮዬ ስለገዛ ነው እንጂ የአባቴን ሁኔታ ሳላውቅ መሔድ መቼ ደስ ብሎኝ ነው።

ወይዘሮ የምሥራች ስማቸውን በግብር አውለው ይህን የሰውነት ፈውስ የሆነ ወሬ ስላሰሙን ከልብ ዛሬ አመሰግናቸዋለሁ።

የኢትዮጵያ ጉዳይ በዓለም መንግሥታት ጉባዔ ፊት ከቀረበ የኢትዮጵያ ጀግኖች ከፍ ባለ ቈራጥነት ጠላትን እንደሚያሳድዱ የታወቀ ነው። ከመሥዋዕት ይልቅ ፍርድን ማስተካከል ይበልጣል። ግርማዊነታቸው በዓለም መንግሥታት ጉባዔ የተናገሩት፤ ትንቢት የያዘ ኃይል ቃል ዓለምን ስለሚያሰጋው፤ ስለ እውነት ፍርድ መሥዋዕት ሆኖ ስሙን ለታሪክና ለትውልድ መትከል ይገባዋል።

ግርማዊነታቸው የሚናገሩት ትንቢታዊ ቃል በዘመናችን እየተፈጸመ ዓይተናል ትንቢቱ በያንዳንዱ ላይ ደርሶ የዓለምን የመጀመሪያውን የታሪክ ገጽ ነገ እንደሚይዝ አይጠረጠርም።

# ምዕራፍ ፲፫።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ከወይዘሮ የምሥራች በሰሙት ወሬ እንደተጠቀሙ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ከወይዘሮ የምሥራች በሰሙት አጥንትን በሚያለመልም ወሬ አገግመው ከረሙ። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ አባት በቤተ ክርስቲያን በተለይ የጸሎት ቤታቸው ሱባዔ ስለሚገቡ፤ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ በአቅራቢያቸው ሆኖ ሊረዳቸው ከካሣዬ ጋር ለጥቂት ጊዜ ተለያዩ።

ፈውስ የሆነ መልካም ወሬ ካሁን ቀደም ካሣየ ያገኘው ከወይዘሮ የምሥራች ስለሆነ ከዕለታት አንድ ቀን ሊጠይቃቸው ሔደ።

ወይዘሮ የምሥራች፤ አሁን ትዝ ብለኸኝ መቼ ይመጣ ይሆን? እያልኩ አስታውሼህ ነበር። ትዝታህ ከፊቴ ሳይጠፋ ከተፍ በማለትህ ገረመኝ። የፈለግሁህም ከአዲስ አበባ ሰው መጥቶ የሚያስገርም ወሬ ነግሮኝ ነው።

የወሎ ግዛት ጳጳስ የነበሩት አቡነ ጴጥሮስ ለጠላት መሣሪያ አልሆንም ብለው ሐምሌ ፳፪ ቀን በሰማዕትነት በጠላት ተደበደቡ አሉ። ከአንድ ወር በፊት ያሰማሁህ ወሬ ለአጥንቶች ልምላሜ የሚሰጥ ነበር፤ አሁን ያሰማሁህ ግን ከሬት የመረረ ነው።

ካሣዬ፤ ጀግንነትና ቈራጥነት አስተባብረው የያዙት እውነተኛው ሐዋርያ አቡነ ጴጥሮስ ለጠላት መሣሪያ። እንደማይሆኑ የታወቀ ነው። በሐዋርያነታቸው የወረሱት ስም ጴጥሮስ ሲሆን ታላቁ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን የጠላት ወገን ኔሮን ቊልቊል አስቅሎት የለምን

ያን ጊዜ በሮም መከራው የበዛ ቅዱስ ጴጥሮስ፤ ዛሬ ክብሩ የበዛ ሆኗል። እንደዚሁም አቡነ ጴጥሮስ፤ በጠላት ቢደበደቡ፤ ስማቸውና ጀግንነታቸው በታሪክ ለትውልድ ሲተላለፍ ይኖራል።

ይልቁንም በእግዚአብሔር ኃይልና በንጉሠ ነገሥትዋ ድል አድራጊነት ኢትዮጵያ የድል አክሊል በምትቀዳጅበት ጊዜ የአቡነ ጴጥሮስ የውነተኛ የሐዋርያትና የጀግንነት ሥራቸውን ሲያወሳ የሚኖር መታሰቢያ ደማቸው በፈሰሰበት በዚያች ሥፍራ ተቋቁሞ ለትውልድ ምስክርና ኲራት ሆኖ ይኖራል።

ስትታመም ተፈወስ ወይም ሳትሞት ተነሣ የምንድንበት መንገድ እግዚአብሔር በወሰነው እንጂ እኛ ባልነው አይደለም።

በዚህ ዓለም ሰው ሲኖር ትርፉ መልካም ሥራ ሠርቶ ስሙን ለታሪክና ለትውልድ አስተላልፎ ሲወሳ መኖር ነው።

ይህ ካልሆነ በዚህ ዓለም የሰው መኖር ከእንስሳት መኖር ልዩነት የለውም።

በመትረየስ ከመደብደባቸው በፊት ለጥቂት ደቂቃዎች እንዲናገሩ ተፈቅዶላቸው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጠላት እንዳይገዛ የኢትዮጵያም መሬት ጠላትን እንዳትቀበል ገዝተው ማለፋቸውን ለሰማ አንድ ነገር አስታወስኩ። ከአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ጋር ከተንታ ስንመጣ የጠላትን ሁኔታ ለማወቅ ደሴ ከተማ ጐራ ብለን ነበር። ከከተማው ወጥተን መንገድ ስንጀምር ጠላት በብዛት ሲግበሰበስ ከተማዋ የተወረረች ትመስላለች እንጂ ሰው ያለባት ባለመምሰልዋ ኢትዮጵያ መሬት ጠላትን እንዳልተቀበለች በዚያውኑ ጊዜ ተነጋገርን።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ከአባቱ ሱባዔውን ጨርሶ ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ከካሣዬ ጋር እንደተገናኙ ወደ ወይዘሮ የምሥራች ቤት መሔዱንና ምንስ አዲስ ነገር እንደሰማ በፍጥነት ጠየቀው።

የአቡነ ጴጥሮስን መደብደብ ካሣዬ ዘርዝሮ በነገረው፤ ጊዜ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ አቡነ ጴጥሮስ የወሎ ግዛት ጳጳስ በነበሩ ጊዜ የዲቁና ማዕርግ የተቀበለው ከርሳቸው መሆኑን አስታውሶ አዘነ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ሰውን እግዚአብሔር ሲመርጠውና ሲያከብረው ነው እንጂ፤ ራሱን በራሱ ላክብር ቢል አይከብርም። ጊዜ ሥር የሌለው የማይጨበጥ ስለሆነ፤ ከጊዜ አንድ ነገር መንጠቅ ዕድል ነው። አቡነ ጴጥሮስ ቆራጥና ፍጹም ሐዋርያ መሆናቸውን በቅርብ ሆኜ አውቅ ነበር። እግዚአብሔርን የምታመሰግን ሰውነት በአእምሮ የሰፋችና በረድኤተ እግዚአብሔር የለመለመች ናት። ጻድቅ ሰው ከሞተ በኋላ በሰው ልቡና ጸጸትን ይተዋል። አቡነ ጴጥሮስ ግን አሟሟታቸው የሐዋርያነታቸውን ግዳጅ ፈጽመው ስለሆነ መታደል ነው እንጂ ሞት አይደለም።

ከተወደዱ አባቴ ጋር የሱባዔውን ጊዜ በደህና አልፈነዋል። ነገር ግን አባቴ የጠላትን ዓይን ሳታሳየኝ ጥራኝ፤ የኢትዮጵያን ጥፋት፤ የንጉሠ ነገሥቷን ተጋድሎ እያየህ ቸል ትላለህ። ቤተ መቅደስህና ቤተ ጸሎትህ

በርኩስ ጠላት አረመኔ እግር ተረገጠች። አንተን አምነውና በአንተ አምልኮት ጸንተው የተቀመጡ ሁሉ ተጋልጠው ተደበደቡ እያሉ፤ ጧት ማታ ልቅሶ ስለ አበዙ ለሕይወታቸው ሠጋሁ።

ስለ ኢትዮጵያና ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ማዘናቸውን ስወድ፤ ጣላትን በዓይኔ ሳላይ ጥራኝ ስለሚሉ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ቅርብ ነውና ይጠራቸው ይሆን?

ይልቁንም ያሠጋኝ ሱባዔውን ጨርሰን ስንወጣ ከጸሎት ቤታቸው ጠርተው መቃብሬ ከዚህ ስለሆነ ስሞት ከዚህ እንድትቀብሩኝ ብለው ነገሩኝ። ድንጋጤዬን በፊቴ ስላዩት አሁን አይደለም ምናልባት የሞትኩ እንደሆነ ብዬ ነው ብለው ንግግራቸውን ደገፍ አደረጉት።

ካሣዬ፤ ኃዘንና ዕንባ ለአገር ጠቃሚ ነው። ርሳቸውንም የሚጐዳቸው መስሎ ቢታይ ለኛ ይጠቅመናል። ዛሬ ቀኑን በጣም አምዋቸው ውሏል። መታመሜን የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ በአለማወቀ ከመኘታ ቤቴ መጥቶ ዛሬ አላየኝም ብለውኛልና ሒድና ጠይቃቸው።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ የጠሉን ይጠላሉ። የሚያሳድዱን ይሳደዳሉ። መንገዳቸውም ይዘጋባቸዋል። ሕይወታችንን ለማጥፋት የሚሹት ያፍራሉ፤ ይጐሳቈላሉ። ክፋትን በኛ ላይ ያስቡ ይወድቃሉ።

በነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ ይሆናሉ። የእግዚአብሔር መላክ ያስጨንቃቸዋል። መንገዳቸውም ዳጥና ጨለማ ይሆናል። እንዳንዳዱንም የእግዚአብሔር መላክ ያሳድዳቸዋል። በከንቱ ያጠፉን ዘንድ ወጥመድ ያጠመዱልን፤ ባላወቁት ወጥመድ ይወድቃሉ።

በባሕርያችን ደካማነት እንቸኩላለን እንጂ ይህንን ለማየት እንደምበቃ በማንጠራጠረው አምላክ ተስፋ አለን።

ሰውን ለማጥፋት የሚፋጠኑና የተፋጠኑ፤ በመጨረሻ ራሳቸው ይጠፋሉ።

# ምዕራፍ ፲፬።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከካሣዬ ጋር ወደ አባቱ መኾታ ቤት ሲሔድ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ከካሣዬ ጋር አባቱን ሊጠይቅ ወደ መኾታ ቤታቸው ሲሔድ ጠሪ ልጅ ወደ ርሱ ሲመጣ ከበሩ ላይ ተገናኙ። ጌቶችን በጣም ስለ አመማቸው በፍጥነት ይፈልጉሀል።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በቶሊ ቢደርሱ ቤተ ሰቡ ሁሉ ተሰብስቦ መላቀስ ጀምሮአል። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ አባባ መጣሁ አለ። ሌሎቹን ወንድሞችህንና ቤተሰቦቹን ሁሉ በጸጥታ አስቀምጣቸው አሉትና ትእዛዛቸውን ፈጸመ።

ውድ ባለቤቴና ልጆቼ ቤተሰቦቼ ሁሉ፤ ውሎ። ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት መቅረት እንደሌለ ታውቃላችሁ። ነፍሴን ከሥጋዬ የሚለይ መልአከ ሞት ማጅራቴን ይዞኛል። አንደበቴ ከመዘጋቱ በፊት እንደኔ እስከትሆኑ ድረስ ልትፈጽሙት የሚገባውን ልነግራችሁ ወደድኩ።

ፍቅረ እግዚአብሔርንና ፍቅረ ቢጽን በእጃችሁ እንደጣት ቀለበት፤ በፊታችሁ እንደመስትዋት አድርጋችሁ በየጊዜው ተጠንቅቃችሁ ልትጠብቋቸው እጅግ አስፈላጊዎቻችሁ ናቸው። እነዚህን መሣሪያ ካደረጋችሁ ሁሉንም ነገር አሸናፊ ትሆናላችሁ።

ልጄ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ በአገር ፍቅር የተቃጠልክ መሆንህን መርምሬ ደርሸበታለሁ። የጠላትን ዓይን ሳያሳየኝ እንዲጠራኝ የለመንኩት ፈጣሪዬ፤ ለመናዬን ሰምቶ እነሆ ዛሬ በሥጋ ብለያችሁ በመንፈስ ግን ምን ጊዜም ከመካከላችሁ ነኝ። የኔን አሳብና ልመና ያላስቀረ አምላክ ለአገር ነፃነት የሚቃጠለውን የአንተም የልብህን አይቶ የጠላትን ጥፋትን፤

የኢትዮጵያን ነፃነት በዓይንህ ያሳይህ። ከመጣህ በዚች በአጭርዋ ጊዜ ውስጥ ስለረዳኸኝ የእግዚአብሔር እረዳት መልአክ አይለይህ። ሌሎቹም ቤተ ሰቦቼና ልጆቼ እርስ በርሳችሁ በፍቅር ሰንሰለት ተሳስራችሁ እንድትኖሩ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ይሁኑ።

አገሬ ኢትዮጵያ ሞተሽ አይቼ ትንሣኤሽን ሳላይ ብለይሽም በመንፈስ ካንቺ ጋር ነዋሪ ነኝ። የእሥራኤል አምላክ በገናናው ንጉሥ ነገሥትሽ ላይ አድሮ በቅርብ ጊዜ በነፃነትሽ ደምቀሽና አሸብርቀሽ በዓለም ላይ እንድታጌጪ የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ለመሪሽ ድልን በእጁ አስጨብጦአል።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ አባት ከዚህ በላይ ያለውን ቃለ በረከት አስምተው እንደ ጨረሱ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች። ቤተ ሰቡ ሁሉ ዕንባ በዕንባ እየተራጨ ልቅሶው ደመቀ። በዚያን ጊዜ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ቤተ ሰቡን ሁሉ ተቆጥቶ ልቅሶውን ጸጥ አደረገ። ይህን ያህል የደመቀ ልቅሶ ማልቀስ ይገባን የነበረው አገራችን ስትሞት ነበር። ከአባታችን ኃዘን ይልቅ የአገራችን ኃዘን ያቃጥላል። ስለዚህ ልቅሶው በመጠኑ ሆኖ ከመሞታቸው በፊት ለኔ ባሳዩኝ በጸሎት ቤታቸው የቀብሩ ሥርዓት በቶሎ እንዲፈጸም ያስፈልጋል።

በአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ አሳብ ሁሉም በኅብረት ተመርቶ የመቃብሩ ሥነ ሥርዓት በጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ተፈጸመ።

በሦስተኛው ቀን የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከካሣዬ ጋር ሆኖ ሲናፈስ አባቴን ሳላሳዝን በሞት ተለዩኝ። እስካሁንም እግር ብረት የሆነኝ የአባቴ ፍቅር ነበር። እናቴን፤ ወንድሞቼና እህቶቼ ሊረዷት ይችላሉ። ከተንታ ስንመጣ ደሴ ከተማ ለመግባት ፈሊጥ የገለጠልህ አምላክ ይገለጥልህና ወደ ሸዋ መሬት ለመሔድ የምንችልበትን ዘዴ አጥና ብሎ ለካሣዬ ነገረው።

<u>ካሣዬ፤</u> በዚህ ነገር ካንተ ይበልጥ እኔ አስቤበታለሁ። በኃዘን ላይ ኃዘን አልጨምርብህም እንጂ ከታላቅ ወንድምህ ጋር ለጐሐይቅ ዓርብ እንድትገኝ ከካፒቴን ማሪዮ አንድ ሰው ወረቀት አምጥቶአል።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> አባቴ የጠላትን ዓይን አይለይም ብለው እንደቆረጡ መሞታቸውን የሰማ ነግሮት የአባቴን ሹመት፤ መሣሪያ ለሆነው ሊሰጥ ይሆናል። እንኳን የአባቴን ሹመት አገሬን ነፃነቴንና ንጉሠ ነገሥቴን አጥቻለሁ።

<u>ካሣዬ፤</u> በጥሪው መሠረት መሔድ ይገባሀል። የቀረህ እንደሆነ ለመላ ቤተ ሰቡ ሁሉ የሚተርፍ መዘዝ በአንተ ምክንያት ይመጣል።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ይህ እንዳይደርስብኝ ወደ ሸዋ ግዛት ለመሔድ አስቤ ምክንያት ቀረሁ። አባቴ ከሞቱ በኋላ እህል ውኃዬ አላልቅ ብሎ ጠላት የጥሪ ወረቀት ላከልኝ።

ጥሪውን ተቃውሜ ወደ ሸዋ ግዛት እንዳልሔድ የኔ ዘዘዝ ለመላ ቤተ ሰቡ ተርፎ በጠላት የተደበደቡ እንደሆነ የማይረሳ ጸጸት አተርፋለሁ፤ እንግዲህ ታላቅ ወንድሜን አስነስቼ ልሒድ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ታላቅ ወንድሙ ሐይቅ ደረሱ። ባላወቁትና ባልተገለጸላቸው ምክንያት ለጠላት መሣሪያ በሆኑ ርጎራጌ ፈጽሞ በሌላቸው እየተገፉና እየተደበደቡ እጃቸው ተቈራኝቶ በሽቦ በጥብቅ ታሠሩ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ የእሥራቱ ሥቃይ ካለፋቸው ሥቃዮች ሁሉ የመረረ ስለሆነበት በታላቅ ድምፅ ጮኸ። የቀኝ ክንዱን የተፈጥሮ መልኩ ለውጦና ፍጹም ደም ጐርሶ ሊፈነዳ ተቃረበ። በጩሆቱ ምክንያት የጠላት ወታደሮች ከእሥር ቤት ድረስ መጥተው ከፍ ባለ ሥቃይ በሚሰቃየው በአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ጩሆት እየተሳሳቁ «ቦኖ» ሲሉ

የወገናቸው ሥቃይ ያልተሰማቸው የጠላት መሣሪያዎች ከጠላት ጋር አብረው ይስቁ ጀመር።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ጨሆቱ ጸጥታ ስለነሳቸው ስለ ስቃዩ ሳይሆን ስለ ጩሆቱ እሥሩን ትንሽ አላሉለት። የታሰሩት ያለ አንድ ምክንያት ባላወቁት ነገር ስለ ነበረ፤ ከሦስተኛው ቀን ተፈትተው በሰው ደም በሰከረ በካፒቴን ማሪዮ ጽሕፈት ቤት ቀረቡ። በጠረጴዛው ላይ በብዕር ፋንታ ሽጉጥ ተቀምጦ ነበር።

ካፒቴን ማሪዮ፤ ሌሊት በቤታችሁ ቀን በጫካ እየዋላችሁ በመንግሥታችን ላይ የምታደርጉትን አዳም ተከታትዬ ደርሸበታለሁ። ከመካከላችሁ አንዱ በጦር ሜዳ የወጋን ነው። እንደናንተ በመንግሥታችን ላይ የሚያምፁት መቃብራቸውን ራሳቸው ቆፍረው በዚህች ሥፍራ የሚቀበሩበት ጊዜ ከፊቴ ተደቅኖ ይታየኛል።

አባታችሁ የጠላትን ዓይን አላይም እያለ መፎከሩ ስመቼ፤ ጊዜ ስፈልግለት ሞተ። የኛን መንግሥት ያላወቀና ለኛ መሣሪያ ያልሆነ የሹመት አገር ይዞ ሊኖርና ከሞተም በኋላ ለልጆቹ ሊተላለፍ አይችልም። ከልብ ሆነው በእውነት የሚያገልግሉ ሹመቱን ይጠቀሙበታል።

የአባታችሁ ይዞታ የነበረውን ለአለቃ ሡራልን ሰጥተነዋል። በአለፈው ጊዜ እንደምታደርጉት ወደ ፊት በመንግሥታችን ላይ የአድማና ይህን የመሰለ ሥራ የምትፈጽሙ መሆናችሁን የሰማሁባችሁ እንደሆነ ያለ ርኅራኄ (ትረሸናላሁ) ትገደላላችሁ።

አባታችሁ ራሱ ያሳርሰው የነበረውን የእጅ እራሽ ከሁለት ቤት ጋር ይዛችሁ ሹመቱንና የተረፈውን መተዳደሪያ ከሁለት ቤት ጋር ለአገልጋያችን ለአለቃ ሡራልን ተሰጥቶአል። ባለፈው ጥፋታችሁ የተቀጣሁት ቅጣት በቂ ሲሆን፤ ወደ ፊት ካላረፋችሁ ይህ ቅጣት ለጥፋታችሁ ዋዜማ ነው እንጂ የሚፈጸምባችሁን ቅጣት ወደፊት ታያላችሁ።

ሥቃዩ እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ሳይረሳው የሚኖር እስራቱንና ከካፒቴን ማሪዮ የወረደባቸውን የዛቻ ናዳ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ታላቅ ወንድሙ ተቀብለው ወደ ቤታቸው ከተመለሱ በኋላ፤ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ወደ ኋላ ያሳለፋቸውን አንዳንድ ነገሮች አስታወሰ።

በጀግንነት ያረፈው ቍስለኛው የክብር ዘበኛ ባልደረባ ወታደር ሥጋዊ አካሉ በሥቃይ ላይ ወድቆ ነፍሱ ከሥጋው ጋር ስትታገል፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተናገሩትን ትንቢታዊ ቃል ጠቅሶ ነፃነት የሌለው ሕዝብ በውርደትና በመረረ ኀዘን የሚኖር፤ በክብሩና በንብረቱ፤ በመቃብሩ መሬት እንኳን የሚያዝበት፤ እንደ ከብት እየተነዳ ካገሩ የሚወሰድ ስለሆነ፤ ወንድና ሴት በአጭር ታጥቀው ጠላትን መከላከል ያስፈልጋል አለኝ። የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል እንደተባለው ጀግናው ወታደር ይህን በተናገረኝ ጊዜ የጠላት አገዛዝ ከሚፈጸምባቸው አንዱ እኔ ዕድለ ቢሱ አይደለሁምን? ብዬ ሞት መነፈነን በኀዘን ብገልጥለት ከስሕተት ቈጠረብኝ እንጂ አልተቀበለኝም።

ጠላት የአገሬን መሬት አካፈለኝ፤ አባቴ ከልጅነት እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ የደከሙበትን ንብረታቸውን ላልደከመው ለጠላት መሣሪያ እንዳካፍል አስገደደኝ። የተፈጸመብንም ቅጣት የቅጣት ዋዜማ እንጂ ቅጣቱ ይህ ብቻ አለመሆኑ ተነገረን። በቈፈርነው ጉድጓድ እንደምንቀበር አረጋገጠልን። በነፃነት ኮርቶ የኖረ የአንድ አገር ሕዝብ ይህ ዓይነት ግፍ ሲፈጸምበት ምን ማድረግ ይገባው ይሆን? ሁሉን ቻይና አድራጊ አምላክ ኢትዮጵያውያንን አይረሳም። የደረሰብንንም መከራ ከመከራ አንቈጥረውም። እያሳደዱ እጃችንን አሳልፈው የሚሰጡ፤ መሠረት በሌለው በጠላት ስብከትና የማታለያ ገንዘብ የተሸነፉ ፍቅረ ንዋይ ያደረባቸው ናቸው። ጌታችንንም አሳልፎ የሰጠው ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ይሁዳ ነው። እኛንም አንዳንዳችንን እያሳለፉ የሚሰጡን በግብር የይሁዳ ተከታዮች ስለሆኑ፤ የኢትዮጵያ ትውልድ ሲረግማቸው ይኖራል።

በአንድ ቅጥር ግቢ የሚገኙትን ሁለቱን ቤቶቻችንን እንድናካፍል ተገደድን። ርቀነው ምክንያት የፈለገ ጠላት ቀርበንማ እንደማያኖረን አምነን ቤታችንን ጥለን እንሰደድ።

# ምዕራፍ ፲፫።

## በአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ምክር መላው ቤተሰብ እንደተባበረ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈን አሳብ መላ ቤተ ሰቡ ተቀብሎ ቤታቸውን ጥለው ሊሰደዱ ቈረጡ። የአባታቸው ንብረት የደረጀ ስለ ነበረ፤ ሁሉንም አጠቃሎ ለማንሣት ጊዜ የሚጠይቅ ሆነ። የለጐሐይቅ ግዛት ወደ አልሆነው አውራጃ መጓጓዝ ጀመሩ። ከዕለታት አንድ ቀን የመቶ አለቃ በድሉ ተረፈ ደርሶበት የማያውቅ ልቡ ከመጨነቅ ጋር በኃይል እየመታው ቀኑን ሙሉ ፍጹም ጸጥታ አጥቶ ዋለ። ከማታው በግምት ሁለት ሰዓት ሲሆን፤ ከካሣዬ ጋር ሲጨዋወቱ የጨረቃው ብርሃን በጣም ደማቅ ስለ ነበረ ሰውነታቸውን ሊያንቀሳቅሱ ከአጥር ግቢአቸው ወጣ ብለው ሔዱ። ከእኩል ሰዓት በኋላ በግምት ሦስት መቶ የሚሆን የጠላት ወታደር የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈን አባት ቤት ዙሪያውን ከቦ በአጥሩ እየዘለለ ገባ። ወታደሩ እንደ ደረሰ የአጋጠመውን በሰደፍ እየደበደበ በአንድ አነስተኛ ክፍል በሽቦ እያቈራኘ ሲያስር ከቤተ ሰቦቹ የጩኸት ድምፅ ተሰማ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በቤተ ሰቡ ላይ ምን አደጋ ደረሰ ብለው እየተሯሯጡ ከአጥሩ በር ሲደርሱ፤ ከጐረቤት ነዋሪ የሆኑ ራሳቸውን ለማዳን ከተሰወሩበት ወጥተው የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈን ካሣዬን ያዟቸው።

ቤተ ሰቡን የሚያተራምሰው የጠላት ወታደር ነውና ራሳችሁን ለማዳን ወደ ኋላ ተመልሳችሁ ፍጻሜውን አዳምጡ አሏቸው። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ምክራቸውን ተቀብለው ተመለሱና በአንድ ከፍተኛ በሆነ ተራራ ጥግ ተቀምጠው ያዳምጡ ጀመር።

ቤተ ሰቡ ሁሉ በአንድ አነስተኛ ክፍል በሽቦ ከተቈራኙ በኋላ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ታላቅ ወንድሙ በመካከላቸው ባለመገኘታቸው የጠላት ወታደሮችና በተለይም አዝማቹ በጣም ተናደዱ። ቤቱንና አጥር ግቢውን በባትሪ አንድ ባንድ ፈትሸው አለመኖራቸውን አረጋገጡ። የሚገኙበትን ሥፍራ ቤተ ሰቡ እንዲመራ በጉማሬ አለንጋ አንድ ባንድ ይሸነቁጡት ጀመር። በቤተ ሰቡ ላይ፤ የድብደባ ሥቃይ ቢበዛባቸውም ሥቃዩን በትዕግሥት ተቀበሉት እንጂ ለጠላት ወታደር ፍላጐት የሚጠቅም ድምፅ አልሰጡም።

በጐረቤት ተደብቀው ይሆናል በማለት በየመንደሩ ወታደሩ እየዞረ አተራመሰው። ጐረቤተቹም በጭካኔ ተደበደቡ። ግን የጠላት ወታደር አንዳች ነገር ሊያገኝ አልቻለም።

በቤትም በጐረቤትም የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከነታላቅ ወንድሙ አለመኖራቸውን የጠላት ወታደር ስለአወቀ መፈለጉን አቆመና ንብረት ቈጠራ ጀመረ። ሌሊቱን ሙሉ ከብቱንና ቤት ያፈራውን ልዩ ልዩ ዕቃ ሲቈጥር አድሮ ከንጋቱ በአሥራ ሁለት ሰዓት ወንድም ሴትም ሳይቀር በሽቦ ቍራኛ እንደታሠረ ከከብቱና ከሙሉ የቤት መሣሪያው ጋር ወደ ሐይቅ ተነዳ።

ቤቱና ቅጥር ግቢው ወና ሆኖ መቅረቱን የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ስለ አረጋገጡ፤ ታላቅ ወንድሙ ወደ ሚገኝበት ደሴ ከተማ ሔዱ። እንደ ደረሱ አገኙትና የሆነውን ሁሉ ዘርዝረው ነገሩት።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ሌሊቱን ሙሉ የጠላት ወታደር በቤተ ሰቡና በጐረቤቱ ላይ ከፍ ያለ ጭካኔ የፈጸመው እኔና አንተ በመካከላቸው

ባለመገኘታችን ነው። ራሳችንን ለማዳን ወደ አንዱ ዘወር ብንል አገራችን ሰፊ ናት። ነገር ግን ከሀያ በላይ የሆነውን ቤተ ሰብ በኛ ምክንያት ከመከራ ላይ ጥለን ነገ በጠላት የተደበደቡ እንደሆነ፤ የሕይወታችንን መኖር የሚያስጠላ ከፍ ያለ ጸጸት እናተርፋለን። ይልቁንም በየባላገሩ የሚኖሩ እህቶቻችን ከባሎቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ሊጠይቁን መጥተው መታሠራቸውና መደብደባቸው የበለጠ አሳዝኖኛል።

እንደ በግ መንጋ ከቤታችን እየተወሰድን እንደ ምንደበደብ ያወቅነው የነፃነት ጸጋ ርቃን እርቃናችንን በሆነ ጊዜ ነው። በኛ ምክንያት ብዙ ወገኖቻችን ከሚደበድቡ እንደሚታረድ በሬ በቀጥታ ወደ መታረጃ ቄራው ሔደን የተዘጋጀልንን የሞት ጽዋ እንቀበል።

<u>ታላቅ ወንድሙ፤</u> በሁለታችን ምክንያት መላ ቤተ ሰቡ ከሚደበድበ የኛን መደብደብ እመርጣለሁ። ነገር ግን ለጐሐይቅ አውራጃ ስለ ሆእን ለጠቅላይ ግዛቱ አመልክተን ቁርጡን እንወቅ።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> በግልጥ ከታወቀ ጠላት ይልቅ ወዳህ እየመሰለ የጠላትነት ሥራ የሚሠራ በጣም እንደሚጎዳ ሳይታወቅ እንደሚያጠፋ የታወቀ ነው። በዘር፤ በጠባይ፤ በመንፈስ አንድ ስለ ሆኑ፤ ካፒቴን ማሪዮ ያደረገው ስሕተት ነው ብሎ ከመጣብን መከራ አያድነንም።

በትንሽ ሽንቁር የሚገባ ውሃ ትልቁን መርከብ ያሰጥማል። እንደዚሁም ስለ ኢትዮጵውያን ጥፋት ካፒቴን ማሪዮ ያቀደው እንዲፈጸም በአሳቡ ይተባበርበታል እንጂ፤ ለኛ የሚበጅ አያደርግም። ግን አሳቡን ለማወቅ እንጠይቀው ካልክ መልካም ነው።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ታላቅ ወንድሙ ደሴ ከአገረ ገዢው ጽሕፈት ቤት ደረሱ። ጥቂት ደቂቃዎች ተራቸውን ጠብቀው ቢሮ እንደገቡ አስተርጓሚው ጉዳያቸውን ጤይቃቸው። ትናንትና ሌሊት ከሦስት መቶ የማያንስ የጦር ወታደር ከቤታችን መጥቶ መላ ንብረታችንንና ቤተ ሰባችንን በሽቦ አቈላልፎ አሥሮ ከንጋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ወደ ሐይቅ

እየነዳ ወሰዳቸው። የሠራነውን በደል ሳናውቅ በንብረታችንና በቤተ ሰባችን ይህ አደጋ ስለ ተፈጸመ ነገሩን እንዲያቃልሉልን ለአቤቱታ መጣን።

አገረ ገዥው፤ በመንግሥታችን ላይ ከፍ ያለ ወንጀል ካልሰራችሁ ይህ ይደርስባችኋል ብዬ አላምንም። ካፒቴን ማሪዮ አስተዋይና ለመንግሥቱ አሳቢ መኰንን መሆኑን ስለማውቅ ከፍ ያለ ጥፋት ሳያገኝ በአንድ ሰው ንብረት ይህን ጠንካራ ነገር ይፈጽማል ብዬ አልጠረጥረውም። ነገሩን ያወቀውና ያጠናው እርሱ ስለሆነ የናንተ ወንጀል ለኔ እንግዳ ነገር ነው። ስለዚህ እውነቱን እንድትነግሩኝ በጥያቄ ጊዜያችሁንና የሥራ ጊዜየን ላጠፋ አልወድምና ምንም አያደርጋችሁም ሔዳችሁ ለሱ አመልክቱት።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ታላቅ ወንድሙ በኃዘን ላይ ኃዘን የሚጨምር የጭካኔ መልስ ከተቀበሉ በኋላ፤ ወዴት መሔድ እንደሚገባቸውና ወደማን ሔደው የደረሰባቸውን ጭንቅ ለማካፈል እንደሚችሉ ግራ ገብቷቸው በሜዳ ላይ ይዋልሉ ጀመር።

ሊያደርጉ የሚገባቸውን በአሳባቸው ውሥጥ አንድ ሰዓት ያህል ሲያመላልሱ ቈይተው፤ ከካፒቴን ማሪዮ በታች አገረ ገዥ የነበሩት ያገር ተወላጅ እንዲያማልዷቸው ወደ ቤታችወ ሔዱ።

ከአገረ ገዥው ቤት እንደ ደረሱ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈንና ታላቅ ወንድሙን ፈላጊ ከሐይቅ በመኪና፤ በፈረስ ደረሰ። ፈላጊዎቹ የተፈላጊዎቹን መልክ ለይተው የማያውቁ ስለሆነ ከነሱ ፊት ስለነሱ ለአገረ ገዢው የካፒቴን ማሪዮን መልእክት አደረሱ።

የካፒቴን ማሪዮ መልእክት፤ የመንግሥታችንን ጸጥታ ለማጥፋት ቀን በጫካ እየዋሉና ሌሊት በቤታቸው እያደሩ የሚመክሩ ዓመፀኞች ቤተ ሰባቸው ተይዘው እነሱ ሳይያዙ በመቅረታቸው አዝኛለሁ። የዓመፀኞቹ አባት የጠላትን ዓይን አላይም እያለ እንደፎከረ በጊዜ ማጣት ምክንያት የመንግሥታችንን ኃያልነት ሳያውቀው ሞተ። ልጆቹ የአባታቸውን መንፈስ ተከትለው ጸጥታውን ለማጥፋት መምከራቸውን ካሁን በፊት ደርሼበት

ሦስት ቀን ብርቱ የሆነ የእሥራት ቅጣት ተፈጽሞባቸው ወደ ፊት ባይታገሡ ጉድጓዳቸውን ራሳቸውን ቈፍረው እንደሚቀበሩ አስጠንቅቄአቸው ነበር። የበለጠ ብሶባቸው የዓመፅ ሥራቸውን ስለ ቀጠሉ፤ ንብረታቸውን በሙሉ እንዲወረስ፤ ቤተ ሰባቸውና እነሱም ተይዘው እንዲደበደቡ ወስኜ ዛሬ በዚች ከተማ እንዲደበድቡ ቈርጬ ነበር። ነገር ግን ቤተ ሰቡ ብቻ ተይዞ ሲመጣልኝ፤ በተለይ የምንፈልጋቸው ወንጀለኖች ባለመያዛቸው ያቀድኩት ሳይፈጸም ቀረ። ወንጀለኞቹ በደሴ ከተማ መኖራቸውን ዋናው አገረ ገዥ በስልክ ነግረውኛል። መልካቸው ጠይምና የቀይ ዳማ፤ መጠናቸው አንዱ በሰል ያለ ሲሆን፤ አንዱ ልጅ እግር ነው።

ሁለቱም በርኖስ ገልብጠው ይለብሳሉ። መልክተኖች በመኪናና በፈረስ ልኬአልሁና በጥብቅ አፈላልገው፤ ከአሥራ ሁለት ሰዓት በፊት እንዲልኩልኝ። እነሱ ካልተያዙ በቤተ ሰባቸው ላይ አንዳችም ፍርድ ሳይሰጥ እንደታሠሩ ይቆያሉ።

ያገር ተወላጅ አገረ ገዥው የካፒቴን ማሪዮ መልእክት ደርሶኛል። ወንጀለኞቹን ስለማላውቃቸው ከካፒቴን ማሪዮ በተሰጠው ምልክት መሠረት በከተማው ውስጥ በበኩሌ አፈላልጋለሁ። እናንተም ፈልጉ።

መልእክተኞቹ ከአገር ተወላጅ አገረ ገዢው ተሰናብተው የተሰጥጣቸውን ምልክት መሠረት አድርገው በከተማው ውስጥ ለመፈለግ ተሰራጩ። መልእክትተኞቹ እልፍ እንዳሉ የካፒቴን ማሪዮ መልእክት ከመድረሱ በፊት የደረሰችሁን ወረራና የናንተን አለመያዝ ሰምቼ በአሳቤ ውስጥ ወዴት ባገኟቸው እያልኩ ሳወጣና ሳወርድ እግዚአብሔር በኔ ላይ አድሮ ሊያድናችሁ አስቦ እንደሆነ አላውቅም መጣችሁ። እንደ መጣችሁም የመጣችሁበትን ጨርሳችሁ ሳትነግሩኝ መልእክተኞቹ ተከታትለው ደረሱ። መልእክተኞቹ በከተማው ውስጥ ገብተው ያተራምሱ። እኔ በቀጥታ ሐይቅ ሔጄ ከካፒቴን ማሪዮ ዘንድ ከእግሩ በታች

ወድቄ ነፍሳችሁን ብቻ ለማትረፍ እጥራለሁ። እስከዚያ ፈላጊዎች እንዳይገኟችሁና መዘዛችሁ ለኔ ተርፎ ተያይዘን እንዳንጠፋ፤ አንድ ክፍል እሰጣችኋለሁና ሳትዘዋወሩ ጠብቁኝ።

ምንም እናንተን ለይቼ ባላውቃችሁ፤ አባታችሁ፤ መልካም መንፈሳዊ ሰው መሆናቸውን ስለማውቅ፤ ዘራቸው በጠላት እጅ እንዳይጠፉ የተቻለኝን ያህል እደክማለሁ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከታላቅ ወንድሙ ጋር ያገር ተወላጅ አገረ ገዢው በሰጧቸው ክፍል ተቀምጠው አገረ ገዢው የሚያመጡትን መልስ በናፍቆት እየተጠባበቁ የደረሰባቸውን መከራ እያስታወሱ ይወያዩ ጀመር።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ወንድሜ ሆይ፤ ቢሆንም ባይሆንም ያሁኑ ያዘልህ እንጂ በመጀመሪያ ያሰብከው አሳብ ከበለጠ ጥፋት ላይ ጣለን። ካፒቴን ማሪዮ ከቤተ ሰቡ መካከል ሲያጣን እንደ እብድ ውሻ እንደ ሚሆን አምናለሁ። ሆኖም ያለንበትን ለማወቅ ባለመቻሉ ራሱን በንዴት ከማቃጠል በቀር የፈላጊ ጕርፍ አያወርድብንም ነበር። ችግራችንን እንዲያቃልልን ለአቤቱታ ብንሔድ፤ ወንጀለኞቹ በከተማ ውሥጥ አሉና አሲዛቸው ብሎ አድራሻችንን ነገረ። ራሱ አሲዞ ሊልከን ሲችል፣ ባልታወቀ መንገድ እፈጽማለሁ ብሎ የፈጠረው ዘዴ ይበልጥ እኛን ስለጠቀመ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው። ፍርድ በእግዚአብሔር መሐል እጅ ሚዛን የተያዘ ስለሆነ ሰው ለጊዜው በመዳለል ሚዛኗን ቢያበዛባት የእጁን ሥራ አያጣም። ተበደልን፤ ተደበደብን መድረሻ አጣን የፍርድ ያለህ እያልን ብንጮህበት ካፒቴን ማሪዮ አስተዋይ ስለሆነ የተጨበጠ ወንጀል ካላገኘባችሁ አያስራችሁም አይወርሳችሁም ነበር አለን።

ሰው ከአዳም ጀምሮ በሞት ሲቀሰፍና ሞትን ያህል ታላቅ በለጋራ ሲኖርበት በዓለም እንደሚኖር ሁሉ በተፈጥሮ አንድ ዓይነት በሆነ መሰል ፍጥረት ላይ ልዩ ልዩ አሰቃቂ ግፍ ለመፈጸም ልቡ በጭካኔ የደነደነበትና የሚደነድንበት ምክንያት ፈጽሞ አይገባኝም።

ሁሉን ነገር ማድረግ የሚችል ልዑል እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት በበደለ፤ በደሉን ለመፋቅ ራሱ ሥጋውን ለሞትና ለልዩ ልዩ ሥጋዊ ስቃይ አሳልፎ ሰጥቶ ፍጥረቱን አዳነ።

ምድርን ለሰው መኖሪያ ባርኮ ሲሰጥ በምድር ላይ የሚኖር ሰብአዊ ፍጥረት ርስ በርሱ ተስማምቶና ተዛዝኖ እንዲኖር አዞት ነበር። ነገር ግን አባታችን አዳምን አስቶ ሞት ያስፈረደብን ሠይጣን ሰውን በክፋት መንገድ እየገፋ ርስ በራሱ ያፋጀዋል።

የጦር ጓደኞቼ ካፒቴን ማሪዮን መሰል በሺ የሚቈጠረውን እንደ ቅጠል አርግፈው በመሥዋዕትነት አለፉ። በጦር ሜዳ የጀግንነታቸው ተከፋይ ሆኜ ሞትን ስከተል ሞት ርቃኝ አሁን ለመታረድ እንደቀረበ በግ በመሆኔ በዕድሌ አዘንኩ።

ኢትዮጵያ አገሬ በፍቅርሽ የምቃጠለው ከልብ እንጂ ለውዳሴ ከንቱ አለመሆኑን ልቤና አምላክሽ ምስክሬ ናእው። ጀግኖች ልጆችሽ ስለ አንቺ ነፃነትና ስለ ንጉሠ ነገሥታቸው ክብር ግዳቸውን ፈጽመው መሥዋዕት በመሆኑ ሲለዩሽ፤ እነሱ በዋሉበት የጦር ሜዳ ውዬና የተቻለኝን ያህል ተከላክዬ ሞቴን አልነፈግሁሽም። በፍቅርሽ ጽናት እየተቃጠልኩ ሞተሽ እንዳየሁሽ የሕይወትሽን ትንሣኤ አያለሁ በማለት ነው እንጂ ስለ ራሴ አሁን በቅፅበት ሕይወቴ ብታልፍ በተፈጥሮ ግዴታ የምሞተውን የሞት ጽዋ ተቀበልኩ ማለት ነው።

ለመንግሥታቸውና ለአገራቸው የሚያስቡ፣ ሞተቻውን የማይፈሩ፤ በሰልፍ መሐከል ፊት ለፊት ቀርበው የሚዋጉ፤ ትምህርታቸው የሰፋ፤ እውቀታቸው የበዛ ናቸው። ትምህርት ያነሳቸው፤ እውቀታቸው የጠበበ ለጊዜው እኛን ደስ ይበልን እንጂ ለኋላ ትውልድ ምን ያሳበናል፤ በሀብታቸውና በዕድላቸው ይኑሩ እያሉ አገራቸው ወደ ጥፋት ሕዝባቸው ወደ ጉዳት ሲደርስ ዝም ብለው በሚያዩ እኛችን ሊሰጥ በየመንደሩ ያድኑናል።

ለአንቺ የሞቱልሽና ስለ ንጉሥ ነገሥታቸው ክብር በመከራ የተቀጠቀጡ የሕይወት ትንሣኤሽን አይተው ዋጋቸውን በአጠፌታ ሲቀበሉ በዕለት ደስታ ተደልለው በወገናቸው ደም የታጠቡ፤ እንደየ ሥራቸው ዋጋቸውን የሚቀበሉበትና የተሸነፈው የሚገለጥበት ጊዜ ይደርሳል። ይዘገያል እንጂ ሰው በዚህ ዓለም የሠራውን የጁን ዋጋ አያጣም።

ካፒቴን ማሪዮ በግፍ ንብረታችንን ወርሶ ቤተ ሰቦቻችን በሽቦ አቈራጭቶ ከሀያ የማያንስ የአንድ ቤተ ሰብ ዘር ለመደብደብ መትረየሱን ደግኖ ይጠብቀናል።

ከጀግኖቹ ጋር በጦር ሜዳ ተሰልፌ ተላትን በመትርየስ ያረገበገብሁባቸው ጣቶቼ በሽቦ ታሥረው ተሰቃዩ። የደም ሥሮቼም ፈዘዙ። ከዚህ ሁሉ ውርደት የጀግንነት ሞያ ሠርቼ እንዳላልፍ ከሀያ የማያንሱ ቤተ ሰቦቼ በጠላት እጅ ወደቁ። ምን ማድረግ ይሻለኝ ይሆን? ታላቅ ወንድሙ፤ ከዚህ ዓለም ያማይልፍ ነገር እንደሌለ ከኔ የበለተ ታውቃለህ። እብፊታችን የተዘረጋው መከራችን ያልፋል። በጨለማ የወደቀው የኢትዮጵያ ሕዝብም ታላቅ ብርሃን ያያል። በሞት ጥላ ውስጥ ያሉት ሁሉ ብርሃን ይወጣላቸዋል። ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በእግዚአብሔር አጋዥነት ስለ አገራቸው ነፃነትና ስለ ሕዝባቸው መደብደብ ከፍ ያለ የፖለቲካ ትግል ያደርጋሉ።

በጦር ሜዳ ሞት በመነፈግህና በጠላት እጅ ወድቀህ በመታሠርህ፤ አሁን በሞት ጥላ ሥር በመሆንህ፤ ለአገሬ ምንም ሥራ ሳልሠራላት እንደ በግ ልታረድ ነው እያልክ ታዝናለህ። የኢትዮጵያ አምላክ እስከዚህ አሳልፎ አይሰጠንም። እይምቀበለው ግፍ ለአገራችን ዋጋ ይሰጣል እንጂ ከንቱ ሆኖ አይቀርም። እግዚአብሔር ግፍ አይወድም። በግፍ ሥራ የበለጸጉ እነማን ተጠቀሙ?

# ምዕራፍ ፲፪።

## አገረ ገዥው የአገር ተወላጅ ለጐሐይቅ ሲደርሱ።

ኣገረ ገዢው (ያገር ተወላጅ) ሐይቅ ደርሰው ካፒቴን ማሪዮን ስለለመኑ፤ ለጊዜው ምሬያቸዋለሁ የሚል ቃል አገኙ። ወደዚያው ስልክ ደወሉና የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈንና ታላቅ ወንድሙን አሸከር ወደ ሐይቅ በአውቶሞቢል ይዟቸው ሔደ።

ሐይቅ እንደ ደረሱ በጭንቅ ከታሠሩት ቤተ ሰቦቻቸው ጋር ሳይቀላቀሉ፤ በአገረ ገዢው አቅራቢነት ከካፒቴን ማሪዮ ፊት ቀረቡ። በአገረ ገዢው አማካይነት በርዶ የነበረው ካፒቴን ማሪዮ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈንና ታላቅ ወንድሙን ባየ ጊዜ ደሙ ፈላና ከወንበሩ ላይ ተነሥቶ እየተንጐራደደ ጠረጴዛውን ደበደበ። ሽጉጡንም ሁለት ሦስት ጊዜ ከጠረጴዛ ላይ እያነሣ መልሶ ያስቀምጥ ጀመር። የሚናገረውንም በትክክል ለማስረዳት በጩኸት ምክንያት አስተርጓሚው ሳይችል ቀረ። በመጨረሻ በጭንቅ የታሠሩት ቤተ ሰቦቻቸው ከእስራታቸው ተፈተው ሲቀርቡ ካፒቴን ማሪዮ የበለጠ የደም ፍላት ተሰማው። የማለዱትም አገረ ገዥ በከባድ ድንጋጤ ተዋጡ። የደም ፍላቱን በጩኸት ካሳለፈ በኋላ፤ ስለ ሥራ ጓደኛዬ ይቅርታ አድርጌአለሁ። በኔ አሳብ ግን በመትረየት ልትታጨዱ መትረየሱ ተደግኖ ይጠብቃችሁ ነበር።

እናንተ ቢያጥቧችሁም አትጠሩ። ካሁን ቀደም በሦስት ቀን እሥራት ተቀጥታችሁ በተፈታችሁ ጊዜ ለወደፊቱ ከጥፋት ወጥመድ እንዳትገቡ አስጠንቅቄ ነግሬአችሁ ነበር። ከነገርኋችሁ በኋላ አይሰማብንም ብላችሁ የዓመፅ ሥራችሁን ቀጠላችሁ።

በውነት ግልጥ አድርጌ ልንገራችሁ የምፈልገው መንግሥታችን የናንተን የጥቍሮችን ዓይን ለአንድ አፍታም ቢሆን ማየት አይፈልግም።

ለፖለቲኩ መልክ አልመቸው በማለቱ ነገሩን በለዘብታ ያዘው እንጂ እንደ ፋሽስት ፕላን ቢሆን ጥቁሮችን በሙሉ ወዲያው አጥፍቶ መጨረስ ይፈልግ ነበር። ይህንንም አሳቡን ጊዜና ምክንያት እየፈለገ አንድ በአንድ እስከ አሥር ዓመት ሳይፈጽመውና በሥራ ሳይገልጠው አይቀርም። እናንተ ግን በልባችሁ ውሥጥ ካለው የወንጀል ሥራ ካልተጠበቃችሁ በዚች ስፍራ የደም መፍሰስ የሚጀመር በናንተ ይሆናል። የተወረሰ ዕቃቸው ጭምር እንዲመለስ ፈቅጃለሁና ተቀብላችሁ ሒዱ።

አገረ ገዢው ያገር ተወላጅ፤ ምስጋናቸውን አቅርበው ወደ ደሴ ተመለሱ። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ታላቅ ወንድሙ ከተወረሰው ንብረታቸው አንዳችም ሳይቀበሉ፤ በእስራት ከተሠቃዩት ቤተ ሰቦቻቸው አንድ አገልጋይ ስትቀር የቀሩትን ይዘው ዕለቱን ከቤታቸው ገቡ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ የጠላት ወታደሮች ንብረቱን በወረሱበት ቀን ልብሶቹን አጥቦ ለጊዜው የለበሰው የቤት ውስጥ ልብስ ስለ ነበረ፤ የልብስ እርዛት ደረሰበት፤ ዕቃችሁን ውሰዱ በተባለው መሠረት ዕቃውን ሊያመጣ ከአምስት ቀን በኋላ ወደ ሐይቅ ሔደ፤ ወደ ካፒቴን ማሪዮ ጽሕፈት ቤት ሲሔድ በስብከት ተታላ ከቀረችው ከአባቱ ነዋሪ አገልጋይ ጋር ውኃ ቀድታ ስትመለስ በሩቅ ተያዩ። ከቤተ ሰቡ ተለይታ የጠላት መሣሪያ የሆነችው ያለ ምክንያት ሳይሆን አይቀርምና ይህን አለኝ ወይም ይህን አደረገኝ ብላ እንዳታሲዘኝ ብሎ በሌላ ዘወርዋራ መንገድ ወደ ጽሕፈት ቤቱ ደረሱ። አገልጋይነቱ ርሱን ስትመለከት አደና ቅፍዋት ወድቃ የተሸከመችው እንስራ ተሰብሮ ኖሮ የእንስራውን መሸከሚያ ይዛ እየሮጠች የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ምን ሊያደርገኝ እንዳሰበ አላውቅም ሲያባርረኝ ወድቄ እንስራው ተሰበረ። እራሴን ግን አዳንኩ ስትል አገልጋይ ላደረጋት የወታደር አለቃ ነገረችው።

የደረቅ ጉማሬውን ይዞ በደም ፍላት ወደ ካፒቴን ማሪዮ ጽሕፈት ቤት ሲሔድ የአምሳ አለቃ እብድሉ ተረፈን በአደባባዩ ቆሞ አገኘው። ምንም

ጥያቄ ሳያደርግለት በበርኖሱ ጉሮሮውን አንቆ የተቻለውን ያህል በያዘው ጉማሬ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈን እንደ ነዶ ከመሬት ወቃው። ብዙ ሰዎች በቦታው ሲኖሩ ሊያስጥሉት ከቶ አልደፈሩም። እንዲያውም ከሰማይ የወረደ መዓት እንጂ ከምድር እንደ መጣ አልገመቱም።

የጠላት ወታደር አለቃ ክንዱን ሲደክመው የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈን ጥሎት ሔደ። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከወደቀበት ሆኖ በፃዕር ሲቃትት የጠላት ወታደር እጁን አንተልጥሎ እያንዳ ከካፒቴን ማሪዮ ፊት አቀረበው። የግፍ ዱላውን እንደሚበቃ እንደተቀበለ አይቶ ደስ አለው። የአባቱ አገልጋይ በዚያው ስለ ነበረች የሰባት ዓመት ልጅ ስላለችኝ እዲያመጣልኝ ይገደድ። በዚህ ቂም ምክንያት ይገድሏታል ብላ አመለከተች።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ በአሥራ ሁለት ሰዓት ውሥጥ የአገልጋይዋን ልጅ አምጥቶ ሊያስረክብ ከካፒቴን ማሪዮ በዛቻ ትእዛዝ ተሰጠውና ሔደ።

የተጣለበትን ግዴታ ሊፈጽም በበቅሎ ሆኖ ወደ ቤቱ ብቻውን ሲሔድ በጉማሬ የተደበደበው ሥጋውን ዘልቆ የጐን አጥንቱን የተሰማው ስለሆነ በበቅሎዋ ንቅናቄ መላ ሰውነቱን ውጋት ተሰማው። ይህ ዓይነት አስቸጋሪ ፈተና ሲደርስበት ሕመሙን የሚያስረሳ ከፍ ያለ ነገር ማሰብ ልማዱ ስለሆነ፤ በጠራ ሜዳ ላይ በበቅሎ እየተጓዘ ብቻውን የነጋገር ጀመር።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ከደረሰብኝ ነገር ሁሉ ሰው መሆኔንና ሰው ሆኜ መፈጠሬን ጠላሁ። ድኩም ሆኜ በመፈጠሬ መልካም ነው ብዬ የሠራሁት ከጥፋት ላይ ይጥለኛል። ከካፒቴን ማሪዮ እጅ በእግዚአብሔር ኃይል ሕይወቴ ከተረፈች በኋላ ፈራሽ ሥጋዬን የምከለልበት ልብሴ ስለ ተዘረፈ ላስመልስ ብሔድ ጀርባዬን አቀኑስየ ተመለስኩ።

የአባቴ አገልጋይ ባልሠራሁት ሥራ ቆማ አስደበችኝ። ልጅዋን አምጥቼ እንዳስረክብ አስገደደችኝ። ከልጅነት አሁን እስከደረሰችበት ዕድሜ በአባቴ ቤት ማደጓንና ቤተ ሰብነቷን ባገኘችው ለውጣ አሳልፋ ሰጠችኝ።

ሁሉንም ነገር አየሁ። ይህ ቀን የሚያልፍበትን ጊዜ ለማየት ቸኰልኩ። እንደዚሁ እንደሆነ እንደማይቀር በተስፋ ሳምን ሕይወቴ ብጠላሽም አንቺ አልጠላሽም። ሥቃዬን በሥጋዊ አካሌ እንድቀበል ዕድሌ መረጠኝ። ከዚህ የከፋና የባሰ ካልመጣ ይህን ከሽልማት እቈጥረዋለሁ። ይህ ውርደትና መንከራተት እንደ መንጋ መነዳት የመጣው የነፃነትና የመሪ መታጣት ነው። በሕይወቴ ሙሉ ይህ ዓይነት ሳይደርስብኝ እንደፈለግሁ የምናገረው፤ ያለ አሳብ የማገኘው የሕይወት እንቅልፍ፤ ወደ ፈለግሁበት አገር የምዘዋወረው፤ በጠቅላላው የትናንትናው የነፃነት ኑሮ ትዝ ሲለኝ ሕልም እንጂ እውነት አይመስለኝም። ሁሉም ከእጅ ሳይወጣ እንደ ቀላል ነገር ይታያል። ከእጅ ከወጣ ግን ፀፀቱ እንደ እግር እሳት ያቃጥላል እያለ ከቤቱ ደረሰ።

# ምዕራፍ ፲፯።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ የተዘረፈ ልብሱን ለመቀበል ወደ ለጐሐይቅ ሲሔድ

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ የተዘረፈ ልብሱን ለመቀበል ወደ ሐይቅ ሔዶ የደረሰበትን ፈተና ዘርዝሮ ለቤተ ሰቡ ነገረና ከካሣዬ ጋር ሆነው የአገልጋይዋን ልጅ ወይዘሪት ትሻይ አንቺን ይዘው ሐይቅ ደረሱ።

የተወሰነበት ሰዓት ሊያልቅ ሠላሳ ደቂቃ ሲቀረው ወይዘሪት ትሻይ አንቺን ይዘው ሲደርሱ እናትዋ ከካፒቴን ማሪዮ ጽሕፈት ቤት በውጭ

ስትጠባበቅ አገኟት። ልጅዋን ለብቻ አግልላ ከእኩል ሰዓት የሚበልጥ አነጋገረቻት።

ከፉውንና ደጉን ለይታ የማታውቀውን ወጣት የተንኮል ሥራ በማስተማር ከካፒቴን ማሪዎ ፊት ስትቀርብ የምትናገረውን አስተናቻት። ወዲያው ከካፒቴን ማሪዎ ጽሕፈት ቤት የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ልጅቱን ይዘው ሲቀርቡ፤ እናቷም አብራ ቀረበች። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከመሔዱ በፊት በተለይ ልጅቱ እንድትጠየቅ እናቷ ለካፒቴን ማሪዮ አሳሰበች። ካፒቴን ማሪዮ አሳቧን ተቀብሎ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከካሣዬ ጋር በውጪ እንዲቆይ አደረገ።

<u>ካፒቴን ማሪዮ፤</u> ወይዘሪት ትሻይ አንቺ እናትሽ የኛ አገልጋይ ሆና ጠቅማናለች፤ ከእናትሽ ተለይተሽ ከነአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ጋር ብትቀመጪ ያገኡላሉሻል ብዬ እንድትመጪ አደረግሁ። እናትሽ ውኃ ስትቀዳ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ቢያገኛት አደጋ ሊጥልባት ሲያባርራት ሸሽታ አመለጠችው። በእናትሽና በነአምሳ አለቃ በድሉ መካከል ከፍ ያለ የመንፈስ መለያየት ቂም ተመሥርቷል። ከነሱ ቂም እንድትድኑ ማድረግ የምችል እኔ ነኝ። ስለዚህ ይዞሽ ሲመጣ በመንገድ ምን እንዳለሽ፤ በቤት ውሥጥም ምን እንዳሉና መሣሪያም እንዳላቸው እንድትነግሪኝ እፈልጋለሁ።

<u>ወይዘሪት ትሻይ አንቺ፤</u> እናትሽ ትፈልግሻለችና እንሒድ ብሎ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ቢጠይቀኝ እናቴ በሥጋ ብትወልደኝ ያሳደጉኝ እንደ ልጆቻቸው አድርገው የሚጠብቁኝ እማምዬ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ እናት ስለሆኑ አልሔድም ብዬ ነበር። በአንቺ ምክንያት ከፍ ያለ መከራ ያገኘናል፣ ሒጂ ስላሉኝ፤ በኔ ምክንያት እነሱ ከመከራ ላይ እንዳይወድቁ መጣሁ እንጂ ፈቃዴ ሆኖ አልመጣሁም። በመንገድም ሆነ በቤት ምንም ሲናገሩ አልሰማሁም። በቤታቸውም መሣሪያ የለም። በእናቴና በአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ መካከል የማውቀው ቂም የለም። እናቴ ያደገችው

በአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ አባት ቤት ነው። የሚመለከትዋትም እንደልጃቸው ነበር። አሁን በነሱ ላይ መከራ ሲወድቅባቸው ከድታቸው ከዚህ የተቀመጠችበት ምክንያት አልገባኝም። እኔ ከዚህ መቀመጥ አልፈልግም። ተመልሼ መሔድ አለብኝ።

በናትዋ አሳብ የሌለ እንግዳ ነገር ያለ ፍርሐት በመናገሯ እናቷ ተናዳ ይህንን እንድትናገር የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ መክሯት ነው እንጂ ከርሷ ከአንድ ፍሬ ልጅ ይህ አሳብ አይፈልቅም። ካፒቴን፤ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈን ይመርምሩልኝ። ለርሷ ከኔ እነሱ ሊያስብላት ስለ ማይችሉ ተመልሳ እንዳትሔድብኝ እያመለከትኩ፤ እነሱ የጫኗትን ለማራገፍ ብላ የተናገረችውን እንዳይቀበሏት ስትል አመለከተች። የእግዚአብሔር ረድኤት የተለየው ሰው የተሳሳተም ቢሆን አንዳንድ ጊዜ በመንፈስ ኃይል ትክክል ነገር ይናገራል። ከአንደበቱ ደህና ነገር ወጥቶ የማይውቀው ካፒቴን ማሪዮ ወጣቷ የተናገረችው ከአሳቧ የነቃ ሊሆን ይችላል። እንዳልሽውም ላይሆንም ይችላል።

ልጅቱ ከዚህ ለመኖር ካልፈለገች አስገድደን ልናስቀራትና ልንመልሳት አንፈልግም። አንቺ በናትነትሽ አባብለሽ አስቀሪያት። ስለዚህ ጉዳይ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈን ማነጋገር እፈልጋለሁ አለ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ከካሣዬ ጋር በካፒቴን ማሪዮ ፊት ቆሙ። ኃይል በተሞላ አነጋገር አሁንም ከተንኰል መንገድ አልወጣችሁም። ይህች ከፊታችን የቆመችው ልጅ ምን እንድትናገር መከራችሁ አመጣችኋት ብሎ ቢጠይቅ፣ ምንም የተናገርናትና የመከርናት ነገር የለም፤ እግዚአብሔር እንደመራት ይህን አሉኝ ትበልና የፈለግሽውን አድርግ ሲል የአምሳ አለቃ በድሉ ተፈረ በቈራጥነት መለሰ። የሚነጋገሩበት በአስተርጓሚ ስለ ነበረ፤ ወይዘሪት ትሻይ አንቺ ነገሩን ሰምታ ምንም እንዳልነገሩኝ ነግሬአችሁ ነበር። አሁን ግን ነገሩኝ ብዬ እንደነገርኳችሁ አስመስለው በመናገርዎ በካፒቴን አዘንኩ ብላ መለሰች። በአነጋገሯ ካፒቴን ማሪዮ ተደንቆ ወጣትዋ

በሰው አሳብ ተመርታ የምትናገር አይደለችም። በዚህ ዕድሜዋ ለመናገር ዕድል ቢስጣት ነው። ስለዚህ እነ አምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ወደ ቤታችሁ መመለስ ትችላላችሁ ብሎ አሰናበታቸው።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ ሲሔዱ ወይዘሪት ትሻይ አንቺ በኃይል እያለቀሰች አብራ ለመሔድ የተቻላትን ያህል ብትሞክር እናትዋ በግዴታ በወታደር ወደ ሠፈርዋ አስወሰደቻት።

የአምሳ አለቃ ብድሉ ተረፈና ካሣዬ ጉዞአቸውን ወደ ቤታቸው ቀጠሉ። መንገዱን አቋርጠው ሳያውቁት ከቤታቸው እንዲደርሱ በመንገዳቸው ላይ አሳብ ለአሳብ ተለዋወጡ።

ካሣዬ፤ ጊዜ የማያሳየውና የማያመጣው ነገር የለም። የአባትህ አገልጋይ እጅህን አሳልፋ ሰጠችህ። የአሥራ ሁለት ዓመት ወጣት ከእውነት መንገድ ርቃ የሐሰት መሣሪያ እንድትሆን ወላጅዋ የተቻላትን፤ ያህል ጣረች። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ከልጆች ስለማይለይ፤ የወጣትዋ ለጋ አንደበት ሐሰት እንዲነገርበት ባለማድረጉ ወጣቷ በእውነተኛ ነገር ጸንታ የናቷን ስሕተትና ከሐዲነት በፊቷ ገለጠች። የወጣትዋ ንግግር የጨካኙን የካፒቴን ማሪዮን ሕሊና ሰለመታው በኛ ላይ ሊፈጸም ያሰበውን አሳብ ሊያስቀረው ምክንያት ሆነችን።

ይህ ዓይነት ነገር በሰው ላይ ሲደርስ ትልቅ ትምህርት ትቶ የሚሔድና የሰውን ከንቱነት የሚያሳይ ነው። ለምሳሌ ለሰው ከተወሰነለት ዘመን ብዙውን ዕድሜዋን በአባትህ ቤት ያሳለፈች አገልጋይ በጠላት መንፈስ ተማርካ በወገኖችዋ የሞትና የቂም ሥቃይ እንዲፈጸም ስታደርግ በአባትህ ቤት በኖረችባቸው ዘመናት የተካፈለችሁት ደስታ ከፊቷ ሳይደቀን ቀርቶ ይሆን? አባትህ በመንፈሳዊ ሥራ ሰውነታቸውን የገዙ ስለሆነ መላ ቤተ ሰባቸውን የሚመለከትዋቸው ከአብራካቸው እንደተከፈቱለት ልጆቻቸው እንደሆነ እናውቃለን። አብሮ መብላትና ማደግ ለዚህ ጊዜ ሊሆን ነበር፤

ግን ጊዜ ሲከዳ ለታሪክ ትዝብት ለመጣል የሰውን ልብ በጭካኔ ያደነድነዋል።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ሰው በዚህ ዓለም ሲፈጠር መከራና ደስታ እየተፈራረቁበት ሊኖሩ ነው እንጂ፤ በደስታ ብቻ ተሸፍኖ ሊኖር አይደለም። ሰው በመከራ ካልተፈተነ በዓለም ላይ ጥሎት የሚሔደው ታሪክ የለም መከራ ለሰው አልተፈጠረም።

ሰው ለመከራ ተፈጥሮአል እንጂ። እጠቅላላው ጉዳይ ሳንደርስ በተለይ በቤታችን በደረሰው አዝነን ብዙ እንናገራለን። ሰው ደካማ ፍጥረት ስለሆነ ከስሕተት መንገድ አይቀርም። የማይሳሳት እውነተኛ ዳኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህን ዓለም ኃጢአት ለማስተስረይ ራሱን ለሞት ስለሰጠ የርሱ ደም የዓለምን ኃጢአት ፋቀ።

ምድራዊ ንጉሥ እንደሌላው፤ በፍጡር ባሕርዩ ቢያልፍና ቢሞትም ቅብዓ መንግሥትን የተቀናጀው ከእግዚአብሔር ነው። ለመንበረ መንግሥት በቅቶ ምንም ቅብዓ መንግሥት ቢቀባ ፈሪሐ እግዚአብሔርን መሣሪያ ካደረገ፤ የሚሠራው ሥራ ሁሉ የተወደደ ሆኖ ረጅም ጊዜ በዓለም ገዢ ሆኖ ይኖራል። የአንድ አገር ትልቅነትና ዕድል የሚታወቀው ፈሪሐ እግዚአብሔር ያደረበት ታላቅ መሪ ሲያገኝ ነው። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እግዚአብሔርን ፈሪ፤ የፍርድን ሚዛን ጠባቂ ስለሆኑ፤ እግዚአብሔር ሳይጋልጣቸው ከንጉሣዊ ቤተ ሰባቸው ጋር ተሰደው፤ ስለ ኢትዮጵያ ከጦርነት የበለጠ የፖለቲካ ጦርነት በማድረግ ላይ ናቸው።

ለፈተና ባላያችን ላይ የወረደው ይህ ግፍ የሚጠፋበትና ግፈኞቹና አጥፊዎቹ ብድራቸውን የሚቀበሉበት ቀን በግርማዊነታቸው ትግል በቅርብ ጊዜ ይደርሳል።

በኛ ላይ ግፍ ለመሥራትና ለማሠራት የሚጣደፉት ነገ የእጃቸውን ሥራ አያጡም። ስለዚህ ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው እንደሚባለው ሁሉም የሥራውን ዋጋ ስለማያጣው መከራቸውን በትዕግሥት እንቀበል።

# ምዕራፍ ፲፰።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ከቤታቸው ሲደርሱ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፣ ከቤታቸው ደርሰው የዋሉበትንና ወይዘሪት ትሻይ አንቺው ተጠይቃ የሰጠችውን መልስ ለቤተ ሰቡ ሁሉ አሰሙ። መላ ቤተ ሰቡ በአንድ ድምጽ ወይዘሪት ትሻይ አንቺን አመስግነው መረቁ።

ካፒቴን ማሪዮ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈን ቤተሰብ ሕይወት ካላጠፋ እንደማይተኛ በአነጋገሩ የተረዱት ስለሆነ ቤታቸውን ጥለው ጓዛቸውን አንሥተው ተሰደዱ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ወደ ሸዋ መሬት ለመምጣት ቆርጠው ስለ ተነሡ ካሁን ቀደም አንዳንድ ወሬ ያሰሙአቸውን ወይዘሮ የምሥራችን ከመሠናበታቸው በፊት ለመጠየቅ ከቤታቸው ሔዱ። ወይዘሮ የምሥራች ባዩአቸው ጊዜ ካሣዬ አንተ ከኔ ዘንድ የምትመጣው በአሳቤ በአስታወኩህ ጊዜ ነው ብለው በደስታ ተቀበሏቸው። ካሣዬ፣ በየጊዜው የጠላት መከራ ባይለየን ግርማዊነታቸው የኢትዮጵያን ጉዳይ ለዓለም መንግሥታት ጉባዔ ዤኔቭ ማቅረባቸውን ስንሰማ ለሰውነታችን ልምላሜ ሰጥቶናል። አሁንም ሌላ የሰሙት እንዳለ እንዲያካፍሉን መጣን።

ወይዘሮ የምሥራች፤ ነገር የሚሰማው እንደ አመጣጡ ስለሆነ፤ ደጉንም መጥፎውንም ጆሮ ይሰማል። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን ጉዳይ ለዓለም መንግሥታት ጉባዔ ዤኔቭ ማቅረባቸው የጠላትን የግፍ ሥራ አጉልቶ በማሳየቱ ጠላት በኃዘንና በኃፍረት ላይ ወድቋል። በዚህ ብስጭት በአገር ውሥጥ ያለውን ሰላማዊ ሕዝብ ሽማግሌ፤ ሕፃን ሳይቀር መፍጀት ለጠላት አገዛዝ የሚጠቅም መስሎ ስለታየው አጋጣሚ ምክንያት ይፈልግለት ነበር።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ትውለበለብበት በነበረው ቤተ መንግሥት የጠላት ባንዲራ ተሰቅሎ በማየት በአገር ፍቅር ልባቸው የተቃጠለ ኢትዮጵያውያን በደም ከወረሱት ጀግንነት በግራሲያኒ ላይ የቦምብ አደጋ ጣሉ። ይህን ምክንያት በማድረግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሕፃንና ሽማግሌ ሳይቀር እየተገደለ ከኢትዮጵያ መሬት እንዲጠፋ ግራሲያኒ ትእዛዝ በመስጠቱ፤ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ እየታደነ ተደበደበ። የጦር መሣሪያ ያለው ፋሽስት በጦር መሣሪያ፤ በእጁ የጦር መሣሪያ ያልያዘ በአካፋና በዶማ ኢትዮጵያውያንን ደበደበ። የኢትዮጵያውያን ደም በአዲስ አበባ እንደ ክረምት ጐርፍ ወረደ፤ ቃጠሎው እስካሁን ከተማዋን እንደ ሸፈናት ነው። በያንዳንዱ የሣር ክዳን ቤቶች ኢትዮጵያውያን ተሰብስበው በእሳት ተቃጥሉ። መንገዶችና መንደሮች በኢትዮጵያውያን ሬሳ ሙሉ።

ይኸውም አፈጻጸም በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በየአገሩ እንዲፈጸም ስለታዘዘ በዚህ ግዛት ኢትዮጵያውያን እንዲደበደቡ የተወሰነው ሐይቅ በመሆኑ፤ ካፒቴን ማሪዮ ከጧት እስከ ማታ ደም በማፍሰስ፤ እጆቹ በደም ተነክረዋል። የቦሩ ሥላሴ ካህናት ስማቸውን ለጊዜው የማስታወሰው መላከ ፀሐይ ተክለአቢብ፤ መርጌታ አሰጋኸኝ፤ ገበየሁት አሰጋኸኝ፤ ዓለሙ ፀምሩ፤ መምሬ ፈለቀ፤ ኃይለ ሥላሴ ፈለቀ፤ ሌሎቹም በመቶ የሚቆጠሩ እየተያዙ በሐቅ ተደበደቡ። ለወደፊትም ሐይቅ የኢትዮጵያውያን መገደያ ቄራ እንዲሆን ተቈርጧል።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ከዕለት ዕለት ጠላት በኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጸመው ግፍ እየቀጠለና እየመረረ ሔደ። ይህን ዓይነት ግፍ በሰማሁ ጊዜ ከፊቴ የሚደቀነው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነፃነት የሌለው ሕዝብ በጠላት እጅ እንደ ከብት እየተነዳ የሚወሰድ ነው ያሉት ቃል ነው ኢትዮጵያውያን ከየቤታቸው እየተለቀሙ ታረዱ በቤታቸው ውስጥ እንደሆኑ ተቃጠሉ። ከዓለማዊም ነገር ርቀው በየገዳማቱ እግዚአብሔርን በማገልገል በብሕትውና የተወሰኑ መነኰሳት እየተፈለጉ ታረዱ። የእግዚአብሔር ቃል የሚነገርባቸውና መሥዋዕት የሚሠዋባቸው ገዳማትና አብያተ ክርስትያናት አልባሳትና ንዋየ ቅድሳት ልዩ ልዩ መንፈሳዊ መጻሕፍት እየተለቀሙ ተቃጠሉ። የግርማዊነታቸው ትንቢታዊ ቃል አንዱም ሳይቀር ተፈጸመ።

ግርማዊነታቸው ለጊዜ ሕዝባቸውን በአካለ ሥጋ ቢለዩት፤ በመንፈስ ምንም ጊዜ የማይለዩት በየቀኑ የሚደርስበትን የግፍ አሟሟት ለዓለም መንግሥታት ጉባዔ በጧት በማታ ያሰማሉ። በዓለም የሚኖር ሰብዓዊ ፍጥረት፤ በአንደኛው የሚደርስበትን የግፍ አሟሟት እያየ ዛሬ ቸል ቢል ነገ በላዩ ላይ ይህ ዓይነት ዕድል እንደሚደርስበት ዓለም ዘንግቶ የኢትዮጵያን ጉዳይ በውዝፍ አቆየው። አውሮፓም ይህን ነገር እንዳለቀ አድርጎ ቢቈጥረው በራሱ የሚደርስበትን የሚጠብቀውን ያህል ዕድል ማሰብ ይገባዋል ብለው በጉባኤው ላይ ግርማዊነታቸው የተናገሩን ታሪካዊ ቃል ዓለም የማየትና የመርመር የማመዛዘን አእምሮ ስለ ጐደለው፤ አፋጥኖ ሊሠራበት አልቻለም።

ዓለም በፊት ተደግሶ የሚጠብቀውን የያንዳንዱን፤ ጥፋት ቢያውቅ፤ ኢትዮጵያ በግፍ መወርወርንና ሰላማዊ ሕዝቧ እንደ በግ ዕለት በዕለት የሚፈጸምበትን መታረድ እየሰማ እንደ ቀላል ነገር ባልተመለከተውም ነበር፤ ሰው መጥፊያውን የማያውቅ ደካማ ፍጥረት ስለሆነ የአንዱ ቤት ሲፈርስ ነገ በራሱ እንደሚደርስ አይገምትም።

«እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ ብሎ ግርማዊነታቸው የተናገረው ትንቢታዊ ቃል፤ በዓለም መንግሥታት ጉባዔ ሸንጎ በታላቅ ፊደል ተጽፎ ቢለጠፍ ቧትና ማታ የዓለም መንግሥታት ጉባዔ እያየ፤ ለእግዚአብሔርና ለታሪክ ምስክር ሆኖ የሚኖር ትክክለኛ ዳኝነት በሠራ ነበር። ሰው ቢያልፍ የተናገረው ቃሉ ሳያልፍ ሲነገር ይኖራል። ይህ የግርማዊነታቸው ንግግር በዓለም ታሪክ ለመጀመሪያው ገጽ ይዞ ለትውልደ ትውልድ ሲተላለፍ የሚኖር ነው።

በዘሩና በዘራችን መካከል ያለውን ቂም ለመበቀል ጠላታችን አገራችንን በግፍ ወርሮ በሰላማዊ ሕዝቦች ላይ ታሪክ የማይረሳውን ግፍ ሲፈጽም፤ ዝም ብሎ ያየ ዓለም፤ ዓለምን ለማጥፋት በተነሡ አንዳንድ መሪዎች ምክንያት እያንዳንዱ የራሱን የጥፋት ጽዋ እንደሚቀበል አይጠረጠርም።

ሐይቅ ከአንድ ሁለት ጊዜ በካፒቴን ማሪዮ ፊት ስቀርብ በዚች ስፍራ መጀመሪያ ደም ማፍሰስ የሚጀምረው በናንተ ነው። የመቃብር ጉድጓዳችሁን ራሳችሁ ቈፍራችሁ ትቀበራላችሁ። አጋጣሚ ጊዜና ምክንያት አጥተን ነው እንጂ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ከኢትዮጵያ መሬት አጥፍተን በምድሯ ብቻ ለመጠቀምና አገሯ በወገኖቻችን ተመልታ ኢትዮጵያ የተባለው ስም እንዲጠፋ የታቀደ ድርጅት እንዳለ ነግሮን ነበር።

ሲመኘውና ሲጠባበቀው የነበረው ጊዜና ምክንያት ሰለመላ ሐይቅ የኢትዮጵያውያን መታረጃ ቄራ ሆነ።

ካሣዬ፤ ስለ አገራችን ጉዳይ ለመንፈስ ድፍረትና ኃይል የሚሰጥ ወሬ በተጠማንበት በመጀመሪያው ጊዜ ወይዘሮ የምሥራች ቤት ስሔድ ግርማዊነታቸው የኢትዮጵያን ጉዳይ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ዤኔቭ ማቅረባቸውን ስለ አሰሙ፤ በየጊዜው የሚደርስብንን መከራ በትዕግሥት ለመቀበል ለመንፈሳችን ኃይል ሰጠን። ሁለተኛ ጊዜ ስጠይቃቸው የአቡነ ጴጥሮስን መደብደብ ነገሩኝ። በግራዚያኒ ላይ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን

በምብ መጣላቸው ደስ ሲለን ይህን ምክንያት በማድረግ በሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በአካፋና በዶማ መደብደባቸውንና አዲስ አበባ መቃጠሏን በሦስተኛው እግሬ በመስማቴ ልቤ በኃዘን ተመታ። ብዙ ርቀት አቋርጦ፤ በሙሣሪያው ተመክቶ የመጣ ጠላት ከየካቲት ፲፪ ቀን ጀምሮ በኢትዮጵያ ገዳማት ከዓለማዊ ኑሮ ርቀው ሕይወታቸውን ሙሉ የፈጣሪአቸው አገልጋይ የሆኑትንና ኢትዮጵያዊ የሆነውን ሌላውንም ሁሉ ከኢትዮጵያ ለማጥፋት ጠላት የዘረጋው አቅድ ከሥራ ላይ ዋለ። ሁሉን የምትገዛ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሆይ!

በመከራ ሥጋ በመከራ፤ ነፍስ የተጨነቁትን የምታሳርፍ፤ አቤቱ በአንተ አምነው በጸናችና በቀናች ሃይማኖት ሆነው የሞቱ የወንዶችን የሴቶችን ነፍስ ዕረፍተ ነፍስ ሰጥተህ አሳርፍ።

በሕይወት ሆነው በመከራ ሥጋ ለሚጨነቁት ለሚያዝኑትና ለሚያለቅሱት ዕረፍተ ሥጋን ስጣቸው። በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ የሚዘንመውን የመከራና የሞት ዝናም አስታግሥ።

በሞት ጥላ ሥር ለወደቀው ሕዝብ እውነተኛ ፍርድ ለመጠየቅ ባሕሩንና የብሱን አቋርጠው የተሰደዱትን የኢትዮጵያን መሪ በቸርነትህ አንተ አስቀድመህ መርጠህ የሰጠህንን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በተራዳኢነትህ ደግፈህ ዕንባቸውንና መሪር ኀዘናቸውን ተቀበል።

ወስነህ በሰጠኸው አገሩ፤ ቤቱ፤ ንብረቱ በግፍ የተደበደበውንና የፈሰሰውን የኢትዮጵያንን ደም፤ ድምፅ ተቀብለህና በንጉሠ ነገሥቷ ላይ አድረህ የቸርነትህን ሥራ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ግለጥ።

<u>ወይዘሮ የምሥራች፤</u> የአምሳ አለቃ በድሉና ካሣዬ በአሰማኋችሁ ወሬ ጥልቅ የሆነ ኃዘን ስለ ተሰማችሁ እያንዳንዳችሁ የተናገራችሁትን በጸጥታ አደመጥኩ። እውነት ነው ነገሩ በጣም ያሳዝናል። እንኳን በሺ የሚቈጠር አንድም ቢሆን በከንቱ ደሙ ሲፈስ ያሳዝናል። ነገር ግን አገርን ያህል ጉዳይ

ቀርቶ የአንድ ቤተሰብ ንብረት ለማጥፋት የመጣ ባለጋራ ያለደም ሊለያይ አይችልም። አገራችን በጠላት ብትወረር ከወረራ፤ ለመዳን የምትችለው በወገኖቿ ደም ነው። ጠላት በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የግፍ መቅሠፍት ሲፈጸም በሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ቢሞቱ በጦር ሜዳ በጀግንነት በግንባር ሲዋጉ ሁለት አጠፌታ ከጠላት ወገን እንደ ሞተና እንደሚሞት እናውቃለን። በእጁ መከላከያ ሰንጢ እንኳን የሌለውን ሕዝብ አሮጌ፤ ሽማግሌና ሕፃናት ብሎ ሳይመርጥ፤ ከየመንደሩ እየለቀመ ቢገድል አገዳደሉ የወንድነት ታሪክ የማይመለከት የጭካኔንና የግፍ ሥራን የሚያሳይ ስለሆነ እግዚአብሔርና ታሪክ ዋጋውን አያስቀሩትም። ዕንባ፤ ኀዘን፤ በግፍ መሞት፤ አይቀሩም። እነዚህ ተባብረው ድምፃቸውን ለእውነተኛው አምላክ ሲያሰሙ በመጨረሻው የክብርና የሕይወት አክሊል ያቀዳጃሉ። ያሁኑ ትውልድ በጠላት እየተጨፈጨፈ ቢሞት ለማትተው ነዋሪ አገሩን ለሚከተለው ትውልድ ዘለዓለማዊ የነፃነት ቅርስ ተክሎ በታሪክ ጐዳና የሚያልፍ ስለሆነ፤ ሞቱን ከሞት ቈጥረን ልናዝን አይገባንም።

በጀግንነትና በቆራጥነት እንደ አንድ ወታደር ከጦር ሠራዊታቸው ጋር ሆነው በጦር ሜዳ ከተከላከሉ በኋላ በጦር ሠራዊቱ ላይ የሚዘንምበት የቦምብና የመርዝ ጢስ ጦሩን ስለፈታው ሠራዊታቸውን ፈጽሞ ከማስፈጀት ከሞት የተረፈውን የጦር ሠራዊታቸውን ይዘው መመለስና የዓለም መንግሥታት ጉባኤን እውነተኛ ፍርድ መጠየቅ ለአገራችንና ለኛ የበለጠ የሚጠቅም በመሆኑ ግርማዊነታቸው ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር ጉባኤ ሔደዋል።

እስካሁንም ባደረጉት ታሪካዊ ንግግር ዓለም ስለ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ስለ ራሱ ከሥጋት ላይ ወድቆአል።

ሕዝቤ ሆይ፤ ወደሀ ወደ ቤትህ ግባ፤ ደጅህንም በኋላ ዘግተህ ጥቂት ጊዜ ተሸሸግ የተባለውን እያስወስን፤ በዱር፤ በገደል እየተዘዋወርን የመጣብንን ጠላት ጠንክረን መከላከል ያስፈልገናል።

ካፒቴን ማሪዮ በኢትዮጵያውያን የግፍ ደም ስለሰከረ ወደ ኋላ ያለፋችሁትን ነገራችሁን አስታውሶ እንዳያጠፋችሁ ዘወር ብላችሁ የመቅሠፍቱን ጊዜ ብታሳልፉት ይሻላል።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ ወይዘሮ የምሥራች የተናገሩትን ስምተውና በአነጋገራቸው ተደንቀው ስለ መልካም ምክራቸው አመስግነው ተለያዩ።

ወይዘሮ የምሥራች ወደ ኋላ ያለፋችሁትን በማስታወስ ካፒቴን ማሪዮ አሲዞ ያስደበድባችኋልና፤ የመቅሠፍቱን ጊዜ ወደ ሌላ ዘወር ብላችሁ አሳልፉት ብለው የነገሯቸውን የአምሳ አለቃ በድሉ ለመምጣት የነበራቸን አሳብ ጭምር ስለ ቀሰቀሰው ይህንኑ ፍጹም ቁርጠኛ አሳብ አደረጉ።

# ምዕራፍ ፲፱።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ወደ ሸዋ ለመምጣት ሲያስቡ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ ወደ ሸዋ ለመምጣት ባደረጉት ቊርጠኛ አሳብ ጉዳዩን ለቤተ ሰብ ያሰሙ እንደሆነ አሳባቸውን እንደሚቃወሙ ስለ ተገነዘቡ በምሥጢር ይዘው ከሥራ ላይ ለማዋል ተጣደፉ።

ለአሳባቸው ዋና ተከላካይ የሆነው የፈቃድ ወረቀት (በርሜሶ) ስለሆነ ይህን የፈቃድ ወረቀት እንደምንም ለማግኘት እንደ ሚችሉ በብዙ መንገድ

ሞከሩ። ነገር ግን የፈቃድ ወረቀት በቀላሉ ለማግኘት ባለመቻሉ ምንም ዓይነት ሙከራ ቢያደርጉ የሚያገኙበት መንገድ አጡ።

ካሁን ቀደም የደሴን ከተማ በፈሊጥ ገብተው እንደተመለከቱ አሁንም ዘዴ መፈለግ ግድ ስለሆነ፤ ካቀረቧቸው ብዙ ነገሮች ታላላቅ መኪና (ትሬንታ ኳትሮ) በመንገድ ሲተላለፍ አቁመው ለሾፌሩ ሁለት ፊያሽኮ ቢኖ ገዝተው ከዶሮና ከእንቍላል ጋር ሊያበረክቱ ተስማሙ። በስምምነታቸው መሠረት፤ አዘጋጅተው ከከተማ በራቀ መንገድ ዳር ቆመው ዶሮና እንቍላል ሲያሳዩ ባለ መኪናው ስላቆመላቸው ቢኖውን ጭምር ሰጥተው ረዳቶቼ ናቸው ብሎ አዲስ አበባ እንዲወስዳቸው አጥብቀው ለመኑት። ልመናቸውን ተቀብሎ የጋራዥ ሠራተኛ የሚለብሰውን ልብስ አልብሶ፤ በመኪና ጫናቸው። ከምትፈራውና ወጥመድ ከሆነችው ካራ ቆሬ ከምትባለው ጠባብ በር መኪናው ቆሞ በተቈጣጣሪ (ካራቢኒየሪ) ሲመረመረ በአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና በካሣዬ ላይ ጥያቄ ቀረበ። በዚህም ጊዜ የመኪናው ባለቤት ረዳት ሠራተኞቼ ናቸው ብሎ መልስ ስለ ሰጠ ጥያቄው ቀረ።

አዲስ አበባ ለመግባት የጊዜው ሁኔታ አስጊ ስለ ነበረ መኪናው ደብረ ብርሃን ሲቆም የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ደብረ ብርሃን ቀርተው ከዘመድ ቤት ጥቂት ቀን ለመቆየት ወደ ሚጣቅ ሔዱ። የኢትዮጵያ ጀግኖች በየተራራውና ሸንተረሩ እየተዘዋወሩ በአርበኝነት በጠላት ላይ የሚደርጉትን የጀብዱና የጀግንነት ሥራ በመስማታቸው፥ የኢትዮጵያ የጀግናና የወንድ እናት በመሆንሽ ኲራት ይሰማሻል። ልጆችሽ በተራራዎችሽና በሸንተረሮችሽ ከለላ ካገር አገር እየተዘዋወሩ የሚፈጽሙት የጀግንነት ሥራ ጠላትሽን አሳፍሮታል፤ እያሉ ልባቸው በወገኖቻቸው የጀግንነት ሥራ ተመልቶ ከሚጣቅ ወደ ደብረ ብርሃን ተመለሱ።

ከዚያም የጠላት ሁኔታ ቢመለከቱ በኢትዮጵያ አርበኞች የጀግንነት ሞያ የጠላት መንፈስ ወድቆ ኢትዮጵያን ለመውረር ከአገሩ የወጣበትን ቀን

እያንዳንዱ የጠላት ወታደር ሲረግም አዳመጡ። ይህን በመስማታቸው በኢትዮጵያውያን ጀግንነት በጣም ደስ አላቸው። ደብረ ብርሃን በቆዩበት ጊዜ በእጃቸው የነበረው ገንዘብ ስላለቀባቸው ከገንዘብ ችግር ላይ ወደቁ።

የገንዘብ ችግር ምንም እጃቸውን ቢይዛቸው በደብረ ብርሃን ከተማ ውሎ ማደር ስላሰጋቸው ያለስንቅ በእግራቸው ጉዞአቸውን ወደ አዲስ አበባ ቀጠሉ። የሚሔዱበት የመኪናውን መንገድ ርቀው በአገሬው መተላለፊያ መንገድ ስለሆነ ወደ መንደር ጐራ እያሉ ሲለምኑ ርኅሩኅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምግባቸውን እየተዘከራቸው ሰንዳፋ ሲደርሱ አሥራ ሁለት ሰዓት ሆነ። በከተማው ውስጥ ለማደር ባለመቻላቸው ከከተማው ወጥተው ወደ እንቢሳ መንገዳቸውን ቀጠሉ። ጨረቃዋ ከፀሐይዋ ብርሃን ጋር የሚቀራረብ ብርሃን ሰጥታ ስለ ነበረ በጨረቃዋ ብርሃን እየተመሩ ሰንዳፋ ከዘመድ ቤት ለመድረስ ገሠገሡ። ምንም የጨረቃዋ ብርሃን ቢረዳቸው እንደ ፀሐይ ብርሃን ባለ መሆኑ ከመካከል ሜዳ ሲደርሱ መንገዱ ጠፋቸው። ወደ መንደር ጐራ ብለው ለማደር ቢሞክሩ ጊዜው የመሸ ስለ ነበረ መንደረተኞቹ ፈርተው የሚያስጠጋቸው አጡ። የሚደርቧት አንድ ጥቁር ብርድ ልብስ ስለ ነበረቻቸው እሷን ለሁለት ደርበው በአንዲት ዛፍ ሥር ሌሊቱን ለማሳለፍ ተቀመጡ።

ጊዜ አለ ጊዜ በመንደር መካከል በመታየታቸው ለመንደረተኛው እንግዳ ነገር ሆኖ ወዴት እንደደረሱና እንደገቡ ለማወቅ ከጥቂት ሰዓት በኋላ ተከታትለዋቸው።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ በአንዲት ጥቁር ብርድ ልብስ ተጠቅልለው፤ ድምፃቸውን አጥፍተው ከአሁን አሁን አግኝተው አንዳች ነገር ያገርጉናል ወይም አሳልፈው ይሰጡናል በማለት፤ የዛፍዋን ጥላ ከለላ አድርገው ሲጠባበቁ ሦስት ጊዜ በራስጌአቸውና በግርጌአቸው ሲተላለፉ ሳያዩአቸው ቀርተው አጣናቸው ብለው ተመለሱ። መንፈቀ ሌሊት ሲሆን የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በለሆሳስ ንግግር ጀመሩ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ የአገራችን የኢትዮጵያ ሕዝብ በእንግዳ ተቀባይነቱና በመንፈሳዊ ተግባሩ ዓለም የመሰከረለት ነው። ወገኖቻቸው የሆንን ለአንድ ሌሊት እንዲያስጠጉን ብንለምናቸው ለራሳቸው ፈርተው ሳይቀበሉን ከመቅረታቸው በላይ የመንደሩ ሰዎች ጦርና ጐራዴ ይዘው የፈለጉን ምን ለማድረግ እንደሆነ አልገባኝም። የጠላት ሠላይ መስለናቸው ይሆናል ብዬ ከመጠራጠር በቀር ሌላ ትርጉም አልሰጠውም። የጠላት የግፍ ሥራ በሕዝቡ ላይ ከፍ ያለ መለያየት ስለ ተፈጠረ፤ ሳያስጠጉን የቀሩት ለራሳቸው ፈርተው ነው። ነገር ግን ወገን፤ ዘመድ፤ ቀን ስለሆነ፤ የጊዜው ክፋት እርስ በርሳችን ሊያስተማምነን ባለመቻሉ ከማዘን በቀር ሰዎቹ ተሳስተዋል አልልም።

<u>ካሣዬ፤</u> ከከተማ በራቀ ሥፍራ የሚኖረው ሕዝብ ከደብረ ብርሃን እስከዚህ መግቦንና አሳድሮ ከዚህ ደረስን። ይህ ያለንበት ለአዲስ አበባ ሠላሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ሲቀረው ከሰንዳፋ ከተማ ቅርብ ጐረቤት ነው። ወደ መንደር ጐራ ያልንበት ጊዜ በጣም ምሽት ስለ ነበረ፤ ከጠላት የተላክን ሰላይ መስለን ስለታየናቸው ሰግተው ሊያስጠጉን ካለመቻላቸውም፤ ሁኔታችንን ለማወቅ መከታተላቸው ርግጥ ነው። የሆነ ሆኖ በመከራ ጥላ ሥራ ከወደቅን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ጥላት ከለላችን እግዚአብሔር በመሆኑ አላጋለጠንም። ለመሆኑ ይህ የመከራ ቀን አልፎ የነፃነታችንን ጻጋ አግኝተን መሪያችንን ያገኘን ጊዜ በየጊዜው የደረሰብንን መከራ እንረሳው ይሆን?

እግዚአብሔር በሙሴ ላይ አድሮ እሥራኤልን ከፈርዖን እጅ ከአወጣቸው በኋላ ወደ ኋላ፤ ያለፉትን መከራ እየረሱ ያሳዝኑት ነበር። እኛም ሰው ስለሆን የመረረውን ይህን መከራችንን፤ እንረሳለን ብዬ እፈራለሁ። በአገራችን የምጠጋበት ቤት አጥተን እነሆን ጭው ካለ ሜዳ ከአንዷት ዛፍ ሥር ተጠልለናል። በአሁኑ ጊዜ ለኢትዮጵያውያን ዘመድና ጥግ የሆኑ ዛፎች፤ ሸንተረሮችና ተራራዎች ናቸው። በሰላማዊ ዘመንማ፤ የዱር አውሬ መጠጊያና መጠለያ ነበሩ። የዱር አራዊት የሚጠጉባቸውን

ዛፎችና ሸንተረሮችን ተራራዎችንም፤ ስለቀማናቸው በኢትዮጵያ የደረሰው የግፍ ወረራ ሰብአዊ ፍጥረት በሆነው ብቻ ሳይሆን በአእዋፍና በዱር ዓራዊት ሁሉ ስለሆነ፣ እነሱም ርቀው ተሰደዋል። እንግዲህ ይህንን ከተመለከትን ዘንድ በኛ ላይ ስለሚደርሰው ሁሉ አንደነቅ።

የሌሊቱ ጨለማ በንጋት ብርሃን ተወግዶ፤ መንገዱንና አቅጣጫውን ለማየት ስለ ተቻለ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ከመነሣቱ በፊት መንገዳቸውን ቀጠሉና፤ አምቢሳ አቶ ልመንህ ቤት ደረሱ። አቶ ልመንህም ናፍቆቱን በአቀባበሉ ገልጾ በደስታ ተቀበላቸው።

# ምዕራፍ ፳።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በአቶ ልመንህ ቤት።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ በአቶ ልመንህ ቤት ብዙ ጊዜ አሳለፉ። የአዲስ አበባ ከተማን ሁኔታ በወሬ ከመስማት በቀር በዓይናቸው ባለማየታቸው፤ ለሁለት ቀን ያህል ከተማዋን ለማየት ተስማምተው አዲስ አበባ መጡ።

ቀበና ከዘመድ ቤት አድረው በማግሥቱ ከተማዋን እየተዘዋወሩ የጠላትን አቀማመጥ ሲመለከቱ፤ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ የትምህርት ቤት ጓደኛውን ከልዑል ራስ መኰንን ድልድይ አጠገብ አገኘ። የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ሁሉ እየታደኑ መያዛቸውን ገለጸለትና በከተማዋ እንዳያድር አስጠነቀቀው። አሳቡን ከተቀበለ በኋላ እኩል ሰዓት ያህል በሠዋራ ቦታ እንዲያጨዋውተው የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ ለመነውና በምሳ ሰዓት ሠዋራ በሆነ ቦታ ተነጋገሩ።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> በከተማው ማደር ለኔ በጣም አስጊ መሆኑን ስለ ገለጥክልኝ በጣም አመሰግንሃለሁ። ጥንቱንም የቀለም ጓደኛ

በሥጋ ከተወለደ ወንድም እንደሚበልጥ የታወቀ ነው። አንተ በከተማ ነዋሪ ስለ ሆንክ አንዳንድ ተባራሪ ወሬ መስማት አይቀርምና ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል የሰማኸውን ብትነግረኝ።

የትምህርት ጓደኛው፤ በከተማ፤ ስለ አገኙሁህ ሰምተህ እንደሆነ በማለት ሳልነግርህ ቀረሁ እንጂ የኢትዮጵያ የወደፊት ዕድልማ ተከፍቶ፤ የጠላት ዕድል በሩ ተዘግቶአል። በዚሁም ምክንያት ጠላት ዛሬ በንዴት ራሱ ዞሮአል። እንደምታውቀው የኢትዮጵያ አርበኞች ክንዳቸው እየበረታ በመሔድ፤ ጠላትን መድረሻ አሳጥተውታል። ከዚህም በቀር ጠላት ከጀርመን ጋር ጐን ለጐን ተሰልፎ ዓለምን ሊወጋ አስታወቀ። በኢትዮጵያም ጦርነት ሊቀጥል ተወስኖ ግርማዊነታቸው በካርቱም ሊመጡ ነው። ይህንንም ያገኙሁት ከትልቅ ሥፍራ ስለሆነ ነገሩ እርግጠኛ እንጂ ወሬ አይደለም። ሆኖም ነገሩ እየገፋ መላው ሕዝብ እስኪያውቀው ከአንተ አሳብ ወደ ሌላ አይተላለፍ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ለሰውነት ልምላሜ የሚሰጥ ጣፋጭ ወሬ ከትምህርት ጓደኛው ስለ አገኘ መንፈሱ በደስታ ተውጦ እየፈነደቀ ከካሣዬ ጋር ተጓዘ። የየካን በር እንደ ወጡ ስለ አዩትና ስለ ሰሙት ነገር ተነጋገሩ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዘዋወሩ፤ ፈተናና መታገሥ፤ የድል መንሣትን ተስፋ ያስገኛል። የጠላትን ሁኔታ ለማየት አዲስ አበባ መጥተን ከትምህርት ጓደኛዬ ያገኙሁትን ወሬ ደስ ስለ አሰኘኝ ደስታው በመላው ሰውነቴ ተሰራጨ።

ለወደፊት በዓለም ላይ ሊደርስ የሚችለውን ለማወቅ ከፍ ያለ ስጦታና ችሎታ ያላቸው መሪያችን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ በዓለም መንግሥታት ማኅበር ጉባዔ ቆመው የተናገሩት ትንቢታዊ ቃል እነሆ ተፈጸመ። በውነቱ ትንቢት ተናጋሪ መሪ ለማግኘት ታላቅ ዕድል ስለሆነ ኢትዮጵያ ኩራት ሊሰማት ይገባል። ዓለም ቢፈራውና ቢሸሸው አልቀረለትም።

የኢትዮጵያ አርበኞች ኃይል ካለፈው ጊዜ ይልቅ አሁን እየበረታ ይሔዳል። ኃይሉ ሊበረታ የቻለው፤ የግርማዊነታቸው በካርቱም መምጣት መሰማትና የኢትዮጵያ የድል አክሊል የሚገኘው በግርማዊነታቸው በመሆኑ ነው።

ስለ አገራችን ጉዳይ በተነጋገርን ጊዜ ሁሉ ጠላት ለጊዜው አገራችንን ወርሮ በመከራ ቢቀጣንም፤ ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እንደማይረሳትና አሳልፎ እንደማይሰጣት አስታውሰናል ፡

ይልቁንም የደሴን ከተማ ለማየት በዘዴ በገባን ጊዜ ከተማዋ ረድኤተ እግዚአብሔር ተለይቷት ጠላት እንደ ከብት መንጋ ሲጋፋ አንድ ሰው ያለባት አለመምሰሉን ተገንዝበን፤ ኢትዮጵያ መሬቷ ጠላትን እንዳልተቀበለች ተረድተናል።

በአዲስ አበባ ከተማ ከሌላው በበለጠ ብዛት ጠላት ሲግበሰበስ የከተማዋ ድምቀት ሰውን አይማርክም ነበር። የግርማዊነታቸውን በካርቱም መምጣት ያሰማን አምላክ የኢትዮጵያን ትንሣኤ ያሣየናል።

ካሣዬ፤ በዓለም ላይ ትልቅ ሥራ ለመሥራት የሚቻለው ሠሪው ሰውና ለመሥራት የሚቻልበት ጊዜ ሲገናኙ ነው። የኢትዮጵያ አርበኞች ተስፋ ባለመቍረጥ አገራችንን በታሪክ ከፍ ለማድረግ በታላቅ ጀግንነት ጠላትን ሲያስጨንቁ የግርማዊነታቸው በካርቱም መምጣት ለተስፋችን መድን ሆነ።

ጠላት እየተዘዋወረ ከአርበኞች ጋር ባደረገው ጦርነት እንደ ቅጠል ረግፎ ወደ ኋላ ከመሸሽ በቀር አንድ ቀንም ወደ ፊት ገፍቶ አያውቅም። ቀን ስትጐድል መሣሪያ አገልጋይነቱ ይቀርና የጦር ሠራዊቱ ከመሸሽ በቀር አይመከትም።

በዚህ ዓለም በአንዱ ላይ የግፍ ሥራ የፈጸመ የሠራውን ያህል የእጁን ሥራ እንደማያጣ የታወቀ ስለሆነ ጠላት ተግበስብሶ ከአገሩ እንደወጣ በኖ

የሚቀርበትን ቀንና ጊዜ ልናይ ነው። አዲስ አበባ በጠላት ወገን መልታለች። ነገር ግን ሰው እንዳለ ያህል የማይቈጠረው፤ አቡነ ጴጥሮስ ከመደብደባቸው በፊት በጀግንነትና በቈራጥነት፤ ኢትዮጵያ እንኳን ሕዝቡ መሬትዋ ጠላትን እንዳትቀበል አውግዘው በሰማዕትነት ያረፉ በአዲስ አበባ ከተማ ነው። በአዲስ አበባ ከተማ በጠላት እጅ የፈሰሰው የኢትዮጵያውያን ደም፤ ከመሬቷ ላይ እስካሁን አልደረቀም። ጠላት የሚግበሰበሰው በደም ላይ ስለሆነ የረገጠው ደም ከእግሩ ሳይደርቅ የራሱ ደም የሚፈስበት ጊዜ ደረሰ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ከአዲስ አበባ አምቢሳ ከአቶ ልመንህ ቤት በደህና ደረሱ። በአዲስ አበባ ያዩትንና የሰሙትን ለአቶ ልመንህ ነገሩ። አቶ ልመንህ በሰማው ወሬ በጣም ተደስቶ ምስጋናውን ለእግዚአብሔር አቀረበ።

NIGUSS DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፳፩።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ሁለተኛ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ ሲሔዱ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ በሰሙት ተስፋ ተጽናንተው ከቆዩ በኋላ ሁለተኛው ወደ አዲስ አበባ ለመሔድ ተነሡ። አቶ ልመንህም አብሮ ሔደ፤ ማናቸውንም ነገር ለማየትና ለመስማት ስለ ፈለገ ከአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ከካሣዬ ጋር ወደ አዲስ አበባ መጡ።

አዲስ አበባ ሲደርሱ፤ የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ገጽ የደስታ ብርሃን ያበራ ነበር። ጠላት ትካዜና ኃዘን ወድቆበት የሚሠራውን አላውቀው ብሎ ይባን ነበር። ከተማዋን እየተዘዋወሩ ሲመለከቱ፤ አዲስ አበባ ወደ ፊት የሚገጥማት ደስታ በፊትዋ እያንጸበረቀ ስሟን በግብሯ ትገልጥ ነበር። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ የትምህርት ቤት ጓደኛውን ስለ አጋጠመው፤ ዕድላችን ሊቃና በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድል አድራጊነት የድሉ ጐዳናው ስለ ተከፈተ አሳባችን ይሳካ ጀመር። አንተን ለማግኘት ባደረግሁት ሙከራ ድካም ሳይደርስብኝ ስለ አገኘሁህ እግዚአብሔርን አመሰገንኩ።

ከአንተ የሚገኘው ወሬ ሥጋን ዘልቆ አጥንትን የሚያለመልም ስለሆነ የሰማኸውን አካፍለን ሲል የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ የትምህርት ቤት ጓደኛውን ጠየቀ።

የትምህርት ጓደኛው፤ ካሁን ቀደም ስለ አገራችን ጉዳይ ስትጠይቀኝ ከራሴ ጋር ሦስት ሆነን በሥላሴ አምሳል ተነጋገርን። አሁን ከራሴ ጋር አራት ሆነን ለመነጋገር አንተ ሦስት ራስህን መጣህ። አሁን በምናደርገው

ንግግር አሳብ አይገባንም። ደስ ያለው ልብ ለሰውነት መልካም ነው። ዛሬ የኢትዮጵያውያን ልብ በደስታ ስለ ተመላ በያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ያለው ደስታ በፊቱ ላይ የበራል።

ዋሾና ሥንቅ እያደር ይቀላል፤ እንደ ተባለው ጠላት እኛ እንዳንሰማበት የሚነዛው የውሸት ወሬ እየቀለለና እየተለጠ ስለ ሔደ መድረሻ አጥቶ ይቅበዘበዛል።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሱዳን አገር ስለ ደረሱ «ይህ የምትሰሙት ድምፅ የኔ የንጉሠ ነገሥታችሁ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነው» ብለው ሰፋ ያለ ንግግር በራዲዮ አሰሙ።

ቀጥሎ «ከዛሬ ጀምሮ የታላቂቱ ብሪታኒያ መንግሥት ነፃነታችንን በሙሉ እንድናገኝ ተወዳዳሪ የሌለውን የጦር ኃይሉን ርዳታ ሰጠን። ይኸው እኔም መጣሁላችሁ» የሚል የግርማዊነታቸው አዋጅ በአውሮፕላን ተበተነ።

እንደዚሁም፤ ግርማዊነታቸው በድል አድራጊነት ተጉዘው፤ በአሜድላ የኢትዮጵያን ሰንድቅ ዓላማ ሲሰቅሉ አምስት ዓመት ይገፔለት የምመለስለትን ርዳታ እየጠበቀ ለነፃነቱ በክንዱና በደረቱ ከወራሪው ሲከላከል ወደ ቈየው በናፍቆት ወደ ሚጠብቀኝ ሕዝቤ ስሔድ ደስታዬ ታላቅ ነው» የሚል ንጉሣዊ ቃል ተናገሩ።

ከዚህም ሌላ፤ የኢትዮጵያን አርበኞችና ሕዝብ መንፈስ የሚያበረታታ የግርማዊነታቸው ንግግር በየጊዜው በአውሮፕላን ይበተናል። ጠላት በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመውን የግፍ ሥራ ስናስታውስ፤ አንድም ጠላት ለዘር ሳይቀር ሁሉንም ጨፍጭፎና እንደወጣ ማስቀረት አስፈላጊ ነበር። ነገር ግን ፈሪሃ እግዚአብሔርን መሣሪያ አድርገው ሕዝባቸውን የሚመሩ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጠላት ላይ ብድር እንመለስ በማለት የግፍ ሥራ እንዳይፈጸም ጠላትን በጠላት ዓይን መመልከት እንዲቀር ለሕዝባቸው አዋጅ ተናግረዋል። በእውነቱ ሰው አላፊና ጠፊ

መሆኑን የተረዳና በዚህ ዓለም የሚኖርበት ዘመኑ ሊፈጸም የሚገባ ተግባር ለሰው የሚጠቅም እንጂ ጉጂ መሆን አይገባውም። ሰው በተፈጥሮ፤ እንደሱ ሰው በሆነ ሰብአዊ ፍጥረት ጊዜ ሰጠኝ ብሎ የግፍ ግፍ ቢሠራ ነገ በራሱ ላይ የሚደርስ መከራ አከማቸ ማለት ነው።

ጠላት ኢትዮጵውያንን፤ ከአገራቸው፤ ከመሬታቸው፤ ከቤታቸው ቢያሳድድና ቢያስጨንቅ፤ እየሰበሰበ በከንቱ እንደ በግ ቢያርድ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሱ የሚታረድበት፤ የሚጨነቅበት፤ ጊዜ እነሆ እደጃፉ ቆሞ፤ የእጅህን ተቀበል እያለ ያስደነግጠዋል። የኢትዮጵያውያንስ ስደትና ጭንቀት በአገራቸው ስለሆነ፤ በሞት ከተደበደቡት በቀር በሕይወት ያለው ከአገር አገር እየተዘዋወረ ቈየ።

ጠላት የፈሰሰው በሰው አገር ስለሆነ፤ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ቂሙን ለመቀበል ቢፈልግ፤ ለወሬ ነጋሪ የሚሆን የጠላት ዜጋ፤ ልጅም፤ ሽማግሌም፤ ሳይቀር እንደወጣ የጠላት እንዲቀር ማድረግ ይችል ነበር። አርቆ የመመልከት ሰፊ ችሎታና እውቀት የተሰጣቸው የኢትዮጵያ መሪ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ ይህንኑ አውቀው ከመናገሻ ከተማቸው ሳይገቡ በጠላት ላይ የበቀለ ሥራ እንዳይፈጸም መሪ ትእዛዝ ሰጡ። የመሪውን ትእዛዝ ጠባቂና አክባሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በጠላቱ ላይ በቀል ሳያደርግ እንደሚያልፈው የታወቀ ነው።

ግርማዊነታቸው በድል አድራጊነት ዘንባባ አጊጠው ጉዞአቸውን ቀጥለዋል። በምሥራቅም በኩል የኢትዮጵያ ጦር ድል አድርጎ አዲስ አበባ ለመግባት ይጣደፋል። ከአንድ ሳምንት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ጠላት እጁን ሰጥቶ የኢትዮጵያ ጦር አዲስ አበባ ይገባል። ስለዚህ ወደ ውጪ ሳትሔዱ፤ ከዚህ ሆናችሁ ብታደምጡ ሁሉንም ነገር ትሰማላችሁ። የጠላት ልብ በፍርሃትና በድንጋጤ ስለ ተዋጠ ሰው ማሳደዱ ቅርቶ፤ ራሱ የሚሰደድበትና የሚጠጋበት አጥቶ በጭንቅ ላይ ስለሆነ ሥጋት የለባችሁም።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ ከአቶ ልመንህ ጋር ሆነው በሰሙ ጊዜ ደስታቸው ይህ ነው ተብሎ ሊነገር ተወዳዳሪ ንግግር አይገኝለትም። አቶ ልመንህ በአዲስ አበባ ለመሰንበት በቤተ ሰቦቻቸው ምክንያት ስላልቻሉ፤ በሰሙት እየተደሰቱ ወደ ቤታቸው ሲሔዱ የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በአዲስ አበባ ቆዩ።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል ግርማ በኦሜድላ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ መስቀላቸው ከተሰማ ጀምሮ፤ ጸጋው ተገፎ የነበረ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጸጋ ልብስ ተጐናጸፎ በከተማዋ ሲዘዋወር ረድኤተ እግዚአብሔር አድሮበት ይታያል። አርበኞችና ስደተኞች፤ ከያሉበት ተሰብስበው ግርማዊነታቸውን አጅበው ጠላትን እያሳደዱ ግርማዊነታቸው ደብረ ማርቆስ ገቡ። በምሥራቅ ያለውም የጦር ወታደር ድልን ተጐናጽፎ አዲስ አበባ ሊገባና ጠላት እጁን እንዲሰጥ ሊገደድ ነው። አውሮፕላኖችም በጠላት ላይ እያንዣበቡ፤ ቦምብ ከመጣል አቆሙ። ጠላት መድረሻ ቢያጣ ወደ ጂማና ጐንደር ሌሊቱን ሲሸሽ ሰንብቶአል። ጂማ ወይም ጐንደር ቢሸሽ ጂማና ጐንደር ኢትዮጵያ መሆናቸውን ዘንግቶ ይሆን?

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የድል ጸጋ ለብሰው ደብረ ማርቆስ ሲገቡ፤ ለባዕድ አንገዛም በማለት በገደል፤ በዱር፤ በገደል፤ በውጪ አገር መሰደድ፤ መከራ መቀበል፤ መራብና መጠማት እንዲደርስለት የሚመኘውን ለማየት ያበቃል።

«እግዚአብሔር ለሠራልን ችሮታ ሁላችንም የተገባን ሁነን መገኘት አለብን። ውለታውንም የምመልስበት ቂም፤ በቀል ትተን የፍቅርና የመተባበርን መንገድ ተከትለን፤ አምስት ዓመት በጨካኝ አጥቂ ስትሠቃይ የቈየችውን አገራችንን ማገልገል፤ ወደ ከፍተኛ ሥልጣኔ ደረጃ አድርሰን፤ የሚከተለው ትውልዳችን ከወራሪ ፈተና የሚድንበትን ሠርተን በማቆየት ነው» ብለው ንጉሣዊ ቃል ተናገሩ።

በጠላት ላይ በቀል በመፈልግ፤ ጠላት እንዳይጉላላ ቀደም አድርገው መሪ ትእዛዝ ሰጡን።

ደግሞ አሁን ልናደርገው የሚገባውን የወደፊት መመለስ የምንችለው ቂም በቀል ረስተን እብፍቅር ተሳስረን አገራችንን በሥልጣኔ ደረጃ ለማሳደግ እንድንፋጠንና ተከታዩ ትውልድ ከዳግም ወረራ የሚድንበትን ከፍ ያለ ሥራ ስንሥራ ነው።

የነጻነት ጸጋዋን ተገፎ በነበረ ጊዜ በያንዳንዳችን ልብ ይመላለስ የነበረው ሊረሳን አይገባም። እንግዲህ በነጻነት ጸጋ ስንጐንናጸፍ የመንፈስ መለያየት ሳይኖርብን መከራችንን ሳንረሳ በፊታችን እያስታወስን ለአገራአችን ከልብ ልንሥራላት ይገባናል።

በዚሁ በግርማዊነታቸው ንግግር «ባንዳ፤ ሽፍታ መባባል ካልቀረ የርስ በርስ መፋቀር አይገኝም የሚል ታሪክ የተጐናጸፈው ኃይለ ቃል ይገኛል። ታላቅ መሆን የሚወድ ቅን አገልጋይ መሆን አለበት። ሰው ፊትን ያያል። እግዚአብሔር ግን ልብን ይመለከታል። ሁሉም የሥራውን ዋጋ ስለማያጣው ፍቅርን፤ ኅብረትን፤ ልባዊ ቅንነትን መሣሪያ አድርጎ ወደ ፊት መራመድ ብቻ አገራችንን ይጠቅማታል እንጂ ወደ ኋላ ያለፍነውን እናጣራ ያልን እንደሆነ አንዘልቀውም።

ካሣዬ፤ መከራ ያልመከረውና ያላስታገሠው ሌላ ነገር ሊያስታግሠው አይችልም። በግፍ ሞት ከተቀጡት በቀር ከአሁን አሁን የሞት ጽዋዬን እቀበላለሁ እያለ ሲጠባበቅ የነበር፤ ያ የጨለማ ጊዜ አልፎ በግርማዊነታቸው ድል አድራጊነት ብርሃን ሲወርድ በብርሃኑ እየተመራን ለበጎ ሥራ መሽቀዳደም የመጀመሪያ ሥራችን መሆን አለበት።

በሁለታችን ብቻ የደረሰውን መከራ ስናስታውስ ትዝታው በፊታችን በመጣ ጊዜ እንደ ኢዮብ የተፈጠንባትን ቀን እስከ መርገም ያስመኘናል። መከራ ለሰው መምህር ነው። በአገራችን ጠላት ይህን ያህል የግፍ

መቅሰፍት የፈጸሙብን በምን ምክንያት እንደ ሆነ መርምረን ካወቅን ዘንድ መድኃኒቱን መፈለግ አለብን።

# ምዕራፍ ፳፪።

## የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ የግርማዊነታቸውን መምጣት ሲጠባበቁ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ የግርማዊነታቸውን መምጣት ሲጠባበቁ፤ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም እንደሚገቡ ሰሙ። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ በናፍቆት ይጠባበቁ የነበረው የኢትዮጵያን ትንሣኤ በማየታቸው እጅግ ተደስተው የግርማዊነታቸውንም የታሪክ ሰውነት ለማየት ናፈቁ። ግርማዊነታቸው የሚገቡበት ቀን ስለ ደረሰ የአዲስ አበባ ከተማ በደስታ አሸብርቃ ስትጠባበቅ፤ ግርማዊነታቸው በድል ግርማ ታጅበው በእንጦጦ ብቅ ሲሉ፤ የአዲስ አበባ ከተማና ሕዝብ ከመጠን በላይ በሆነ ደስታ ተቀበላቸው። የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ ምኞታቸው ሰለ ተፈጸመ፤ ለፈጣሪአቸው ልባዊ የሆነ ምሥጋናቸውን ገልጸው ወደ ኋላ ያለፉትን እያስታወሱ መነጋገር ጀመሩ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤ እግዚአብሔር ምድርን ለሰው ሥጋዊ መርኖሪያው እንዲሆን ፈጠረ። እያንዳንዱ እንደ ወገኑ የሚኖርበትን ከፍሎ በቋንቋና በመልክ ለይቶ ሰጠ።

ሰው የራሱ አልበቃው ብሎ፤ የሰውን ቡቃያ አልፎ በማየት ዘወትር ከስሕተት ይወድቃል። አገራችን ኢትዮጵያ የሰው የማትፈልግ፥ እንግዳ ተቀባይና በአምልኮተ እግዚአብሔር የጸናች አገር ስትሆን፥ የራሱ አልበቃው ያለ ጠላት ከአካሏ ቈርጦ የያዘው አንሶት ታሪኳን ለማጥፋት በትዕቢትና በጥጋብ ወርሮ አምስት ዓመት በከርሠ መቃብር አደረች።

በታላቅ ትግልና ድካም ንጉሠ ነገሥቷ ከከርሠ መቃብር አሥነስተው ሕይወታዊ ትንሣኤዋን አሳዩን። የዛሬዋ ቀን ታሪክንና ደስታን አስተባብራ የያዘች ቀን ናት። በናፍቆት የምጠባበቃቸው ንጉሠ ነገሥታችን በድል አድራጊነት በዋና መናገሻ ከተማቸው ገብተው በመካከላችን ተገኙ። የአገራችንን ትንሣኤና ንጉሠ ነገሥታችንን ካየን፤ በተፈጥሮ ግዴታ የምንሞተው ሞት አሁን ቢፈጸም አያሳዝነንም። «አቤቱ ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋልና፤ በሕዝብም ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን፥ ብርሃን ለአሕዛብ ትገልጽ ዘንድ ክብርህንም ለሕዝብህ»

<u>ካሣዬ፤</u> የእግዚአብሔር በረከት በጻድቃን ራስ ጸንቶ ይኖራል። ጥላ ከለላችን እግዚአብሔር ሆኖ በተደረገው ተጋድሎ፥ በብዛት የፈሰሰው የኢትዮጵያ ደም በበረሓ የተንከራተቱት የአርበኞች ድካም፥ በረሓብና በችግር የተጐሳቈሉት የስደተኞች ልፋት፤ በቤቱ ውስጥ የተደበደበውና የግፍ ሥራ የተፈጸመበት ኢትዮጵያዊ፥ ይህ ሁሉ ግፍና በደል በአንድ ላይ ተጠቃሎ ያደረገው ጩኸት፤ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሣሪያ ሆኖ እነሆ ኢትዮጵያ በግርማዊነታቸው ትንሣኤ አገኘች።

ግርማዊነታቸው ድልን ተጐናጽፈው በዋና መናገሻ ከተማቸው ሲገቡ፥ «የሰማይ መላእክት፥ የምድር ሠራዊት ሊያስቡትና ሊያውቁት ይቻላቸው ባልነበረ በዚህ በዛሬ ቀን፤ ቸር እግዚአብሔር በመካከላችሁ ለመገኘት ሳለበቃኝ በሰው አፍ የሚነገር ምስጋና የሚበቃ አይደለም።»

«ልትረዱት የምፈልገው ይህ ቀን ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ ያዲስ ታሪክ ዘመን መከፈቻ መሆኑን ነው።» ብለው ተናገሩ።

ከወገኑ ጋር የሚራዳ የማይጣስ ምሽግ እንዳለው ከተማ ነው። ወደ ኋላ ትተነው የመጣነው መከራ ወደ ፊት ለምንሠራው ሥራ በታሪክ ፊት ምስክር ይሆንብናል። መምህር ለደቀ መዛሙርቱ የሚገባውን የመምህርነት ተግባሩን ከፈጸመ፤ መቀበልና የመምህሩን ትምህርት እስከ መጨረሻው ግብ ማድረስ የደቀ መዛሙርቱ ፋንታ ነው።

መሪያችንና መምህራችን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ በድል አድራጊነት አገራቸው ገብተው የኢትዮጵያን ትንሣኤ ከአበሠሩ በኋላ፥ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወደ ፊት ሊያደርገው የሚገባውን ዘርዝረው ዕለቱን ነገሩን።

በግርማዊነታቸው መሪ ትእዛዝ በእያንዳንዳችን አእምሮ ተቀርጾ ለተከታታዩ ትውልድ ዘለዓለማዊ ሆኖ የሚኖር ነው። ይህ የግርማዊነታቸው ንግግር የታሪክ ገጽ ይዞ የሚኖር ትውልድ የሚቀበለው ነው።

ግርማዊነታቸው በሰጡን መሪ ትእዛዝ ሠርተን ለተከታዩ ትውልድ እንደ ቀዋሚ ነገር ካላቆየን፤ ተከታዩ ትውልድ የግርማዊነታቸውን የታሪክ ሰውነት ሲመለከትና፤ ግርማዊነታቸው ስለ ኢትዮጵያ በየጊዜው የሰጠውን መሪ ትእዛዝ ከሠራውነው ሥራ ጋር ሲያመዛዝን፤ ውጤቱ ያነሰ እንደሆነ፤ ለአሁን ትውልድ ኃፍረት ይሆንበታል። ስለዚህ የወደፊቱም ትግል ከጦርነት የበለጠ የሚያሳስብ ስለሆነ፤ የግርማዊነታቸውን መሪ ትእዛዝ በልበ ሕሊናችን ጽፈን መያዝና በሥራ ማዋል አለብን።

ወደ ፊት ባለው ሕይወታዊ ኑሮ፤ ሊሠራ የሚገባውን የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ የግርማዊነታቸውን ታሪካዊ ንግግር እየጠቀሱ በሰፊው ከተነጋገሩ በህውላ በአዲስ ዘመን አዲስ ሥራ በግርማዊነታቸው ትጋት ስለ ተቋቋመ እንደየ ዕድላቸው ሥራ ይዘው ለአገራቸው በእውነትና በቅንነት ለማገልገል ቍርጥ አሳብ አደረጉ።

<u>የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈ፤</u> ካሣዬ ስለ አገሬ ነፃነትና ሰለ ንጉሠ ነገሥቴ ክብር፤ ደሜን ለማፍሰስ ወደ ማይጨው አብረን ሔደን፤ የመከራውን ጽዋ እኩል ጠጣን። መከራውን አብረን እንደ ተካፈልን፤ የኢትዮጵያን ሕይወታዊ ትንሣኤና፤ ግርማዊነታቸውንም ዓይተን ደስታውን አብረን ተካፍለን። እንግዲህ በየጊዜው እየተገናኘን ፍቅራችንን

እናጸናለን። አገራችንንም በምችለው መጠን ልባዊ በሆነ ፈቃድ እንድናገለግል እግዚአብሔር ይርዳን።

ካሣዬ፤ ተግሣጽ ለጊዜው ደስ አያሰኝም፤ ኋላ ግን የጽድቅ ፍሬ ያፈራል። ባልፈው መከራ እግዚአብሔር ቢገሥጸን፤ ምሕረቱንም መልሶ በዓይናችን አሳየን። ከጭንቅ፤ ከሥጋት ከመባነን ድነን፤ እንደ ልባችን የሕይወት እንቅልፍ አገኘን። እንግዲህ የመከራ ጓደኛ አይረሳሳምና፤ እንደየችሎታችን አገራችንንና ንጉሠ ነገሥታችንን እያገለገልን እንተሳሰብ።

የአምሳ አለቃ በድሉ ተረፈና ካሣዬ፤ የመሰነባበቻ ንግግራቸውን ከፈጸሙ በኋላ፤ የሚከተለውን መዝሙር በሕብረቱ ዘምረው፤ ከቤተ ሰቦቻቸው ጋር ለመቀላቀል ተሰነባብተው ተለያዩ።

## መዝሙር።

ሰላም ላንተ ይሁን ጠቅል የኛ ጌታ
ለሕዝብህ የሆንከን ጋሻና መከታ

ውለታው ብዙ ነው ጠቅል ፈረስህ
አድርሶህልና ከውድ አገርህ

ታምራተ ብዙ ልዩ በመንፈስ
ጠላት የሚያስወግድ የነፃነት ዋስ
ተፈሪ አባ ጠቅል ታዳጊው ንጉሥ።

መሪር እንባ አልቅሼ ቀና ብዬ ባይ፤
ጠቅል መጣ እያለ ነፈሰ ሰማይ።

ሰማዩ ሲነፍስ ያየ ሁሉ ጠላት፤
ተረዳው አወቀው መግባቱን ከአዘቅት።

እናት ኢትዮጵያ እጆቿን ዘርግታ፤
አመጣች ጠቅልን ከለንደን አንሥታ።

ተፈሪ አባ ጠቅል ረቂቁ ንጉሥ፤
ሌት ተቀን ሳይተኛ ደረሰልን በነፍስ፤
የወደቅን ሕዝቦቹን አነሣን በመንፈስ።

በችግር በረሓብ የተራቈተው፤
በሥራት በውርደት የተጨነቀው፤
ጠቅል ደርሶለት ነው ሁሉም የዳነው።

ተጋዳይ አርበኛ ወገን ያኰራችሁ፤
በታሪክ ተፃፈ መሥዋዕትነታችሁ፤
የነፃነት አክሊል ደፉ ወገናችሁ፤
መሠረቱ ቆመ የመታሰቢያችሁ፡

አይተነዋልና የጠላትን እጅ፤
መውጣት ያቃተንን ከቤታችን ደጅ፤
ነፃነት ተገኘ በሉ እንቀዳጅ።

አሥራ ስድስት ሐምሌ ጥቅምት ሀያ ሦስት፤
ከብረው ይኖራሉ ዘለዓለም ከጥንት፤
በማስገኘታቸው ለሕዝብ ሕይወት።

ጥንትም ሲከልላት አገራችንን፤
ወሰን አድርጎ ነው ባሕር ጠረፍዋን፤
ጠላት ግን አሳቡን የዘረጋብን፤
ማጥፋት ብቻ ነበር መልካም ታሪኳን፤
አባ ጠቅል እንጂ አደሰው ስሟን።

አምስት ዓመት ሙሉ ያየሁትን ግፍ፤
ይገባኛልና መናገር መጻፍ።

ኧረ በርቱ በርቱ እንበርታ በጣም፤
ጠቅል ተወለደ ንጉሥ ሰላም።

እንወቅ እንወቅ እንወቅ ተማሩ፤
ከኃይለ ሥላሴ ከጥበብ መምህሩ።

ደስ ይበለን ዛሬ ተገኝቷል ፍሥሓ፤
በኃይለ ሥላሴ እናቅርብ አምኃ፤
ጠላታችን ሆኗል የፈሰሰ ውኃ።

## ተፈጸመ።

አነቃቅቶ ለአስጀመረኝ

አስጀምሮ ላስፈጸመኝ

አምላክ ክብርና ምስጋና ይግባው።

ይኸች መጽሐፍ ለግርማዊነታቸው ፷፫ኛ ኢዮቤልዩ መጀመሪያ ታተመች። አንዳንድ አሳቦችን በማስታወስ ተሻሽሎና ማውጫ ተጨምሮ ሁለተኛ ስትታተም ገጽ ጨምራለች።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

## የደራሲው ሥራዎች

1. ኢትዮጵያና ኢየሩሳሌም (**ታሪክ**)
2. የማይጨው ቁስለኛ (**ልብወለድ**)
3. የዓለም ሰው እርምጃ (**ልብወለድ**)
4. ያይኔ ብርሃን (**ልብወለድ**)